# ክፍል አራት

## የኤርትራ ጉዳይ በአራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ

## (መስከረም- ኅዳር 1949)

ገጽ

1. ለመስከረሙ ቀጠሮ የኢትዮጵያ ዝግጅት ........ 193
2. የጣልያን ሤራ ........ 204
3. የአራቱ ኃያላኖች አቋም ........ 209
4. ጠቅላላው ጉባኤ ሥራውን ሲጀምር ........ 212
5. የኤርትራ ጉዳይ በዋናው ኮሚሲዮን ........ 216
6. ኤርትራ! በኢብራሂም ሡልጣን አስተያየት ........ 227
7. ኢብራሂም ሡልጣን ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች ጋር ........ 229
8. ሕዝቡ የጠየቀው ኢትዮጵያዊነትን ነው ........ 241
9. ንዑስ ኮሚቴ "17" ........ 244
10. የዋናው ኮሚሲዮን ችሎት ........ 255
11. የጠቅላላው ጉባኤ ውሳኔ ........ 259
12. የአክሊሉ ምሬት "...... ጸበ ለጠየቀ ድንጋይ ......" ........ 264
13. በአዲስ አበባ እና በሮማ ........ 271

ለክቡር ወዳጄ ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን፣

« ...... በላኩልኝ ማስታወሻ የገለጹትን አስተያየትና የሰጡኝንም ሀሳብ ተመልክቼዋለሁ:: እርስዎ ያደረብዎ ሥጋት ከእኔ ስሜት ጋር ተመሳሳይ ነው:: እርስዎ እንደአሉት ጉዳያችን እንደአለቀለት አድርገን እርግጠኞች ሆነን መቀመጥ አንችልም:: ሆኖም ሞራላችንን ከፍ አድርገን ለትግሉ ዝግጁ መሆን አለብን:: ወዳጆቻችን የሆኑት ዋና ዋናዎቹ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች በገለጹልኝ አስተያየት፣ በመስከረሙ ጉባኤ ላይ ብዙ ጭቅጭቅ ሊፈጥር የሚችለው፣ የሊቢያና የሱማሌ ጉዳይ ነው እንጂ፣ ከፍተኛ ድጋፍ ያገኘው የኤርትራ ውሳኔ ያለ ችግር እንደሚጸድቅ፣ ተስፋ ሰጥተውኛል::

አሁን ያለውን ሁኔታ ስንመለከት፣ ይህ አስተያየት ትክክል ነው ማለት እንችላለን:: ሆኖም የፖለቲካ ጉዳይ በተሰጠው ግምት ጸንቶ ይፈጸማል ማለት ስለማይቻል፣ ከኛ በኩል ይኸ ጉደለ የሚባል ነገር እንዳይኖር፣ ማናቸውንም ጥንቃቄና ዝግጅት ማድረግ እንገደዳለን:: ...... ሁለተኛ፣ እርስዎ እንዳሉት የላቲን አሜሪካ አገሮች ዋና ዓላማ፣ ጣልያንን መርዳትና በማናቸውም ጉዳይ ለጣልያን መታዘዝ ስለሆነ፣ ጠላታችን በሚያዘጋጅልን ተንኮል ተባባሪነታቸው የማይቀር ነው:: ..... እኛ አቅማችን የሚፈቅድልን ቢሆን ኖሮ፣ ለመጭው መስከረም ወር፣ የጣልያን መንግሥት ምን ዓይነት ተንኮል እንደአቀደብን በቅድሚያ ማወቅ በጣም ይጠቅመን ነበር:: ነገር ግን የገንዘብና የሰው ኃይል ስለሚያጥረን፣ የጠላታችንን ተንኮል የምንሰማው ዝግጅቱ ሥር ከሰደደ በኋላ ነው:: በዚህ ምክንያት የምናደርገው ጥረት ሁሉ በተከላካይ ቦታ ላይ ብቻ እንድንሆን ይወስነናል:: አሁንም የተቻለንን ያህል መፍጨርጨር ስለሚያስፈልግ፣ ወደ ላቲን አሜሪካ አገሮች ረዥሙን ጉዞ እንዳደርግ የተወሰነው፣ እስካሁን ሲነዛብን የቆየውን የጠላታችንን የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ለመከላከል ይረዳን ይሆናል ተብሎ ነው::

...... ከእኔ ጋር አብረውኝ እንዲጓዙ የተፈቀደው፣ ክቡር አቶ ተስፋዬ ተገኝ በፓሪስ የገርማዊነታቸው ሚኒስትር እና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ልጅ አምሩ ዘለቀ ብቻ ስለሆኑ፣ እርስዎ ያሉት ሰው አብሮኝ እንዲጓዝ አልታሰበም:: ቢቻል ገብረመስቀል ክፍለእግዚአ ቢጨመርልኝ ደስ ይለኝ ነበር:: ነገር ግን በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ወጭው ይከብዳል ስለሚባል፣ መሳካቱን እጠራጠራለሁ:: ...... እርስዎ እንደአሳሰቡኝ ሁሉ፣ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ጉዳያችን በጥሩ ይፈጸምልናል ብለን ተስፋ ብናደርግም፣ በአለፈው ጊዜ እንደደረሰው፣ በጣም አስቸጋሪ በሆነው በሱማሌ ምክንያት፣ የምንጠብቀው ሳይወሰን ወይም ሊጓተት እንደሚችል፣ ጸሐፊ ትእዛዝ ባሉበት ለጃንሆይ በሰፊው አስረድቻለሁ:: እርስዎም አዲስ አበባ እንደተመለሱ በተጨማሪ ለማስረዳት እንደሚችሉ አምናለሁ::

በጠቅላላው ስለገለጹልኝ ቁም ነገር ያለው አስተያየት ከልብ እያመሰገንኩ፣ በየጊዜው ከርስዎ የሚደርሰኝ ምክርና አስተያየት በጣም የሚጠቅመኝ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ልገልጽልዎ እወዳለሁ::

ወዳጅዎ አክሊሉ ሀብተወልድ

አቶ አክሊሉ እና ብላታ ኤፍሬም የተለዋወጧቸው አስተያየቶች በግልጽ የሚያስረዱት፣ መስከረም 20 ቀን 1949 ዓ.ም በሚከፈተው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ፣ የኤርትራ ጉዳይ በቀላሉ ይፈጸማል ብሎ እርግጠኛ መሆን አለመቻሉን ነው:: ከዚህም በቀር ለጉባኤው ዝግጅትም ሆነ ለሚያስፈልገው ሙግት፣ ኢትዮጵያ ብዙ ችግር እንደአለባት መገንዘብ ይቻላል:: የገንዘብና የሰው ኃይል ስለሚያጥራት፣ በጠላት በኩል የሚጠነሰስባትን ተንኮል ዝርዝሩን በቅድሚያ ለማወቅ አልቻለችም:: የጣልያን መንግሥት ግን በቂ አቅም ስላለው፣ ከተባበሩት መንግሥታት አባሎች መካከል፣ አንዳንዶቹን በገንዘብ በመግዛት፣ ሌሎቹን

# ለመስከረሙ ቀጠሮ የኢትዮጵያ ዝግጅት

በ1949 ዓ.ም በሰኔ ወር መጨረሻ በገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ስለ ኤርትራ ጉዳይ ጃንሆይ በአደረጉት ከፍተኛ ስብሰባ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ አክሊሉ ሀብተወልድ ያቀረቡት ሪፖርት ከተደመጠ በኋላ፣ ልዑል ራስ ካሣ « ..... አሁን የሚያስፈልገን ጠበቃችን ለመስከረሙ ሙግት ደህና አድርጐ እንዲሰናዳ አደራውን መስጠት ነው ..... » ሲሉ በተናገሩት መሠረት፣ ንጉሠ ነገሥቱ መወሰናቸው ይታወሳል::

በግንቦት 17 ቀን 1949 ዓ.ም በተደረገው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ ከፍተኛውን ድጋፍ ያገኘው የኤርትራ ጉዳይ፣ በመጨረሻ ሳይጸድቅ ተንጠልጥሎ በቀጠሮ የተላለፈው፣ የጣልያን ወደ ትሪፖሊታንያ እና ሱማሌ የመመለስ ዕድል፣ በመሰናከሉ ምክንያት ስለሆነ፣ በመስከረሙ ስብሰባ ላይ ትክክለኛው ፍርድ ተገኝቶ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች ፍጹም ደስታ ይሆናል ተብሎ በናፍቆት ይጠበቃል:: ምንም እንኳን ጥቂት ሰዎች ከሐምሌ እስከ መስከረም ባለው ጊዜ ውስጥ፣ ምን እንደሚፈጠር አይታወቅም እያሉ ቢሰጉም፣ በንጉሡ ነገሥቱና በአካባቢያቸው፣ በጠቅላላውም በመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ዘንድ፣ ከእንግዲህ ወዲህ፣ የኤርትራን ጉዳይ እንቅፋት ሊያጋጥመው ይችል ይሆናል የሚል ሀሳብ አላደረም:: እንደ እውነቱም ከሆነ፣ አዲስ አበባ ሆኖ ጉዳዩን ለተከታተለው፣ በዚያን ሰዓት ያለው ጠቅላላ ሁኔታ ሙሉ ተስፋ የሚሰጥ እንጂ፣ ጥርጣሬ የሚያሳድር ነገር አልታየበትም::

የሶስቱ ኃያላን መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፣ የአሜሪካው ዲን አቸሰን (DEAN ACHESON) የታላቋ ብሪታንያ ኤርነስት ቤቨን፣ (ERNEST BEVIN) የፈረንሣዩ ሮበርት ሹማን፣ (ROBERT SCHUMAN) በመስከረም 20 ቀን 1949 ዓ.ም በሚከፈተው የተባበሩት መንግሥታት አራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ ባለፈው ግንቦት ወር መንግሥቶቻቸው የተስማሙበት የኤርትራ ውሳኔ እንዲጸድቅ፣ ሙሉ ድጋፍ የሚሰጡ መሆናቸውን፣ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አረጋግጠዋል:: በዚህ ሁኔታ ሲታይ፣ በመስከረሙ ጉባኤ ላይ በአባል መንግሥታቶች መካከል ንትርክ የሚፈጥረውና፣ አንድ ዓይነት ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚያስቸግረው፣ የሊቢያና የሱማሌ ጉዳይ ነው ብሎ ለማሰብ አያዳግትም:: ይሁን እንጂ በነዚህ በሁለቱ አገሮች ላይ ጣልያን ሞግዚት ሆና ማስተዳደር አይገባትም የሚለው የዓረቦቹና የእስያውያኖቹ ተቃውሞ፣ በዚህ በመስከረሙ ስብሰባ ላይ የበለጠ ተጠናክሮ ከመጣ፣ ሌላ ምን ዓይነት መፍትሔ ተገኝቶ አብዛኛዎቹ አባል መንግሥታቶች ሊስማሙ ይችላሉ ? ......

– ፕሮብሌሙ እየተወሳሰበ መጥቶ፣ የሊቢያና የሱማሌ ችግር የማይፈታ ከሆነ፣ ባለፈው ጊዜ በስሎ ለውሳኔ ብቻ የቀረበውን የኤርትራን ጉዳይ እንደገና መልሶ ጥሬ አያደርገውም ወይ ? .......

በሶስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ምኞቷ ሳይሳካላት የቀረችው ጣልያን፣ የላቲን አሜሪካ ወዳጆቿን ይዛ፣ በዚህ በአራተኛው ስብሰባ ላይ፣ የኢትዮጵያን ዕድል ለማሰናከል ምን ዓይነት እንቅፋት ትደነቅር ይሆን ? ...

አቶ አክሊሉ ሀብተወልድና ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን፤ የአራተኛውን የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ቀጠሮ የሚጠብቁት፣ በዚህ ዓይነት የሥጋት መንፈስ እንደነበረ አንዳንድ ማስረጃዎች ያሳያሉ:: በሐምሌ 1949 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ፤ ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በላኩላቸው የግል ማስታወሻ እንዲህ የሚል ቃል ይገኝበታል::

*ወዳጄ ክቡር አቶ አክሊሉ፤*

*« ...... ጉባኤያችን ካለቀ ጀምሮ እስካሁን ድረስ፣ የመስከረሙ ቀጠሮአችን በአእምሮዬ እየተመላለሰ ማስጨነቁን አልተወኝም:: እንደምታውቀው ነገር በቶሎ ሲቆረጥ ጥሩ ነው:: ውሎ ሲያድር ብዙ ጊዜ ለጠላትና ለክፉ ነገር ይበጃል:: ያ ሁሉ ድካም የተደረገበት ጉዳያችን፣ በግንቦቱ ስብሰባ ባለማለቁ ዕድለኞች ሳንሆን ቀርተናል:: ..... ለመስከረሙ ስብሰባችን፤ የየመንግሥታቱ መልዕክተኞች፤ ሀሳባቸውን ሳይለውጡ የሚዘልቁና ጉዳያችን እንደሚጸድቅልን፤ እርግጠኞች መሆን የምንችል አልመሰለኝም:: በተለይ ግሊያን፣ ትሪፖሊታንያን እና የሞቃዲሾ ሱማሌን የማታገኝ ከሆነ፤ እነዚያ አፈኞች የላቲን አሜሪካ መንግሥቶችን፣ ጉዳያችንን ለማዘናከል ከጣሊያን ጋር እንደሚሆኑ ጥርጥር የለውም:: በታላላቆቹ በእንግሊዞችና በአሜሪካኖች በኩል የሚኖረን ድጋፍ፣ ያድነን እንደሆነ አላውቅም:: የችግራችንን ክብደት ሳወራህ፤ ለዚህ የሚበጀው ምን እንደሆነ፣ አንተ ካቀድከው የተለየ የማቀርብልህ ሀሳብ የለም:: በላቲን አሜሪካ አገሮች እየተዘዋወርክ አስተያየታቸውን እንዲለውጡ የምታደርገው ድካም እንዲባረክ፣ ሙሉ ምኞቴና ተስፋዬ ነው:: በመጨረሻም ሁለት ሀሳቦች ልገልጽልህ እወዳለሁ::*

*1ኛ/ ለመስከረሙ ቀጠሮአችን ብዙ ሥራ ስለሚጠብቀን፣ ጃንሆይ የኤርትራ ጉዳያችንን እንደአለቀ አድርገው በሙሉ ተስፋ እንዳይጠብቁ፤ አንዳንድ ችግር ሊኖር እንደሚችል አጥብቀህ ብታስረዳቸው አስፈላጊ ይመስለኛል::*

*2ኛ/ የላቲን አሜሪካ አገሮች፤ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ለኢትዮጵያ ደጋፊና ለጣሊያን ተቃዋሚ ነው ብለው ስለሚያምኑ፣ወደ ላቲኖቹ ስትሄድ አማካሪው (ስፔንሰር) ባይከተልህ ጥሩ ነው:: ይኸ ሰው ቅን ሀሳብ ያለውና ጥሩ አገልጋይ ቢሆንም፣ በላቲኖቹ ዘንድ እንደ ሰላይ ስለሚቆጠር፣ ለጉዞህ የሚረዳ ስለአልመሰለኝ ነው::*

*በል ወዳጄ ክቡር አቶ አክሊሉ፣ እኔ ተጨንቄ አንተን የባሰ ለማስጨነቅ ሀሳቤ አይደለም:: የሚሰማኝን ልንገርህ ብዬ ነው:: ..... ለሁሉም እግዚአብሔር ይርዳን ..... »*

*ወዳጅህ ብላታ ኤፍሬም ተወ/መድህን*

በፖለቲካ ትግል ዛሬ በትልቁ የተገነባው፣ በማግሥቱ በቀላሉ እንደሚፈርስ፣ ዛሬ የፈረሰውም ወዲያውኑ በፍጥነት እንደሚገነባ የታወቀ ስለሆነ፣ የኤርትራ ጉዳይ ባለፈው ግንቦት ወር የተሰጠው ከፍተኛ ድጋፍ፤ እስከ መስከረም ጸንቶ ስለመቆየቱ ዋስትና አለመኖሩን፣ ብላታ ኤፍሬም የገለጹት የሥጋት አስተያየት መሠረት ያለው ነው:: የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም ወዲያውኑ በሰጧቸው መልስ፤ ተመሳሳይ የሆነ ስሜታቸውን እንዲያውቁት አድርገዋል::

*ለክቡር ወዳጄ ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን፣*

*« ...... በላኩልኝ ማስታወሻ የገለጹትን አስተያየትና የስጡኝንም ሀሳብ ተመልክቼዋለሁ:: እርስዎ ያደረብዎ ሥጋት ከእኔ ስሜት ጋር ተመሳሳይ ነው:: እርስዎ እንደአሉት ጉዳያችን እንደአለቀለት አድርገን እርግጠኞች ሆነን መቀመጥ አንችልም:: ሆኖም ሞራላችንን ከፍ አድርገን ለትግሉ ዝግጁ መሆን አለብን:: ወዳጆቻችን የሆኑት ዋና ዋናዎቹ የተባበሩት መንግሥታት አባሉች በገለጹልኝ አስተያየት፣ በመስከረሙ ጉባኤ ላይ ብዙ ጭቅጭቅ ሊፈጥር የሚችለው፣ የሊቢያና የሱማሌ ጉዳይ ነው እንጂ፣ ከፍተኛ ድጋፍ ያገኘው የኤርትራ ውሳኔ ያለ ችግር እንደሚጸድቅ፣ ተስፋ ሰጥተውኛል::*

*አሁን ያለውን ሁኔታ ስንመለከት፣ ይህ አስተያየት ትክክል ነው ማለት እንችላለን:: ሆኖም የፖለቲካ ጉዳይ በተሰጠው ግምት ጸንቶ ይፈጸማል ማለት ስለማይቻል፣ ከኛ በኩል ይኸ ጐደለ የሚባል ነገር እንዳይኖር፣ ማናቸውንም ጥንቃቄና ዝግጅት ማድረግ እንገደዳለን:: ...... ሁለተኛ፣ እርስዎ እንዳሉት የላቲን አሜሪካ አገሮች ዋና ዓላማ፣ ጣልያንን መርዳትና በማናቸውም ጉዳይ ለጣልያን መታዘዝ ስለሆነ፣ ጠላታችን በሚያዘጋጅልን ተንኮል ተባባሪነታቸው የማይቀር ነው:: ..... እኛ አቅማችን የሚፈቅድልን ቢሆን ኖሮ፣ ለመጭው መስከረም ወር፣ የጣልያን መንግሥት ምን ዓይነት ተንኮል እንደአቀደብን በቅድሚያ ማወቅ በጣም ይጠቅመን ነበር:: ነገር ግን የገንዘብና የሰው ኃይል ስለሚያጥረን፣ የጠላታችንን ተንኮል የምንሰማው ዝግጅቱ ሥር ከሰደደ በኋላ ነው:: በዚህ ምክንያት የምናደርገው ጥረት ሁሉ በተከላካይ ቦታ ላይ ብቻ እንድንሆን ይወስነናል:: አሁንም የተቻለንን ያህል መፍጨርጨር ስለሚያስፈልግ፣ ወደ ላቲን አሜሪካ አገሮች ረዥሙን ጉዞ እንዳደርግ የተወሰነው፣ እስካሁን ሲነዛብን የቆየውን የጠላታችንን የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ለመከላከል ይረዳን ይሆናል ተብሎ ነው::*

*...... ከእኔ ጋር አብረውኝ እንዲጓዙ የተፈቀደው፣ ክቡር አቶ ተስፋዬ ተገኝ በፓሪስ የግርማዊነታቸው ሚኒስትር እና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ልጅ እምሩ ዘለቀ ብቻ ስለሆኑ፣ እርስዎ ያሉት ሰው አብሮኝ እንዲጓዝ አልታሰበም:: ቢቻል ገብረመስቀል ክፍለእግዚእ ቢጨመርልኝ ደስ ይለኝ ነበር:: ነገር ግን በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ወጭው ይከብዳል ስለሚባል፣ መሳካቱን እጠራጠራለሁ:: ...... እርስዎ እንደአሳሰቡኝ ሁሉ፣ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ጉዳያችን በጥሩ ይፈጸምልናል ብለን ተስፋ ብናደርግም፣ ባለፈው ጊዜ እንደደረሰው፣ በጣም አስቸጋሪ በሆነው በሱማሌ ምክንያት፣ የምንጠብቀው ሳይወሰን ወይም ሊጓተት እንደሚችል፣ ጸሐፊ ትእዛዝ ባሉበት ለጃንሆይ በስፊው አስረድቻለሁ:: እርስዎም አዲስ አበባ እንደተመለሱ በተጨማሪ ለማስረዳት እንደሚችሉ አምናለሁ::*

*በጣቅላላው ስለገለጹልኝ ቁም ነገር ያለው አስተያየት ከልብ እያመሰገንኩ፣ በየጊዜው ከርስዎ የሚደርሰኝ ምክርና አስተያየት በጣም የሚጠቅመኝ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ልገልጽልዎ እወዳለሁ::*

*ወዳጅዎ አክሊሉ ሀብተወልድ*

አቶ አክሊሉ እና ብላታ ኤፍሬም የተለዋወጧቸው አስተያየቶች በግልጽ የሚያስረዱት፣ መስከረም 20 ቀን 1949 ዓ.ም በሚከፈተው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ፣ የኤርትራ ጉዳይ በቀላሉ ይፈጸማል ብሎ እርግጠኛ መሆን አለመቻሉን ነው:: ከዚህም በቀር ለጉባኤው ዝግጅትም ሆነ ለሚያስፈልገው ሙግት፣ ኢትዮጵያ ብዙ ችግር እንደአለባት መገንዘብ ይቻላል:: የገንዘብና የሰው ኃይል ስለሚያጥራት፣ በጠላት በኩል የሚጠነሰስባትን ተንኮል ዝርዝሩን በቅድሚያ ለማወቅ አልቻለችም:: የጣልያን መንግሥት ግን በቂ አቅም ስላለው፣ ከተባበሩት መንግሥታት አባሎች መካከል፣ አንዳንዶቹን በገንዘብ በመግዛት፣ ሌሎቹን

በፕሮፓጋንዳ በማታለል፣ ብዙ ወገን አፍርቶ የሚፈልገውን ያደርጋል። ኢትዮጵያ በዚህ መልክ ለመወዳደር አትችልም። ከታላቋ ብሪታንያ እና ከአሜሪካ የምታገኘው እርዳታ፣ የአስተያየት ድጋፍ እንጂ፣ የጠላቶቿን ኃይል የምትቋቋምበት መሣሪያ አይደለም። ኃላፊነቱ የሚመለከታቸውና ጉዳዩን በትክክል የሚያውቁት አቶ አክሊሉና ብላታ ኤፍሬም የዛሬውንና የነገውን ሁኔታ እያወጡ በተወያዩበት መንፈስ፣ አዲስ አበባ ያሉት አብዛኞዎቹ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ከሥጋቱም ሆነ ከዝግጅቱ አይካፈሉም ነበር።

በአዲስ አበባ አስተያየት፤ እንግሊዞችን የሚያህል ደጋፊ እያለን የኤርትራ ጉዳይ የሚጠበቀውን ውሳኔ ከማግኘት አይታገድም። ግማሹ የኤርትራ ግዛት ወደ ሱዳን እንዲቀላቀል የእንግሊዞች ጥቅም ስለሆነ፣ በእነሱ ጥረትና ኃይል ለኢትዮጵያ የታሰበውን የደጋውንና የክርስቲያኑን ክፍል በቀላሉ እንረከባለን። ....... ግብፆችና ሌሎቹም የዓረብ አገሮች፣ እነ አቶ አክሊሉ በፓለስቲን የእሥራኤል መንግሥት እንዳይቋቋም የተቃወሙላቸውን ውለታ ቀጥረው፣ በመስከረሙ ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያን እንዲደግፉ ማድረግ ነው። ...... ከጣልያን ጋር ሆነው ኢትዮጵያን የሚያጠቋት የላቲን አሜሪካ አገሮች ናቸው ስለተባለ፣ አቶ አክሊሉ የጃንሆይን መልዕክትና የኒሻን ገጸ በረከቶች ይዘው በመጓዝ፣ ከመሪዎቹ ጋር ተነጋግረው ጠላትነታቸውን በወዳጅነት መለወጥ ነው እያሉ፤ ሥራውን በማቃለል መሀል ሠፋሪዎች እና መኳንንቶች ነን ባዮች የሚሰጡትን ትችት፤ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ብዙ ጊዜ ያስታውሱት ነበር።

እስከ ዛሬ ድረስ እንደታየው፤ የላቲን አሜሪካ አገሮች ኢትዮጵያን ሲተናኮሉ የቆዩት፤ ከጣልያን ጋር በዘርና በሀይማኖት ዝምድና ላይ ተመሥርተው ብቻ ሳይሆን፣ በኤርትራ ጉዳይ የሮማ መንግሥት የሚነዛላቸውን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ እውነት መስሎአቸው እየተቀበሉ ነው። ስለዚህ ይህንን የጠላት ፕሮፓጋንዳ ለመቋቋም፣ አንድ የመልዕክተኞች ቡድን ወደ ላቲን አሜሪካ ተልኮ፤ ኤርትራ እውነተኛው ታሪኳ ምን እንደሆን እና የኢትዮጵያም ጥያቄ በምን ላይ እንደተመሠረተ፤ ለየአገሩ መሪዎችና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች እንዲያስረዳ የንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ሆነ።

<u>የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የበጐ ፈቃድ መልዕክተኞች፣</u>

- አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣
- አቶ ተስፋዬ ተገኝብ በፓሪስ የገርማዊነታቸው ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር፣
- ልጅ እምሩ ዘለቀ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ሹም፣

በሐምሌ 1949 ዓ.ም በመገናኛዎችና በአየር ትራንስፖርት በኩል በነበረው ከፍተኛ ችግር እየተሰቃዩ፣ አምስቱን ዋና ዋና የተባሉት የላቲን አሜሪካ አገሮች ለመጐብኘት ረዥሙን ጉዞ ጀመሩ።

የአክሊሉ ሚሲዮን የሚጐበኛቸው ብራዚል፣ አርጀንቲና፣ ቺሊ፣ ቬንዙዌላ፣ ሜክሲኮ፤ በጠቅላላ አምስት አገሮች ብቻ እንዲሆኑ የተወሰነው፣ 1ኛ/ በመላው የላቲን አሜሪካ አገሮች የበጐ ፈቃድ መልዕክተኞች ለመላክ፣ በወጪም ሆነ በሰው

ኃይል ረገድ የኢትዮጵያ አቅም ስለማይፈቅድ፤ 2ኛ/ ከላቲን አሜሪካ አገሮች ውስጥ ዋና ዋና ቀንደኞቹ፤ እነዚህ አምስቱ ስለሆኑ፤ እነሱን አስረድቶ ማሳመን ከተቻለ፣ ሌሎቹ የእነዚህን የአምስቱን አገሮች ምክር ይከተላሉ ተብሎ ተጠንቶ ነው:: ከነዚህ ከአምስቱ አገሮች መካከል በአርጀንቲና የነገሠው የፋሽስቱ የፔሮን መንግሥት፤ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መልዕክተኞች አልቀበልም ስለአለ፣ የተጐበኙት አራት አገሮች ብቻ ናቸው::

በኤርትራ ጉዳይ፤ ከጣልያን የሚነዛውን መሠረተቢስ ፕሮፓጋንዳ ለማጋለጥና እውነተኛውን ታሪክ ለማስረዳት፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ረዥሙን ጉዞ ሲጀምሩ፤ ልክ በዚያኑ ጊዜ፤ በሴኔት ምክትል ፕሬዚዳንት በሳልቫቶሬ አልዲሲዎ (SALVATORE ALSDISIO) እና በውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር በጁሴፔ ብሩዛስካ፣ (GIUSEPPE BRUSASCA) የሚመራ አንድ ትልቅ <u>የጣልያን መንግሥት የመልዕክተኞች ቡድን መላውን የላቲን አሜሪካ አገሮች ለመጐብኘት በልዩ አውሮፕላን ከሮማ ተነሣ፡፡</u> የዚህ የሮማ መንግሥት ሚሲዮን ዋና ዓላማ፤ በመጀመሪያ ደረጃ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልዕክተኞች፣ የሚያደርጉትን ጉዞና ያቀዱትን ፕሮግራም በቅርብ እየተከታተለ፣ እነሱ ጉብኝታቸውን ጨርሰው አገሩን ሲለቁ፣ እሱ እየተተካ፣ በኢትዮጵያ በኩል የተገነባውን ዲፕሎማሲ ማፍረስ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፤ ለቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶች የጣልያን መንግሥት አዲስ የቀየሰውን ፖሊሲ በማስረዳት፣ ለመስከረሙ ቀጠሮ፣ ሀያ አንዱን የላቲን አሜሪካ መንግሥታቶችን ማዘጋጀት ነበር::

በዚያን ዘመን አገራችን ኢትዮጵያ፣ በአንዳቸውም የላቲን አሜሪካ አገሮች ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ስለሌላት፣ ጣልያን የሚሠራውን ተንኮል በትክክሉ ለማወቅ አልቻለችም:: ጣልያን ግን በመላው ላቲኖች ዘንድ የተሟላ መገናኛ ስለዘረጋችና ብዙም ወገን ስለአላት፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በዚህ ጉዞው ምን ዓይነት አቀባበል እንደተደረገለት፣ ከማን ባለሥልጣን ጋር እንደተነጋገረ፣ ምን ዓይነት ሀሳብ እንዳቀረበና፣ ምን መልስ ተሰጥቶት እንደተሸኘ፣ የነ ጁሴፔ ብሩዛስካ ሚሽን ወዲያውኑ ያውቀው ስለነበረ፣ አቶ አክሊሉ የደከሙበትን አፍራሽ ዘዴ ለመፍጠር ችግር አልነበረበትም::

የደቡብ አሜሪካ አገሮች ከጣልያን ጋር በዘርና በሀይማኖት ባላቸው ግንኙነት መሠረት፤ በዚያን ጊዜ የፖለቲካውም ጉዳይ በይበልጥ ስለአስተባበራቸው፣ የሮማ መንግሥት እየፈተፈተ የሚያጉርሳቸውን ፕሮፓጋንዳ ከመቀበል በስተቀር፤ ከሌላ ምንጭ የሚሰሙት፣ ወይም ለማረጋገጥ የሚሞክሩት ምንም ነገር እንዳልነበረ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ለመገንዘብ ችለዋል:: ለምሣሌ ያህል አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ከብራዚል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ሲነጋገሩ ያጋጠማቸው ክርክር ሊጠቀስ የሚገባ ነው::

የብራዚሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ፈርናንዴዝ፣ በ1949 ዓ.ም የሰባ ዓመት (70) ዕድሜ ነበረው:: ካቶ አክሊሉ ጋር የሚተዋወቁት ከ13 ዓመታት በፊት በ1936 ዓ.ም በዤኔቭ የመንግሥታት ማህበር ጉባኤ ላይ ነበር:: ከዚያም በኋላ በ1945 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከተቋቋመ ጀምሮ፤ በየስብሰባው በመገናኘት ወዳጅነታቸውን የቀጠሉ በመሆናቸው፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወደ ብራዚል የተጓዙት የሚስተር ፈርናንዴዝን ድጋፍ አገኛለሁ በሚል ተስፋ ነው::

የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ሪዮ ደዣንየሮ (RIO DE JANEIRO) ሲደርሱ የተደረገላቸው አቀባበል የሞቀ ቢሆንም፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ፌርናንዴዝ በጣልያን ፕሮፓጋንዳ የተመሰጠ ስለሆነ፣ አስተያየቱን ለማቃናት ቀላል አልነበረም:: « ..... ኤርትራ ለኢትዮጵያ ካልተሰጠች ብላችሁ ስትሟገቱ፤ ከአያት ከቅድመ አያት ጀምሮ እንደ አገራቸው ቆጥረው የሚኖሩት፣ ሶስት መቶ ሺህ ጣልያኖች የት ይድረሱ ነው የምትሉት? ..... » ሲል የብራዚል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጥያቄውን አቀረበ:: አቶ አክሊሉ ሲመልሱ፣ « ..... በኤርትራ የሚኖሩት ጣልያኖች ሶስት መቶ ሺህ አለመሆናቸውን እና ቢፈ ቢቆጠሩ ከሃያ ሺህ አለመብለጣቸውን እኔ ስናገር ልታምነኝ አትችልም:: ነገር ግን በሚኒስቴርህ ውስጥ በጣልያንኛ የታተመ ኢንሳይክሎፔዲያ ቢኖርና፣ አብረን በኤርትራ የሚኖሩትን ጣልያኖች ቁጥር ብንመለከት ደስ ይለኝ ነበር ...... » አሉት:: ፌርናንዴዝ ወዲያውኑ ከመጻሕፍት ቤቱ የጣልያን ኢንሳይክሎፔዲያ አስመጥቶ ከአቶ አክሊሉ ጋር አብረው ገለጡት:: ይህ የታሪክ መዝገብ የታተመው በ1935 ዓ.ም ነው:: ሆኖም በ1934 ዓ.ም በኤርትራ ነዋሪ የሆኑት የጣልያን ዜጎች ከአንድ ሺህ (1000) የማይበልጡ መሆናቸውን እና፣ በሞቃዲሾ ሱማሌ ያሉት አምስት መቶ አለመሙላታቸውን ሲያመለክት፣ የብራዚሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የመገረም መንፈስ አሳየ:: የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪም፣ የጣልያን መንግሥት በየጊዜው መዋሸት የማይታክተው መሆኑን በማስረዳት፣ አንዳንድ ምሳሌዎች ጠቀሱለት:: « ...... ባለፈው ሶስት ወር፣ በትክክለኛው ቀን ሰኞ ሚያዝያ 11 ቀን 1949 ዓ.ም የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮምት ካርሎ ስፎርዛ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ፣ በኤርትራ የሚኖሩት የጣልያን ተወላጆች በብዙ በመቶ ሺህ ናቸው ብሎ ሲናገር፣ እኔ ተነስቼ ከሃያ ሺህ እንደማይበልጡ አስረድቼ ነበር:: ታስታውሳለህ ወይ ? ብለው ጠየቁት:: የስባ ዓመቱ አዛውንት ትዝ የሚለው፣ በኤርትራ የሠፈሩት ጣልያኖች ሶስት መቶ ሺህ መሆናቸውን ከሮማ መንግሥት የተዘጋጀውን ዶክመንት ደጋግሞ ማንበቡን ብቻ ነበር:: ከእንግዲህ ወዲህ ይህን የመሰለውን ስህተት የብራዚል መንግሥት እንደማይቀበል ከገለጸ በኋላ፣ ስለ ኢትዮጵያ መልዕክተኞች ክብር ባደረገው ታላቅ የምሳ ግብዣ ላይ፤ የአድዋን ታሪክ በመጥቀስ የተናገረው ቃል የኢትዮጵያን ጥያቄ የሚደግፍ መስሎ ታየ:: « .... የአድዋ ጦርነት ጊዜ የሀያ ዓመት ወጣት ተማሪ ነበርኩ:: ጦርነቱ የሚካሄደው በጣልያን ኮሎኒያሊስትና በኢትዮጵያ ነፃ መንግሥት መካከል ሲሆን፣ ተማሪዎች በሁለት ወገን ተከፍለን እንጣላ ነበር:: <u>እኔ የምኒልክ አድናቂና ደጋፊ ነበርኩ</u> ....... » አለ::

...... የብራዚል የካቢኔ ሚኒስትሮችና የውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎች፣ (ከጣልያን በስተቀር) በተካፈሉበት የምሣ ግብዣ ላይ፣ ሚስተር ፌርናንዴዝ ይህንን ንግግር ያደረገው፤ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተላከለትን ኒሻን ከአንገቱ እስከ ወገቡ አንዠርግጎ ነው:: ይህም ኒሻን አጋጣሚ ሆኖ <u>የዳግማዊ ምኒልክ ታላቅ ኮርዶን</u> ነበር:: ከግብዣው ፍጻሜ በኋላ፣ የሁለቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የመጨረሻውን ውይይት ሲያደርጉ፣ ሚስተር ፌርናንዴዝ ለአቶ አክሊሉ የገለጹላቸው አስተያየት፤ « .... እኛ ላቲኖች የቅኝ ገዥዎችን አስተዳደር የቀመስን ስለሆነ፣ ለሕዝቦች መብትና ለትክክለኛ ፍርድ እንዋጋለን:: ..... አሁን እንደተረዳነው፣ በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያ ጥያቄ፣ መሠረታዊ እምነታችንን የሚመለከት ስለሆነ እንደግፋለን ...... » የሚል ነበር::

ሚስተር ፌርናንዴዝ የሚነገርለት ዝና፣ በቃሉ የማይረጋ፣ አንዱን ከአንዱ የሚያምታታ ከመሆኑም በላይ፤ ለጣልያን የጠለቀ ወዳጅነት አለው እየተባለ ነው::



የኢትዮጵያና የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች አክሊሉ ሀብተወልድና ሮበርት ሹማን፡

(ፓሪስ ሐምሌ 1949)
(ፎቶ U.N)

በእርግጥም የብራዚሉ የዲፕሎማሲ መሪ፣ ለጣልያን መንግሥት የነበረውን ተቆርቋሪነት የሚያሳይ አሁን በቅርቡ (በ1990 ዓ.ም) የተገለጠ አንድ ዶክመንት ተገኝቷል:: የጉዳዩ መነሻ፤ ጣልያን ትሪፖሊታንያን በሞግዚትነት ስለሚያስተዳድርበት ሁኔታ ነው:: ለዚህ ጉዳይ በ1949 ዓ.ም በሶስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ክርክሩ በሚካሄድበት ጊዜ፣ ጣልያን ትሪፖሊታንያን ለማግኘት በጣም ስለፈለገች፣ <u>ለአስተዳደሩ የሕዝብ ወኪሎች ተመርጠው የሚመክሩበት ፓርለማ አቋማለሁ</u> የሚል ሀሳብ አቅርባ ነበር:: በዚህ ጊዜ የብራዚል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የጣልያንን አምባሳደር ጠርቶ፣ « .... ይህ እናቋቁማለን የምትሉት ፓርላማ፤ የጣልያንን የአስተዳደር ሥልጣን የሚቀንስ እንዳይሆንባችሁ መጠንቀቅ አለባችሁ .... » የሚል ምክር ሰጥቶ ነበር:: የጣልያን መንግሥት ለቀረበለት ለዚህ ቃል የሆነ የወዳጅነት ምክር፤ ከፍ ያለ አድናቆቱንና ምሥጋናውን ለሚስተር ፌርናንዴዝ መግለጹን፤ ዛሬ በሮማ ከፋርኔዚና የተገለጠው ዶክመንት ያስረዳል:: በዚሁ ዓይነት በሐምሌ 1949 ዓ.ም የጣልያን መንግሥት ከፍተኛ ሚሽን ከኢትዮጵያ መልእክተኞች ቀጥሎ ሪዮ ዲ.ዠንየሮ ሲገባ፣ ሚስተር ፌርናንዴዝ ለአቶ አክሊሉ የሰጠውን ተስፋ ወዲያውኑ ወርውሮ፣ ከጣልያን ጋር እንደተሰለፈ፣ የደጋስፐሪ ካቢኔ የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር ጁሴፔ ብሩዛስካ በራፖሩ ገልጦታል::

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፤ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት አቅሙ በሚፈቅደው መጠን፤ የኢትዮጵያ የበጐ ፈቃድ መልዕክተኞች በላቲን አሜሪካ የጐበኟቸው አገሮች ብራዚልና ቺሊ፣ ቬንዙዌላና ሜክሲኮ ብቻ ናቸው:: የነዚሁም መንግሥታት መሪዎችና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፤ ከኢትዮጵያ የቀረበላቸውን ሀሳብ አዳምጠው በኤርትራ ጉዳይ ድጋፍ ለመስጠት መስማማታቸውን ስለገለጹላቸው፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ወደ አዲስ አበባ የተመለሱት በጉዞአቸው ውጤት ተስፋ አሳድረው ነው:: እንግዲህ ይህ የተሰጣቸው ተስፋ፣ እስከ መስከረም 20 ቀን 1949 ዓ.ም ድረስ ጸንቶ ቆይቷል ? ወይስ ተለውጧል ? ትክክለኛውን ሁኔታ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የተደረጉት ክርክሮችና በመጨረሻም የተሰጠው ውሳኔ አብራርቶ ይነግረናል::

ለመስከረሙ ቀጠሮ የኢትዮጵያ ዝግጅት በላቲን አሜሪካ አገሮች፣ የበጐ ፈቃድ ሚሲዮን በመላክ ብቻ አልተወሰነም:: አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ከዚህ ከረዥሙ ጉዞአቸው ሲመለሱ፤

1ኛ/ የላቲን አሜሪካ አገሮች ጠላትነታቸው በጣም የሚጐዳን ስለሆነ፤ ይህንን ለመከላከል እጅግ ከፍ ባለ ፍጥነት በብራዚል፣ በቬንዙዌላና በሜክሲኮ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን እንዲከፈት፣

2ኛ/ ከመስከረሙ ቀጠሮ በፊት፣ በተቻለ ፍጥነት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለመላው የተባበሩት መንግሥታት አባል አገር መሪዎች፤ በኤርትራ ጉዳይ ለኢትዮጵያ ድጋፍ እንዲሰጡ ልዩ መልዕክት እንዲያስተላልፉ፣

3ኛ/ የጃንሆይን መልዕክት ለየመንግሥታቱ መሪዎች የሚያቀርቡ፤ ከአዲስ አበባ ልዩ መልዕክተኞች ለመሾም የሰውም ሆነ የገንዘብ ችግር ስለአለ፤ አሁን በውጭ አገር ያሉት የኢትዮጵያ አምባሳደሮችና ሚኒስትሮች፣ ለየተመደቡበትና በአካባቢያቸው ለሚገኙት አገሮች

መልዕክቱን እንዲያደርሱ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ያቀረቡት ሀሳብ እንዲፈጸም ንጉሠ ነገሥቱ አዘዙ::

በዚያን ዘመን በልዩ ልዩ የውጭ አገር መንግሥታቶች ዘንድ የተወከሉት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሮችና ጉዳይ ፈጻሚዎች፣ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሲነታቸውን፣ ከዚህም በላይ የኢትዮጵያን ታሪክና ባሕል በጨዋነት የሚያስከብሩ መሆናቸው የታወቀ ነው:: ነገር ግን አብዛኛዎቹ የሚሲዮን መሪዎች፣ የዲፕሎማሲው ተግባር የሚጠይቀው ጥያና ስልት ስለሚያጥራቸው፣ ስለ ኢትዮጵያ የሚታሰበውን ለመከታተል፣ እንደየጉዳዩ ሁኔታ የኢትዮጵያን አቋም አብራርቶ ለማስረዳት፣ የተዛነፈውን አስተያየት ለማቃናት፣ ያለውን መልካም ስሜትና ግምት እያዳበሩ፣ ለአገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅም ለማስገኘት ይቸገሩ ነበር:: በዚህ ምክንያት፣ ኢትዮጵያ በኢንተርናሽናል የዲፕሎማሲ መስክ ላይ በጣም የሚያስፈልጋትን ትክክለኛ መረጃ ስለማታገኝ ጉዳቷ ቀላል አልነበረም:: አብዛኛዎቹም የሚሲዮን መሪዎች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ችላ እያሉ፣ በቀጥታ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚያቀርቡት ሪፖርት ቁም ነገሩን እየሳተ፣ በወግ ሥርዓት ላይ የሚመረከዝ ብቻ እንደነበረ በግልጽ ያሳያል::

በዚህ በኤርትራ ጉዳይ፣ ጃንሆይ ለመላው የተባበሩት መንግሥታት መሪዎች የላኩትን መልዕክት፣ ሁለት የኢትዮጵያ ሚሲዮን ኃላፊዎች ለየተወከሉበት አገር መሪዎች በምን አኳኋን እንደአደረሱ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ የጻፉት ሪፖርር እንደ ምሣሌ ተወስዶ ቢጠቀስ፣ የጊዜውን የዲፕሎማሲ ሥራ አፈጻጸም የሚያሳይ ትክክለኛ ስዕል ሊሆን ይችላል:: እነዚህ ሁለት የሚሲዮን መሪዎች እነማን እንደነበሩና፣ የተወከሉብትም አገር የት መሆኑ ስለማይገለጽ፣ ሪፖርሮቹ <u>በቁጥር 1</u> እና <u>በቁጥር 2</u> ተለይተዋል::

<u>ከቁጥር 1. የተወሰደ፤</u>

« ...... ግርማዊነትዎ እንዳደርስ ያዘዙኝን ታላቁን ንጉሣዊ መልዕክትዎን ይዤ ለ ........ አገር ....... መሪ ነሐሴ 20 ቀን 1941 ዓ.ም (በአውሮፓ አቆጣጠር መስከረም 3 ቀን 1949) በአፊሴል በማቅረብ በሰፊው ተነጋግሬአለሁ::

....... በግርማዊነትዎ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ የተሰጠኝን የባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትርነቴን የክብር ልብስ ለብሼ፣ በአውቶሞቢሌ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አስደርጌ፣ አንደኛውንና ሁለተኛውን የሌጋሲዮኑ ፀሐፊዎቼን አስከትዬ፣ በተሰጠኝ ቀን ቀጠሮና ሰዓት ከቤተመንግሥቱ ስደርስ፣ የግርማዊነትዎ እንደራሴ በመባል የተደረገልኝ ታላቅ አቀባበል፣ ይህ ነው የማይባል ሥርዓትና ክብር የሚታይበት ነበር::

....... እስከዚህ የደረሰ እጅግ የተከበረ አቀባበል የተደረገልኝ፣ ዓለም በሚያደንቀው በግርማዊነትዎ ታላቅነት ስለሆነ፣ ይህንን ከፍተኛ ዕድል ለኢትዮጵያ የሰጠውን ቸሩ ፈጣሪያችንን ሳመሰግን ሰንብቻለሁ::

....... የግርማዊነትዎ ልዩ መልዕክተኛ ሆኜ የቀረብኩላቸው የ ........ አገር ...... መሪ በታላቅ ክብር በተቀበሉኝ ጊዜ፣ ግርማዊነትዎ ለአገራችን ለኢትዮጵያ ሌት ተቀን ስለሚደርጉት ጥረትና፣ እንዲሁም <u>ግርማዊነትዎ ስለጠየቀው ዋና ነገር ደህና አድርጌ ሳስረዳቸው ከፍ ባለ ፈገግታ አጸምጠውኛል::</u> ........ እኝህ የተከበሩ

ታላቅ መሪ የግርማዊነትዎን ልዩ መልዕክተኛ ይህን በመሰለ በሚያስደስት አኳኋን በመቀበላቸውና፣ በደስታ መንፈስ በማነጋገራቸው፣ ከግርማዊነትዎ ምሥጋና ቢጻፍላቸው፣ ለአገራችን ከፍ ያለ ጥቅም መሆኑን መሬት ስሜ በታላቅ ትህትና አሳስባለሁ:: ........ »

<u>ከቁጥር 2 የተወሰደ፣</u>

« ........ ከግርማዊ ጃንሆይ የተሰጠኝን ከፍተኛ ትእዛዝ መሬት ስሜ ከተቀበልኩ በኋላ፣ ለአገሩ መሪ ..... ለማስረከብ ቀጠሮ ጠይቄ ለነሐሴ 27 ቀን ከቀኑ በአምስት ሰዓት ቀጠሮ ተሰጥቶኝ ከቤተመንግሥቱ ልደርስ፤ የግቢው ዋና አዛዥና የፕሮቶኮሉ ሹም ተቀብለውኝ፣ በነጭ ሐር ጨርቅ የተሸለሙ ወንበሮች በተደረደሩት የማረፊያ ሳሎን አዳራሽ፤ ጥቂት ዕረፍት ካደረግኩ በኋላ፣ በዋናው የእልፍኝ አስከልካዩና በፕሮቶኮሉ ሹም አማካይነት ........ መሪው ወደ አሉበት ትላቁ አዳራሽ ገብቼ ወንበር ከተሰጠኝ በኋላ፣ እሳቸውም (መሪው) በፍቅርና በወዳጅነት አነጋገር የግርማዊነትዎን ጤንነት ሲጠይቁኝ፤ ዝቅ ብዬ በታላቅ ትህትና ደህንነትዎን ከገለጽኩላቸው በኋላ፣ የጃንሆይን ልዩ መልዕክት በእጃቸው ሰጥቼ፣ በታላቅ ደስታ ከተቀበሉ በኋላ፣ እጅግ ደስ የሚያሰኝ የሻይ ግብዣ ተደረገልኝ::

ባርያዎ ከዚህ ቀደም እንዳመለከትኩዎ፣ እኚህ ደግ መሪ ለግርማዊነትዎ ያላቸው ፍቅርና አድናቆት ከፍ ያለ ሲሆን፣ ጠቅላይ ሚኒስትራቸው ግን የተማረ ነው ቢባልም፣ ብዙ ጨዋነት ስለሚጎድለው፤ ግርማዊነትዎ በሚደከምበት ስለ ኤርትራ ወደ እናት አገር መመለስ ጉዳይ፤ ምን እንደሚያስብ አፍ አውጥቶ አልተናገረም:: ሆኖም ከአኳኋኑ እንደተረዳሁት ኤርትራ ወደ እናቷ ከመጣች፣ ሱማሌም ከተጨመረች፤ ገናናው መንግሥትዎ ኃይለኛ ይሆንብናል ብሎ የሚጨነቅ ሳይሆን አይቀርም:: ከአንዳንድ የቤተመንግሥቱ የቅርብ ሰዎች እንደሰማሁት፣ ይኸ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ በአገሩም ውስጥ አንዳንድ የሚሠራው ተንኮል እየተደረሰበት ስለሆነ፣ ከእንግዲህ <u>ቢበዛ አንድ ዓመት ቢቆይ ነው እንጂ፤</u> መሻሩ የማይቀር ነው:: የአምላክ ፈቃዱ ሆኖ <u>እሱ ሲነቀል</u> ለኢትዮጵያ ግለፊያ ነገር ይሆናል ብዬ አሰባለሁ::

ረዥም ዕድሜና ጤና ለግርማዊነትዎ እንዲሰጥልኝ ፈጣሪዬን እየለመንኩ፣ ከዙፋንዎ ሥር ዝቅ ብዬ መሬት እስማለሁ:: ....... »

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁለቱ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን መሪዎች ባቀረቧቸው ራፖሮች፤ ለኤርትራ ጉዳይ ድጋፍ ለማግኘት ጃንሆይ ለየመንግሥታቱ መሪዎች ለላኩት ልዩ መልዕክት፤ ምን መልስ እንደተሰጠ አይናገሩም:: ይልቁንም በቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው ራፖር እንደሚያመለክተው፣ ጃንሆይ ለኤርትራ ጉዳይ የጠየቁትን ድጋፍ ብርቱ ምሥጢር አድርጎ በመያዝ « ...... <u>ግርማዊነትዎ ስለጠየቀው ዋና ነገር በሰፊው አስረድቻለሁ</u> ....... » በሚል በተሰወረ ቃል የመልዕክቱ ውጤት ተገልጿል:: በቁጥር 2 የታየው ራፖር ደግሞ የበለጠ የሚያስገርም ሳይሆን አልቀረም:: ጃንሆይ ስለ ኤርትራ ጉዳይ የየመሪዎቹን ድጋፍ የጠየቁት፤ ከሶስት ሳምንታት በኋላ ለሚከፈተው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ሲሆን፣ ባለሙሉ ሥልጣን መልዕክተኛው ያቀረቡት ራፖር፣ <u>አሁን ያለው ጠቅላይ ሚኒስትር ከአንድ</u>

ዓመት በኋላ ይሻራል ተብሎ ስለሚወራ፣ እሱ ሲነቀል በዚያን ጊዜ ሙሉ እርዳታ እናገኛለን በሚል ተስፋ የተዘጋ ነው።

በጠቅላላ አነጋገር ኢትዮጵያን በልዩ ልዩ አገሮች የወከሏት የአብዛኞዎቹ ዲፕሎማቶች የተግባር አፈጻጸም፡ ከዚህ በላይ በቀረበው ምሣሌ ዓይነት ነው ቢባልም፣ ቁጥራቸው አነስተኛ ይሁን እንጂ፡ ጊዜው የጠየቀውን የዲፕሎማሲ ስልት የተከተሉ አንዳንድ ታላላቅ የሚሲዮን መሪዎች እንደነበሩ የታወቀ ነው። በ1949 ዓ.ም በአምባሳደርነትና በሚኒስትርነት ደረጃ፣ በዋና ዋና ሥፍራዎች ከተመደቡት መካከል፣ ለምሣሌ ያህል በፓሪስ አቶ ተስፋዬ ተገኝ፣ በለንደን አቶ አበበ ረታ፣ በሕንድ አቶ አማኑኤል አብርሃም ያበረከቱት የዲፕሎማሲ ተግባር የሚዘነጋ አይደለም።

በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ፡ ፍርድ ለሚጠብቀው የኤርትራ ጉዳይ፡ ከሐምሌ እስከ መስከረም አጋማሽ 1949 ዓ.ም ድረስ፡ በኢትዮጵያ በኩል የተደረገው ዝግጅት ይህን ያህል ጠላትን ተቋቁሞ ድል ለመምታት የሚያስችል አልነበረም።

-- ከሶስቱ የምዕራብ ኃያላን መንግሥታት ውስጥ ምንም እንኳን በፈረንሣይ እርዳታ ሙሉ በሙሉ መተማመን ባይቻልም፣ የታላቋ ብሪታንያ እና የዩናይትድ ስቴትስ ድጋፍ እንደሚቀጥል ታውቋል።

-- የኢትዮጵያ የበጐ ፈቃድ መልዕክተኞች የጐበኟቸው፡ ብዙ ተከታዮች እሏቸው የተባሉት እራቱ የላቲን አሜሪካ አገሮች የኢትዮጵያን ጥያቄ ለመደገፍ የሰጡት ቃል ይፈጸማል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል።

-- ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለመላው የተባበሩት መንግሥታት መሪዎች ያስተላለፉት መልዕክት፡ ለሁሉም ደርሶ የድጋፍ መልስ የሰጡት መሪዎች ቁጥር አሥራ አምስት ደርሷል።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ከሙሉ ሥልጣን ጋር የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ሆነው፣ ከአዲስ አበባ ወደ ኒውዮርክ ከመነሣታቸው በፊት፣ በገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ንጉሣዊ ስብሰባ ተደርጐ የተነገራቸው፡ ኤርትራን ቢቻል በሙሉ፣ ሳይሆን በከፊሉ አስፈርደህ ይዘህልን ተመለስ፡ የሚል የጠነከረ አደራና ትእዛዝ የተጣሐደበት መምሪያ ነበር።

እዚህ ላይ ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን፡ በሐምሌ ወር ላቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በገለጹት አስተያየት፣ « ....... የመስከረሙን ቀጠሮ ጃንሆይ እርግጠኛ የሆነ ተስፋ አድርገው እንዳይጠብቁ ማዘጋጀት ያስፈልጋል .... » ማለታቸው ይታወሳል። የመስከረሙ ውጤት ቀላል እንደማይሆን፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ጋር ሆነው ለንጉሠ ነገሥቱ በሰፊው ማስረዳታቸው አልቀረም ነበር። ነገር ግን በአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት የእንግሊዝ፣ የአሜሪካና የፈረንሣይ አምባሳደሮች፣ ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት እየመጡ፣ በኤርትራ ጉዳይ የየመንግሥታቸው የድጋፍ አቋም የጸና መሆኑን እና፡ በአብዛኞዎቹም አገሮች ዘንድ፡ ምንም ዓይነት ችግር እንደማይኖር ስለሚነግሯቸው፣ ንጉሠ ነገሥቱ ባሳደሩት ትልቅ ተስፋ ላይ፣ የነ አክሊሉን ጥርጣሬ ማስገባት አልፈለጉም። ይልቁንም የእነዚህ የሶስቱ ኃያላን መንግሥታቶች የተጨበጠ ድጋፍ ስለአለ፡ የጣልያን ተንኮል አደናቃፊ ሊሆን የማይችል መስሎ ታያቸው። በገነተ ልዑል

ቤተመንግሥት በተደረገው ታላቅ ስብሰባ፣ ተካፋይ የሆኑትም መሣፍንቶችና መኳንንቶች፣ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ጠንክረው እንዲከራከሩና አሸናፊ ሆነው እንዲመለሱ አደራ ብለዋቸዋል:: ሁኔታው እንደሚያስረዳው የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ከአዲስ አበባ ተነስተው ረዥሙን ጉዞ ወደ ኒውዮርክ የቀጠሉት፣ እጅግ አሳሳቢና እንቅልፍ የሚነሣ፣ ኃላፊነት ተሸክመው ነው::

በተባበሩት መንግሥታት ሸንጐ ላይ፣ ምንም እንኳን ጣልያን ወዳጆቿን እነ አርጀንቲናን አሰልፋ ጦርነት እንደምትገጥማቸው የሚጠበቁት ቢሆንም፣ የጠላት ሴራ በምን ዘዴ ተሰናድቶ እንደሚገጥማቸው፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መረጃ የላቸውም:: ከሌሎቹም አባል መንግሥታት መካከል እነማን ብድግ ብለው፣ የጣልያን ደጋፊና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ እንደሚሆኑ፣ በትክክል የሚያውቁት ዝርዝር አልነበረም:: ደጋፊዎቻችን ሆነው ባለፈው ግንቦት ወር ድምፅ ከሰጡን አገሮች መካከል፣ እነማን ሀሳባቸውን ለውጠው ወደ ጣልያን እንደአጋደሉ አላወቁም:: በጠቅላላው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልዕክተኞች፣ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ተደራጅቶ የጠበቃቸው የጠላት ተንኮል፣ ከአሰቡትና ከጠረጠሩት በላይ ነው::

## የጣልያን ሤራ

ግንቦት 6 ቀን 1949 ዓ.ም ሎንዶን ላይ የተፈረመው የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት፣ ሞቶ መቀበሩን የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንደገለጸው ሁሉ፣ ጣልያኖችም ይህ ስምምነት ከተቀበረበት ለምን ጊዜውም እንደገና ነፍስ እንዲዘራ አንፈልግም ብለው፣ በመስከረም ለሚከፈተው ለአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ፣ ያልተጠበቀ አዲስ አቋም ይዘው ለመቅረብ ወሰኑ::

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ጸሐፊ በቪቶሪዮ ዞፒ (VITTORIO ZOPI) ሰብሳቢነት፣ በፋሽስት ዘመን የሠለጠኑ ዲፕሎማቶች፣ እነ አልቤርቶ ታርኪያኒ አጥንተው ያቀረቧቸውና፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዲጋስፐሪ ጸድቀው በሥራ ላይ እንዲውሉ የተሞከሩት፣ የጣልያን ዋና ዋና የተንኮል ፕሮግራሞች የሚከተሉት ነበሩ::

...... በጣልያን ዲፕሎማቶች አስተያየት፣ የሰባ ሰባቱ (77) ዓመት ሽማግሌ ካርሎ ስፎርሳ፣ ሎንዶን ላይ ከታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ስለኮሎኒዎቹ የወደፊት መፍትሔ ያደረገው ስምምነት ከፍ ያለ ጣጣ አስከትሏል::

1. ከኤርትራ ግዛት አብዛኛዎቹ አውራጃዎች ለኢትዮጵያ እንዲሰጡ ካርሎ ስፎርሳ ያደረገው ስምምነት፣ የጣልያንን ጥቅም ጉድቷል:: በዚህ ምክንያት የቀኞቹም ሆኑ የግራዎቹ የፖለቲካ መሪዎች፣ የዲጋስፐሪን መንግሥት ክፉኛ አውግዘዋል::

2. በጣልያን ላይ እምነት ያሳደሩትና ከጣልያንም ጋር በሕብረት ለመኖር፣ ጽኑ ፍላጐት ያላቸው አብዛኛዎቹ ኤርትራውያኖች፣ በዚህ አገራቸውን ለኢትዮጵያና ለሱዳን በሚከፋፍለው በቤቨን ስፎርሳ ስምምነት ጥልቅ ሀዘናቸውን

አስምተዋል:: በተለይ የደጋውና የምሥራቅ አውራጃዎች ለኢትዮጵያ እንዲሰጡ የተደረገው ስምምነት፡ መላውን የኤርትራ ሕዝብ አስቆጥቷል:: የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር መሆንን ጨርሶ አይፈልግም::

3. አሁን ግን፡ አጋጣሚው ረድቶን በሶስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ የቤቨን ስፎርሳ መፍትሔ ባለመጽደቁ፣ የወደፊቱን የኤርትራን ሕዝብ ዕድል የሚያቃና እና፣ ለጣልያንም ተገቢ የሆነ ሚና ለመጫወት የሚያስችላት ጥሩ መንገድ ከፍቷል::

4. ስለዚህ፡ ለቅኝ ግዛቶቻችን መፍትሔ እንዲሆኑ ባለፈው ጊዜ የደከምንባቸውን መንገዶች ለውጠን፣ በአዲሲቷ የጣልያን ሬፑብሊክ ስም፡ በአዲስ መንፈስና በአዲስ ሀሳብ፣ አዲስ አቋምና አዲስ ፕላን አዘጋጅተን፣ ለአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ እንዲቀርብ ማድረግ አለብን::

5. ይህም በመጪው መስከረም በሚደረገው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ የሚቀርበው ሀሳብ፣ « .... ኤርትራና ሊቢያ በቀጥታ ነፃነታቸውን እንዲቀበሉ፣ ሱማሌ ለተወሰነ ጊዜ በጣልያን ሞግዚትነት ከተዳደረች በኋላ ነፃነቷ እንዲሰጣት ... » የሚል መሠረታዊ አቋም የያዘ ከሆነ፣ ሁለት ሶስተኛውን የተባበሩት መንግሥታት አባሎች የድጋፍ ድምጽ ለማግኘትና ለመጽደቅ ይችላል:: ይህንንም ሀሳብ አብስለን ለጉባኤው የምናቀርበው፡ ወዳጆቻችንን የላቲን አሜሪካ አገሮችን ቀደም ብለን በሚገባ አሰናድተን ነው:: ኤርትራ ነፃ መንግሥት ሆና እንድትቆም በማድረግ፣ ከኢትዮጵያ ወረራ እናድናታለን:: በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት በኤርትራ ያሉት ዜጎቻችንም በሠላምና በነፃነት መኖር ይችላሉ::

6. በሊቢያ፡ ለትሪፖሊታንያም ሆነ ለሲረናይክ ነፃነት መስጠት ያስፈልጋል ስንል፡ ዓረቦችና የእስላም አገሮች፣ ከቶ የማይጠብቁት የደስታ ዱብ እዳ ስለሚሆንባቸው፣ ወዲያው ጠላትነታቸውን ሠርዘው፡ ወዳጆቻችን ሆነው ከእኛ ጋር ይቆማሉ::

7. በሱማሊም ጉዳይ የሞግዚት አስተዳዳሪነቱ ለእኛ እንዲሰጥ ሀሳቡ በሚቀርብበት ጊዜ፡ የዓረብና የእስላም አገሮች ድጋፍ በቀጥታ ይጐርፍልናል:: በሚቀርብበት ጊዜ፡ የዓረብና የእስላም አገሮች ድጋፍ በቀጥታ ይጐርፍልናል:: ኤርትራም በቤቨን ስፎርሳ ስምምነት መሠረት ግማሹ ኢትዮጵያ፣ ሌላው ወደ ሱዳን ይከፋፈላል ከሚለው ሀሳብ ይልቅ፣ ኤርትራ አንድነቷ ተጠብቆ ነፃነቷን እንድታገኝ የሚቀርበው ሀሳብ፣ ዓረቦቹንና እስላሞቹን በይበልጥ እንደሚማርክ ጥርጥር የለውም:: ኤርትራን እኛ ፈጥረን አሁን ካለችበት ደረጃ ካደረስናት በኋላ፣ እሥመራንም በዘመኑ ቴክኖሎጂ ገንብተን አውሮፓዊ ሥርዓት ያለው የጣልያን ከተማ ካደረግናት በኋላ፣ እንዴት ለኃይለሥላሴ ፊውዳል መንግሥት እናስረክባታለን ? ስለዚህ፡ ..... በመስከረሙ ጉባኤ ላይ ያለንን አቅም በሙሉ አስተባብረን፣የኤርትራን የወደፊት ዕድል ወደ ነፃነት ማሻገር አለብን:: .......

የአዲሲቷ ጣልያን ሬፑብሊክ መንግሥት አዲሱ አቋም፡ ከዚህ በላይ በተገለጸው አኳኋን ከተመሠረተ በኋላ፣ በተለይ በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያን ጥያቄ ከዓለም መንግሥታት ሸንጐ ለማስረዝ፣ አንባቢን የሚማርክ የሀሰት ታሪክ ለመፍጠርና፣ አቀራረቡን ለማሳመር፣ ብዙ ሊቃውንቶች የተሰየሙበት የፕሮፓጋንዳ ኮሚቴ ተቋቁሞ፣ የተዘጋጁት ጽሑፎች፣ በያለበት መሠራጨት ጀመሩ::

...... በታሪክ ምን ጊዜም ኤርትራ፣ የኢትዮጵያ ግዛት ሆና አታውቅም። ...... የጣልያን መንግሥት በ1885 ዓ.ም፣ መላውን ኤርትራ ቅኝ ግዛት አድርጎ የያዘው፣ ከኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ነጥቆ አይደለም። ..... የጥንታዊ ታሪክ ተመራማሪዎች እንደደረሱበት፣ ይህች ኤርትራ የምትባል አገር፣ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት፣ ምንም እንኳ የጭለማ ሕይወት ተጋርዶባት የኖረች ቢሆንም፣ የራሷ የሆነ ባሕልና ቋንቋ እንደነበራት፣ የሚያመለክቱ ብዙ ማስረጃዎች ሲቀርቡ፣ ከኢትዮጵያ ታሪክና ካልቸር ጋር የሚያገናኛት አንዳች ምልክት አልተገኘም።......አክሱም ላይ ነግሠው ትግራይንና ኢትዮጵያን በአንድነት አስተዳድረው ነበር የሚባሉትም ነገሥታቶች፣ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ወደ ኤርትራ ዘልቀው አያውቁም። ..... እርግጥ፣ አልፎ አልፎ እነዚህ የትግራይ ነገሥታቶች ከአሥመራ በስተደቡብ በኩል የሚገኙትን፣ ደጋማ ሥፍራዎች ይዘው እንደነበረ ይነገርላቸዋል።

...... አድዋ ላይ፣ በኢትዮጵያና በጣልያን መካከል የደረሰው ግጭት በግዛት ምክንያት አይደለም። ሁለቱ መንግሥታቶች ውጫሌ ላይ በተፈራረሙት ውል፣ ጣልያን በኢንተርናሽናል ግንኙነቶች፣ ኢትዮጵያን ለመርዳት ዳግማዊ ምኒልክ ተስማምተዋል የሚለውን የውሉን 17ኛ አንቀጽ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ውሸት ነው ብለው በመካዳቸው ነው። ...... ከአድዋ ጦርነት በኋላ፣ በጣልያንና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከል የዕርቅ ስምምነት ሲደረግ፣ ከመረብ ምላሽ ያለው አገር በሙሉ የጣልያን ቅኝ ግዛት መሆኑን፣ አፄ ምኒልክ በፊርማቸው አረጋግጠዋል። በዚያን ጊዜ ንጉሠ ምኒልክ በሁለቱ አገሮች መካከል በደረሰው ግጭት አሸናፊ ሆነው ስለቀረቡ፣ ከመረብ ምላሽ ያለውና በጣልያን የሚተዳደረው የኤርትራ ግዛት፣ የኢትዮጵያ ስለሆነ ይመለስልኝ አላሉም። የዕርቁ ስምምነት ሲዘጋጅ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ዋና ጥረት፣ ጣልያን በኢትዮጵያ አስተዳደር ውስጥ እንዳትገባ ቃሏን እንድትሰጣቸው ብቻ ነበር።

...... በኢትዮጵያና በጣልያን ግዛት መካከል ያለው ወሰን፣ በትክክሉ የመረብ ወንዝ መሆኑ በውል ተረጋግጦ ከኖረ ከሃምሣ ዓመት በኋላ፣ የኃይለሥላሴ መንግሥት በድንገት ተነስቶ፣ ኤርትራ የኢትዮጵያ ግዛት ስለሆነች፣ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል አለባት ሲል፣ ያቀረበው ጥያቄ ተገቢ ያልሆነና መሠረት የሌለው ነው። በጥንታዊው ዘመን ኤርትራና ኢትዮጵያ በአንድ መንግሥት አስተዳደር የኖሩ ከመሆናቸውም በላይ፣ በዘርና በቋንቋ፣ በባሕልና በሀይማኖት ሁለቱ ሕዝቦች አንድ ዓይነት ናቸው በማለት፣ የኃይለሥላሴ መንግሥት ለተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች የሚያሠራጨውን የፈጠራ ሰነድ፣ የታሪክ ሊቃውንቶች አይቀበሉት ተገርመዋል። ....... ወደ ኋላ ተመልሶ ይህን የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያወራውን የጥንቱን ታሪክ መመርመር ቢያስፈልግ፣ የኤርትራን ግዛት በሙሉ ለማስተዳደሩ ማስረጃ ያለው፣ ከጣልያን በስተቀር ሌላ መንግሥት ሊኖር አይችልም። ....... እርግጥ በ1557 ዓ.ም ቱርኮች የምጽዋን ወደብ መያዛቸው ትክክል ነው። ቀጥሎም ግብፆች በቱርክ ስም ይህንኑ የምፅዋን ወደብ ይዘው፣ ለተወሰነ ጊዜ መቆየታቸው አይካድም። ይሁን እንጂ ቱርኮቹም ሆኑ ግብፆች፣ ከምፅዋ አልፈው ወደ ኤርትራ ግዛት አልገቡም። በትክክለኛው ታሪክ ከ1885 ዓ.ም ጀምሮ የኤርትራን ግዛቶች አጠቃልላ ያስተዳደረች ጣልያን ብቻ ነች። .... ስለዚህ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ በመስፋፋት ፖሊሲው ኤርትራን ለመያዝ ዋና ግቡ ስለሆነ፣ በየጊዜው የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ሁሉ፣ በፈጠራ ታሪክ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸው በተባበሩት መንግሥታት ዘንድ መታወቅ አለበት። ...... እርግጥ ኢትዮጵያ የባሕር በር ስለሌላት በአሰብ በኩል መተላለፊያ እንድታገኝ ይገባታል። ለዚህም የጣልያን

መንግሥት ከ1928 ዓ.ም ጀምሮ ድጋፉን አልነሳትም፡፡ ከዚህ ሌላ ግን ከጣሊያን ጋር ለብዙ ዘመናት በመኖር፡ ቀጥሎም በእንግሊዝ አስተዳደር ለአሥር ዓመታት በመቆየት፣ በሥልጣኔ ከፍ ያለ የመሻሻል ዕድል ያገኘው የኤርትራ ሕዝብ፣ የኢትዮጵያ የፊውዳል አስተዳደር ቀንበር እንዳይወድቅበት፣ ለትክክለኛ ፍርድና ለዲሞክራሲ መብት የቆሙ አገሮች ሁሉ፣ በጥብቅ እንዲያስቡበት ያስፈልጋል፡፡

....... ኤርትራን የፈጠረችና ምድረ በዳ የነበረችውን አገር አልምታ የሕዝቡን ኑሮ ወደ ሰብዓዊ ሕይወት ያሻገረችው ጣልያን ስለሆነች፣ ከእሷ በስተቀር የኤርትራን ሕዝብ ፍላጐት የሚያውቅና ለችግሩም መፍትሔው ምን እንደሆነ፣ ሀሳብ ማቅረብ የሚችል ሌላ አገር የለም፡፡ ስለሆነም፡ የኤርትራ ሕዝብ ነፃነቱን አግኝቶ ራሱን ችሎ እንዲተዳደር፡ የአዲሲቷ ጣልያን መንግሥትና ሕዝብ ጽኑ ድጋፉን ብቻ ሳይሆን፣ ከፍተኛ የሞራልና የማቴሪያል እርዳታውን ለማቅረብ ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡..... »

የሮማ መንግሥት ከሐምሌ 1949 ዓ.ም ጀምሮ ስለ ኤርትራ ጉዳይ የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮችን አስተያየት ለመለወጥ፡ በፕሮፓጋንዳ መስክ ያደረገው ዘመቻ ከዚህ በላይ በተገለጸው አኳኋን ነበር፡፡ ጣልያን ይህ በአዲስ መንገድ ጠንስሶ የሚያስራጨው ሀሳብ፣ ሶስት ዓይነት ጥቅም ያስገኝልኛል ብሎ ሙሉ ተስፋ አድርጓል፡፡

-- የመጀመሪያው፡ ኢትዮጵያ ኤርትራ ትመለስልኝ ብላ ያቀረበችው ጥያቄ ተገቢ አይደለም ተብሎ በተባበሩት መንግሥታት በድምፅ ብልጫ እንዲሠረዝ ነው፡፡

-- ሁለተኛው፡ አዲሲቷ የጣልያን ሬፑብሊክ፣ ቅኝ ግዛቶቿ የነበሩት አገሮች ሊቢያና ኤርትራ ነፃነት ሊሰጣቸው ይገባል ብላ ስትቀርብ፣ በጠቅላላው ኮሎኒያሊስት ባልሆኑ አገሮች ዘንድ እድናቆትንና መልካም ግምትን ለማግኘት ነው፡፡

-- ሶስተኛው፣ ኤርትራና ሊቢያ ነፃ ሲወጡ፣ በአድሚኒስትሬሽኑና በካልቸሩ ከጣልያን ጋር ተዋህደው የኖሩ በመሆናቸው፣ እዲስ ለሚያቋቁሙት መንግሥት እርዳታ ሰጭ ሆኖ ለመግባትና የተመቻቸ ቦታ ይዞ የንግድና የኤኮኖሚን ጥቅም ለማዳበር ነው፡፡

ለቅርብና ለሩቅ ጊዜ የተነደፈውን ይህንን የጣልያን ሀሳብ በተግባር ላይ ለማዋል፣ ከሁሉ አስቀድሞ የኢትዮጵያን ጥያቄ ማሰናከል አስፈላጊ ስለሆነ፣ የላቲን አሜሪካ አገሮችን ለማስጠናትና ለማስለፍ፣ በጁሴፔ ብሩዛስካ የውጭ ጉዳይ ም/ሚኒስትር የሚመራ የመልዕክተኞች ጓድ የተሰየመው ለዚህ ግብ ነበር፡፡

እንደሚታወሰው፡ ኢትዮጵያ ባላት አቅም ወደ ላቲን አሜሪካ የላከቻቸው የበጐ ፈቃድ መልዕክተኞች፡ የጐበኟቸው አራት አገሮች ብቻ ናቸው፡፡ የጣልያን ሚሲዮን ግን በልዩ እውሮፕላን እየተጓዘ የሀያ እንዱን የላቲን አሜሪካ አገሮች በማግበል፡ የኢትዮጵያን ጥያቄ እንዲቃወሙና አዲሱን የጣልያን ፖሊሲ እንዲከተሉ ከፍ ያለ ጥረት አድርጓል፡፡ በዚሁ ጉዞው፣ ጁሴፔ ብሩዛስካ በመንግሥቱ ስም ለየአገሩ መሪዎች ካቀረበላቸው ገጸ በረከቶች ሌላ፡ በኒውዮርክ የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ፣ የጣልያን ነገረ ፈጆች ሆነው በየኮሚቴው ለሚጮሁትና

ለሚያምታቱት፣ ለአርጀንቲና፣ ለጓቴማላ እና ለብራዚል ቋሚ መልዕክተኞች፣ ዋጋ ያላቸው ስጦታዎችና የኒሻን ሽልማት ለግሷል።

በኒውዮርክ የአርጀንቲና ዋና መልዕክተኛ አምባሳደር ሆሴ አርሴ "JOSE ARCE" የሊቢያ፣ የኤርትራና የሱማሌ የወደፊት ዕድል፣ በተባበሩት መንግሥታት እንዲወሰን ጉዳዩ ከቀረበበት ከመስከረም 1948 ዓ.ም ጀምሮ፣ በይፋ የጣልያን ዋና ቃል አቀባይ ሆኖ፣ የሮማ መንግሥት በየጊዜው የሚሰጠውን ልዩ ልዩ መምሪያ በየነጥቡ እየተከተለ፣ የሎቢንግ ይታገል ነው። በቅርቡም ጨምሮ 1949 ዓ.ም፣ በአፄ አክሊሉ የሚመሩት የኢትዮጵያ የበጐ ፈቃድ መልዕክተኞች አርጀንቲና ዋና ከተማ ቦነስ አይረስ (BUENOS AIRES) ሲደርሱ፣ መንግሥቱ አልቀበልም ብሎ በር እንዲዘጋባቸው ያደረገው አምባሳደር ሆሴ አርሴ ስለሆነ፣ ለደጋስፐሪ መንግሥት ያደረገው ውለታ በቀላል የሚታሰብ አይደለም። አምባሳደር አርሴ፣ በአርጀንቲና መንግሥትና በራሱ ስም ሆኖ እስካሁን ለጣልያን መንግሥት ያበረከተው እርዳታና፣ ወደፊትም የሚያቀርበው አገልግሎት እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ፣ አልፎ አልፎ በተለይ ከሚሰጠው ገርሻ ውጭ፣ በኦፊሴል የጣልያንን አንደኛ ደረጃ የክብር ከከብ ታላቅ ኮርዶን ኒሻን ተሸልሟል። በዚህ ሽልማት ክርግ መንግሥት የተሰጠውን ከፍተኛ ክብር ለማመስገን፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለሙት ስፎርሳ በጻፈው ደብዳቤ፣ እንዲህ የሚል ቃል ይገኝበታል። «.....በበኩሌ ለጣልያን መንግሥትና ሕዝብ ያለኝን ታማኝነትና የጋለ ስሜት ከመግለጽ ምን ጊዜም እንደማልቦዝን አረጋግጣለሁ። ....... ጣልያን በአዲስ መልክ የጀመረችውን የትልቅነት እርምጃ እንድትቀጥል በእገሬ ሕዝብ ስም ሆኜ የማቀርበው ምኞት፣ ጥልቅ የሆነና የወንድማማችነትን መንፈስ የያዘ ነው...»

ሁለቱ፣ በዘር ወንድማማችነትና፣ በፖለቲካም የሩቅ ሽርሽር ምርቶች የሆኑት፣ የጣልያን እና የአርጀንቲና መንግሥታቶች፣ ለሊቢያ፣ ለኤርትራና ለሱማሌ ጉዳይ፣ በመስከረም በሚከፈተው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ፣ ሕብረታቸውን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አጠንክረው አዲሱን ፕላን ለማስወሰን ተዘጋጅተዋል። እንዲሁም በኒውዮርክ ከሚገኙት የላቲን አሜሪካ አገሮች ቋሚ መልዕክተኞች መካከል፣ የጓቴማላው አምባሳደር ካርሎስ ግራሲያ (CARLOS GARCIA) እና የብራዚሉ አምባሳደር ካርሎስ ሙኒዚ (CARLOS MONIZ), ለአዲሱ የጣልያን ፕላን ከፍተኛ ጥረት ለማድረግ ቃል ስለሰጡ፣ እነሱም እንደ አርጀንቲናው መልዕክተኛ ከፍተኛ ኒሻንና ስጦታ ተቀብለዋል።

በጠቅላላው፣ በጣልያን የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር የሚመራው የመልዕክተኞች ቡድን፣ መላው የላቲን አሜሪካ አገሮችን በመጐብኘት በአዲስ መልክ ያዘጋጀውን ፕላን፣ ከሀይቲ በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ ስለተቀበሉት፣ ፍሬያማ የሆነ ውጤት ይዞ ተመልሷል።

በስሰተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት እንዳይጸድቅ በድንገት ከደጋፊነት ወደ ተቃዋሚነት ተገልብጦ ያከሸፈው የሀይቲ ዋና መልዕክተኛ ሴናተር ኤሚል ሰንት ሎት፣ አሁንም በለመደው መልክ በመስከረሙ ስብሰባ ላይ ሌላ አዲስ ዕክል እንዳይፈጥር ጣልያኖች ለማግባባል ሞክረው ነበር። ኋላ ግን ጉዳዩን ሲያጠኑት ኤርትራና ሊቢያ ነፃነታቸውን ይቀበሉ የሚል ሀሳብ ሲቀርብ፣ የሀይቲው መልዕክተኛ ለማን ሲል ማንን ይቃወማል ? የጥቁር ዘር የሆነው መንግሥት ኤርትራ ነፃ ይውጣ ሲባል፣ ከመደገፍ በስተቀር

ሌላ ምርጫ ስለሌለው፣ መለማመጥ አያስፈልግም ብለው ተውት:: በመሠረቱ ሴናተር ስንት ሉት፣ በሶስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ደህና አድርጉ ከበጠበጠ በኋላ፡ ለአራተኛው ስብሰባ ተካፋይ ሳይሆን ቀርቷል::

ከመስከረሙ ጉባኤ በፊት፡ የጣልያን ጥረት በላቲን አሜሪካ አገሮች ብቻ የተወሰነ አልነበረም:: በዓረቦቹና በእስያውያኖቹም ዘንድ መልዕክተኞች እየላከ፣ ለቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶቹ መፍትሔ ያዘጋጀውን አዲሱን ፕላን በማስረዳት፡ የሚያስፈልገውን ድጋፍ ሲሰበስብ ከርሟል:: የዓረብ መንግሥታቶች ዋናው ዓላማቸው፡ የሊቢያ አንድነት ተጠብቆ በፍጥነት ነፃነት እንዲሰጥ ስለሆነ፣ ሱማሌ ለተወሰነ ጊዜ በጣልያን ሞግዚትነት እንዲተዳደር የቀረበውን ሀሳብ አይቃወሙም:: በኤርትራም ጉዳይ፡ አገሩን ኢትዮጵያና ሱዳን ከሚከፋፈሉት ነፃነት እንዲሰጠው የታቀደውን የጣልያን ፕላን ለመደገፍ አይቸገሩም:: የጣልያን መንግሥት ባቀረበው ሀሳብ ላይ፣ ዓረቦቹ ትንሽ ጥርጣሬ ያደረባቸው፡ ስለ ሊቢያ አገሮች ነፃነት ሲነገር፡ ትሪፖሊታንያ፣ ሲረናይክና ፌዛን በአንድነት ተዋህደው፣ መሆን አለመሆኑን፡ አጠናባጁ የሮማ መንግሥት በቂ ማብራሪያ ባለመስጠቱ ነው:: በሊቢያ ጉዳይ የጣልያን እውነተኛው ፍላጐት፡ በተለይ ትሪፖሊታንያ እና ሲረናይክ የተለያየ መንግሥት እንዲቆምላቸው ነው:: ጣልያን የተመቻቸ ቦታና ጥቅም ይኖረኛል ብሎ የሚያስበውም፡ በትሪፖሊታንያ ላይ መሆኑ የታወቀ ነው:: ይሁን እንጂ ይህንን የውስጥ እቅዱን በይፋ ከማውጣት፡ እንዲሁ በደፈናው እያምታታ ለሊቢያ ነፃነት ደጋፊ ሆኖ መታየትን መርጧል::

በእስያውያኖቹም በኩል፣ የጣልያንን ሀሳብ በደፈናው የሚቃወም የለም:: በተለይም በኢትዮጵያ ላይ፡ ጥላቻውን የሚያሳየው የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዛፍሩላህ ካን፡ በሐምሌና በነሐሴ ወራቶች ውስጥ ከሮማ መንግሥት ጋር ልዩ ወዳጅነት ሲገነባ ስለሰነበተ፡ በመስከረሙ ጉባኤ ላይ የጣልያን አጨብጫቢ እንደሚሆን ሙሉ እምነት ተጥሎበታል::

## የአራቱ ኃያላኖች አቋም

ለሊቢያ፣ ለኤርትራና ለሱማሌ የወደፊት ዕድል መፍትሔ ነው ተብሎ የቀረበው የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት ከወደቀ በኋላ፡ የአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያጸድቀው ጣልያን ያዘጋጀውን አዲሱን ፕላን፣ ታላቋ ብሪታንያ ለጥቅሟ ስትል ሙሉ ድጋፏን እንደምትሰጥና፡ አሜሪካም እንደሚተባበር፡ የሮማ መንግሥት እርግጠኛ ነበር::

በሊቢያ ጉዳይ የጣልያን መንግሥት የቀየሰው አጠናባጅ መፍትሔ፡ ሁለት ዓይነት ትርጉም እንዲኖረው ታስቦ የተቀናጀ ነው:: የመጀመሪያው፡ ዓረቦቹንና እስያውያኖቹን ለማጭበርበር ሸፈንፈን ባለ አነጋገር፣ ለሊቢያ አሁኑኑ ነፃነት መሰጠት ይገባል፡ የሚለው ቃል ነው:: ሌላው የተደበቀው እውነተኛው ሀሳብ ግን፡ በሊቢያ ውስጥ ያሉት ሁለቱ ዋና ዋና አውራጃዎች፣ ትሪፖሊታንያ እና ሲረናይክ፣ ለየብቻቸው ነፃ መንግሥት ተብለው የመጀመሪያው በጣልያን፣ ሁለተኛው በታላቋ ብሪታንያ የበላይ መሪነት እንዲተዳደሩ ለማድረግ ነው:: በመሠረቱ ለትሪፖሊታንያ እና ለሲረናይክ ለየብቻቸው የኦቶኖሚ አስተዳደር እንዲሰጣቸው፡ እንግሊዞች ቀደም ሲል የሚፈልጉትና አሁንም የሚመኙት መሆኑ የታወቀ ነበር:: ይሁን እንጂ እነዚህ ሁለቱ አውራጃዎች ለየብቻቸው ነፃነት እንዲሰጣቸው፡

የጣልያን መንግሥት ልባዊ ምኞትና ጽኑ ፍላጐት መሆኑ ተብራርቶ የታወቀ እንደሆነ፣ ዓረቦቹ የሊቢያን አንድነት የሚሻረር ሀሳብ ነው ብለው እንዳያወግዙት፣ የሮማ መንግሥት ብልጥ ለመሆን እንግሊዞችን በይፋ እያናገረ፡ እሱ በጀርባ ሆኖ ለመግፋት ፈለገ፡፡ የሮማ መንግሥት በአዲስ መልክ የወጠነው ምኞት፣ በትሪፖሊታንያ እና በኤርትራ ላይ፣ የጣልያን ስሜት ያላቸው መንግሥታቶች ተቋቁመው፣ ከፍተኛ የኤኮኖሚና የሶሻል ጥቅም ለማግኘት ስለሆነ፡ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ፣ ከታላቋ ብሪታንያ ጋር መረዳዳትና መቀራረብ፣ በጣም አስፈላጊነቱን አምኖበታል፡፡ እንግሊዞች ግን ይህን በአዲስ መልክ የተወጠነውን የተጭበረበረ ሀሳብ ተቀብለው፣ የጣልያን ተባባሪ ሆነው መታየትን አልፈቀዱም፡፡

በሰኔ ወር 1949 ዓ.ም፡ የሮማ መንግሥት ለሊቢያና ለኤርትራ ነፃነት እንዲሰጣቸው ለመጠየቅ ሀሳቡን በሚያውጠነጥንበት ጊዜ፡ እንግሊዞች በራሳቸው መንገድ በመጓዝ፣ ለሲሬናይካ አውራጃ የኦቶኖሚ አስተዳደር አቋቁመናል ብለው መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ ይህንንም እርምጃ ሲወስዱ፡ የቀድሞ አስተዳዳሪውን የጣልያንን መንግሥት ማማከር አስፈላጊ ሆኖ አላገኙትም፡፡ የመንግሥቱ መሪ ደጋስፐሪና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ካርሎ ስፎርሳ፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት እኛን ሳያማክር ወይም አስተያየታችንን ሳይጠይቅ፣ እንዴት ለሲሬናይካ አውራጃ የኦቶኖሚ አስተዳደር ያቋቁማል ? በማለት ለመቃወምና ለማጉረምረም ሞክረው የሚያዳምጣቸው አጥተዋል፡፡ የታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማሲ መሪ ኧርነስት ቤቪን፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለደጋስፐሪ መንግሥት ያለው ግምት በጣም እየቀነሰ ስለሄደ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ከጣልያኖች ጋር የተለየ ውይይትም ሆነ ስምምነት መደራደር አያስፈልግም ብሎ ዘግቷል፡፡ በግንቦት 6 ቀን 1949 ዓ.ም የቤቪን ስፎርሳ ስምምነት ሉንዶን ላይ እንደተፈረመ፡ ጣልያኖች ችኩሎች በመሆናቸው፣ አጉል ፕሮፓጋንዳ ነዝተው ውጤቱን እንደአበላሹት ሁሉ፣ አሁንም አዲስ መፍትሔ አቅርበን እናስፈጽማለን በማለት የሚያደርጉትን ማምታታት፣ እንግሊዞች አላመኑበትም፡፡ የሮማ መንግሥት ኤርትራን በእጅ አዙር ለመግዛት፣ የሊቢያን አንድነትና ነፃነት እንደግፋለን እያለ፡ የዓረብ መንግሥታቶችን ሲያታልል እንደሰነበተ፣ እንግሊዞች ደርሰውበታል፡፡ ስለዚህ፣ የታላቋ ብሪታንያ ዲፕሎማቶች፣ የጣልያንን የማጭበርበር ሥራ ደህና አድርገው ስለተረዱት፣ ለመስከረሙ የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ፣ ከጣልያን ጋር ከመሰለፍ ይልቅ፣ ራሳቸው የሚፈልጉትን አቋም ይዘው፡ ብቻቸውን ለመታገል ወሰኑ፡፡

የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ያለው አቋም፣ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ጋር በመሠረቱ አብሮ የሚጓዝ መሆኑ ምንጊዜም አልተሸሸገም፡፡ በተለይ በኤርትራና በሱማሌ ጉዳይ፣ እንግሊሶ አሜሪካኖች፣ በቤቪን ስፎርሳ ስምምነት መሠረት ባለፈው ግንቦት ወር ተስማምተውበት የነበረውን ውሳኔ ዛሬም ይደግፉታል፡፡ ለአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ዝግጅት ሲደረግ፣ በአሜሪካና በእንግሊዝ መካከል መጠነኛ ልዩነት የተፈጠረው፡ ሊቢያን በሚመለከት ጉዳይ ብቻ ነበር፡፡ ይኸውም፣ በሊቢያ አንድነት አመሠራረት ላይ እንግሊዞች በጥድፊያ መሆን አይችልም በማለት፡ ትሪፖሊታንያ እና ሲሬናይካ ለየብቻቸው ነፃነታቸውን እንዲቀበሉ ያስፈልጋል ሲሉ፡ አሜሪካኖች የሊቢያን አውራጃዎች አንድነት አዋህዶ አንድ መንግሥት ለማቋቋም ጊዜ የሚፈጅበት ምክንያት ስላልታያቸው ነው፡፡ በኤርትራ ጉዳይ ግን አሜሪካና እንግሊዝ ያላቸው አቋም ኢትዮጵያን የሚረዳ እንጂ ጣልያንን የሚደግፍ አልነበረም፡፡

ከሶስቱ የምዕራብ ኃያላን መንግሥታቶች መካከል፣ ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መፍትሔ የተጣመመ ሀሳብ ይዛ፣ ብቻዋን ተጣምማ የቀረችው ፈረንሣይ ነች። በ1945 ዓ.ም ገና ከጠዋቱ ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሌ ለቀድሞ ገዥዎቻቸው ለጣልያን መመለስ አለባቸው ብላ ፈረንሣይ የተሟገተችው፣ ከጓደኛዋ ከኮሎኒያሊስት ጣልያን ጋር በመተባበር፣ በሰሜን አፍሪካ ባሉት ግዛቶቿ ውስጥ የነፃነት እንቅስቃሴ እንዳይፈጠር አፍኖ ለመያዝ ነበር። አሁን በ1949 ዓ.ም፣ ለሊቢያ የኦቶኖሚ አስተዳደር ወይም ነፃነት የተሰጠ እንደሆነ፣ የዚህ መንፈስ ወደ እነ ቱኒዚያ ተሻግሮ እንዳይበጠብጣት፣ ፈረንሣይ ስትሰጋበትና ስትከላከለው የቆየችው በሽታ እየተጠናከረ መጣባት። በቅኝ ግዛት አስተዳደር ረገድ ምንም ዓይነት ልምድ የሌላቸው አሜሪካኖች፣ ለሊቢያ ነፃነት ቢሰጥ፣ ፈረንሣይ የምትፈራበትን ምክንያት ለመረዳት ብዙ ጊዜ ወስዶባቸዋል። በወዳጆቻቸው በእንግሊዞች በኩል የፈረንሣይ ችግር የት ላይ እንደሆነ ከተገነዘቡ በኋላ፣ « .... ፈረንሣይ በሰሜን አፍሪካ፣ በቅኝ ግዛትም ሆነ በፕሮቴክቶሬ ለያዘቻቸው አገሮች፣ ሕዝቡ ሳይጠይቃት ወይም ሳያምጽባት፣ ቀደም አድርጋ የኦቶኖሚ አስተዳደር መብት ብትሰጣቸው፣ በሊቢያ ነፃነት ምክንያት የሚቀሰቀስባት ችግር አይኖርም ...... » የሚል ሀሳብ ወረወሩ። ይዘን ከአሜሪካኖች የቀረበውን አስተያየት፣ ፈረንሣይ ጨርሶ የማትቀበለው ስለሆነ፣ ሀሳቡ ወደመነጨበት ወደ ባለቤቱ እንዲመለስ ከማድረግ በስተቀር፣ ክርክርም ሆነ ውይይት አያስፈልገውም ብላ ዘጋች። አተኩሮ ለሚመለከተው፣ በሊቢያ ጉዳይ ፈረንሣይ በአሜሪካኖች ላይ ማዘኗና መበሳጨቷ ተገቢ ሆኖ አልታየም። ሊቢያ በቶሎ ነፃ መንግሥት ሆና መቆም አለባት ብላ አዲሱን መፍትሔ ያዘጋጀችው፣ የፈረንሣይ ዋና ወዳጅ ኮሎኒያሊስቷ ጣልያን ነች። ሀሳቡም በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ እንዲጸድቅ በላቲን አሜሪካ፣ በመካከለኛው ምሥራቅና በእስያ አገሮች ዘንድ፣ ከፍተኛ ጥረት አድርጋ ብዙ ድጋፍ የሰበሰበችው የፈረንሣይ ዋና ወዳጅ አዲሲቷ ጣልያን ነች። ስለዚህ፣ አጠገቧ ያለውን ከዱተኛ ጓደኛዋን የሮማን መንግሥት በመውቀስ ፋንታ፣ ሀዘኗ ወደ ዋሽንግተን ለምን እንደተጓዘ፣ ለማንም ግልጽ አልነበረም። በኤርትራ ጉዳይ ከመነሻው ጀምሮ እንደታየው፣ ፈረንሣይ አይኗን ጨፍና ያለ አንዳች ይሉኝታ ጣልያንን ስትደግፍ እንደኖረች ይታወሳል። በነሐሴ ወር 1949 ዓ.ም የተቃዋሚ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ከላቲን አሜሪካ ጉዞአቸው ሲመለሱ በፓሪስ አልፈው፣ የፈረንሣይን የዲፕሎማሲ መሪ ሮበርት ሹማንን ባነጋገሩበት ጊዜ፣ ከኤርትራ ግዛት ከምዕራባዊው ቆላ በስተቀር ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል፣ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ጋር ድጋፋችንን በድጋሚ እናጸናለን የሚል ቃል ተሰጥቷቸው ነበር። አሁን ግን ኤርትራ ሳይከፋፈል የግዛቱ አንድነት ተጠብቆ ወዲያውኑ ነፃነቱን መቀበል አለበት ብላ፣ ጣልያን የወጠነችውን ሀሳብ፣ የፈረንሣይ ሪፐብሊክ በምን መልክ እንደምትየው፣ በጉባኤው ዋዜማ አስተያየቷን ፈጥና መስጠት አልፈለገችም።

የሶቪየት ሕብረት መንግሥት፣ ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች፣ ለሶስተኛ ጊዜ የሚያቀርበው መፍትሔ፣ ከሌሎቹ ኃያላን መንግሥታቶች አቋም የተለየ እንዲሆን ፈልጓል።

1. ሊቢያ፣ አሁኑኑ እንደነቷ ተመሥርቶ ነፃነቷ ተሰጥቷት መንግሥት እንድትቆምና፣ በአገሩም ላይ እስካሁን ሰፍረው የቆዩት የምዕራብ የጦር ኃይሎችና አስተዳዳሪዎች፣ በፍጥነት ለቅቀው እንዲወጡ፣

2. ኤርትራና ሱማሌ፡ ለአምስት ዓመታት በተባበሩት መንግሥታት ሞግዚትነት ከተዳደሩ በኋላ ነፃነታቸውን እንዲቀበሉ፣

3. በኤርትራ ግዛት ውስጥ ያለው የአሰብ የባሕር ወደብ፡ ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዲሰጥ፡ ለመጨረሻ ጊዜ ከሶቪየት ሕብረት መንግሥት የተዘጋጀው ረቂቅ ውሳኔ ያመለክታል።

ይዘ ለሶስተኛ ጊዜ ከሞስኮብ የተዘጋጀው ረቂቅ መፍትሔ፣ ምንም እንኳን የሊቢያ አንድነትና ነፃነት የጊዜ ገደብ ሳይወሰንበት በፍጥነት መፈጸም አለበት የሚል ቢሆንም፡ ዓረቦቹም ሆኑ እስያውያኖቹ ከሞስኮብ ጋር ሆነው ማጨብጨብን አልፈለጉም። ለአንዳንድ ጥቅም ሲባል ከሞስኮብ ጋር እየተቀራረብን የኮሙኒዝም ወባ ከሚነድፈን፡ በሩቁ ሆነን በጤና መኖር ይሻለናል ብለዋል። የሶታሊን መንግሥት ግን ተስፋውን ሳይቆርጥ፣ በመልማት ላይ የሚገኙትን አገሮች በሙሉ ማርኮ ቀይ ባንዲራ ስቅለው እንዲሰለፉለት ጥረቱን ይቀጥላል።

እንግዲህ፡ የተባበሩት መንግሥታት አራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት፣ በዋዜማው የሚታየው የአራቱ ኃያላን መንግሥታት አቋም ሲመዘን፣ በኤርትራ ጉዳይ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ በስተቀር፣ ከሌሎቹ ከመስኮብና ከፈረንሣይ፡ ኢትዮጵያ የምትጠብቀውን ድጋፍ እንደማታገኝ መገንዘብ ግልጽ ነበር። የማይተኛላት ጠላቷ የጣልያን መንግሥት ዋና ምኞት፣ የአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ለኢትዮጵያ የአሰብን የባሕር በር ብቻ ሰጥቶ እንዲያሰናብታት ነው። ጣልያን ይህንን ጽኑ ምኞቷን ከግብ ለማድረስ፣ ሎጥሮቿ የሆኑት የላቲን አሜሪካ አገሮች ከበሮ እየደለቁ ተሠልፈውላታል። ዓረቦቹና እስያውያኖቹ፡ የሶቪየት ሕብረትና ሳቴሊቶቹ፡ ኤርትራ ነፃነቷን ትቀበል የሚል ሀሳብ ሲቀርብ ለመቃወም ስለማቸገሩ፡ ወደዱም ጠሉም ድጋፍ ይሰጣሉ ብላ፣ ጣልያን በሙሉ ተስፋ ጠብቃለች።

## ጠቅላላው ጉባኤ ሥራውን ሲጀምር

« ...... ነገር በቶሎ ሳይቆረጥ ውሎ ሲያድር ብዙ ጊዜ ለጠላት ይመቻል፣ ለተንኮል ይበጃል ...... » ሲሉ ጭንቀታቸውን የገለጹት ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን፡ አንዳንዶቹ እንደሰጡት ትርጉም፣ ከፍርሃት የመነጨ ስሜት ሳይሆን፣ አርቆ ከመገመት የተነሳ ነው።

የበጋው ወራት አልቆ የበልግ ሲጀምር እንደተለዋወጠው አየር፣ የኤርትራም ዶሴ ለአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የቀረበው፣ ከአራት ወራት በፊት ከነበረበት ቦታ ተፈናቅሎ፣ በጠላት ተንኮል ተዘበራርቆ ነበር። የጣልያን መንግሥት የኢትዮጵያን ጥያቄ ለማሰናከል፣ በአራት ወራቶች ውስጥ ሌት ተቀን በመሥራት የጠመጠመው ተንኮልና የነዛው ፕሮፓጋንዳ፣ የብዙዎቹን አባል አገሮች አቋም ለማቃወስ በቅቷል። ብዙዎቹ መልዕክተኞች፡ ባለፈው ግንቦት ወር በተካሄደው ጉባኤ ላይ፣ እጅግ ከፍ ባለ ድምፅ የደገፉትን የኤርትራን መፍትሔ፡ በመጀመሪያ ደረጃ እንዲታይ አልፈለጉም። ስምምነት አጥተው መወሰን አቅቷቸው የነበረውን፣ የሊቢያንና የሱማሌን ጉዳይ ጣልያን እንደሚፈልገው በቅድሚያ ለመፈጸም መዘጋጀታቸው ያልተጠበቀ ነበር።



ከግራ ወደ ቀኝ የጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የ U.N የፖለቲካ ኮሚቴ ሊቀመንበር እና የእንግሊዙ በ U.N ነዋሪ መልዕክተኛ፣ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፡

(ጥቅምት 1949)

-- እንደ አርጀንቲናው አምባሳደር ሆሴ አርሴ የመሳሰሉት የላቲን አሜሪካ መልዕክተኞች፣ ከሮማ መንግሥት በተሰጣቸው ገጸ በረከትና መምሪያ፣ ጉባኤው ሲከፈት የኢትዮጵያ ጥያቄ እንዲሠረዝ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ተጠናክረው ቀርበዋል::

-- ከእስላምና ከእስያ አገሮች መካከል፣የሐምሌንና የነሐሴን ወራት ከጣልያኖች ጋር ሲወዳጅ የከረመው፣ የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዛፍሩላህ ካን፣ (ZAFRULLAH KHAN) ኢትዮጵያን ከጠላቷ ጋር ሆኖ ለማጥቃት ተዘጋጅቶ መጥቷል::

በፓሌስቲን የተቋቋመው የእሥራኤል መንግሥት፣ የተባበሩት መንግሥታት አባል እንዳይሆን፣ ኢትዮጵያ ተቃውማ ያበረከተችላቸውን እርዳታ ዓረቦቹ ረስተውት፣ ለሊቢያ ነፃነት ፍለጋ፣ የጣልያን ደጋፊዎች ሆነው ተሠልፈዋል:: የኢትዮጵያ ድጋፍ የተነፈጋት እሥራኤልም ቂሟን ለመወጣት፣ በኤርትራ ጉዳይ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንግሥት ለማበሳጨት ወሰነች:: አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የአሜሪካኖቹን ቁጣ ችላ ብለው፣ የእስራኤልን የተባበሩት መንግሥታት አባልነት የተቃወሙት፣ ለኤርትራ ጉዳይ የዓረቦቹን ድጋፍ ማግኘት ለኢትዮጵያ ይጠቅማል ብለው ነበር:: ነገር ግን ከዓረቦች ጋር የሚደረግ ወዳጅነት፣ እንደተለዋዋጩ አየር፣ በየጊዜው የሚቀያየር ስለሆነ፣ በግንቦት 17 ቀን ለኢትዮጵያ የሰጡትን ድጋፍ፣ በመስከረሙ ስብሰባ ላይ ለጣልያን ሲሰውጡ የሕሊና ችግር አላጋጠማቸውም::

ለኤርትራ ጉዳይ፣ ጣልያን በኩል ሁለት ዓይነት መፍትሔዎች ተጠንስሰዋል:: <u>የመጀመሪያው ምርጫ</u>፣ ኤርትራ አሁኑኑ ነፃነቷ ተሰጥቷት መንግሥት እንድታቋቁም የተባለው ሀሳብ ነው:: <u>ይህ የማይቻል ከሆነ</u>፣ አምስት አባል አገሮች የሚሰየሙበት የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን፣ ወደ ኤርትራ ተልኮ የሕዝቡን ፍላጎት እንዲያጣራና፣ ለሚቀጥለው ዓመት ራፖሩን እንዲያቀርብ፣ የሚል ሀሳብ ተወጥኗል:: ይህ ሁለተኛው ሀሳብ፣ በአብዛኛዎቹ አባል መንግሥታቶች ሲደገፍ፣ የሚመረጡት የመርማሪው ኮሚሽን አባሎች ከእነዚሁ ከጣልያን ጠበቆች መካከል እንዲሆኑ የሮማ መንግሥት ወገኖቹን አደራ ብሏል::

እንግዲህ፣ የአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ዓመታዊ ጉባኤ ሲከፈት፣ ጠቅላላው ስዕል እንደሚያሳየው፣ የኤርትራ ጉዳይ መልኩን እየለወጠ፣ ኢትዮጵያ ከለፋችበት መንገድ እየሸሸ፣ ወደ አልተጠበቀ አቅጣጫ መጓዙን ነው:: የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልዕክተኞችም፣ በኒውዮርክ የትናንት ደጋፊዎቻቸው የነበሩት ዛሬ ተቃዋሚዎቻቸው ሆነው ሲመጡባቸው፣ እነዚህን ሁሉ ያልተጠበቁ ጠላቶች ለመቋቋም፣ ምን ያህል ከባድ ችግር እንደገጠማቸው መገመት ይቻላል::

ማክሰኞ መስከረም 20 ቀን 1949 ዓ.ም፣ የተባበሩት መንግሥታት አራተኛው ዓመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ በአፊሴል ሲከፈት፣ ከቀረቡለት አጀንዳዎች መካከል፣ በአሥራ ዘጠነኛው ቁጥር ላይ የተመደበው፣ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች የሊቢያ፣ የኤርትራና የሱማሌ ጉዳዮች ነበሩ::

ጉባኤው ሥራውን በጀመረ ማግሥት መስከረም 21 ቀን 1949 ዓ.ም፣ የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲን አቸሰን (DEAN

ACHESON) በሰጠው መግለጫ፣ « ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መፍትሔ መስጠት ከዚህ ስብሰባ የሚጠበቅ ትልቁ ተግባር ነው » በሚል ቃል ካስጠነቀቀ በኋላ፣ « ..... በሶስተኛው ጠቅላላ ስብሰባ ጊዜ፥ በሚገባ ተጠንቶ በጣም ከፍተኛ የሆነውን የአባል መንግሥታቶችን ድጋፍ ያገኘው የኤርትራ ጉዳይ፣ በዚሁ በታሰበለት መንገድ እንዲጸድቅ የአሜሪካ መንግሥት አጥብቆ ይጠይቃል ...... » አለ:: ዲን አቸሰን ስለ ሌሎቹ ቅኝ ግዛቶች አስተያየቱን ሲሰጥ፣ ሊቢያ አንድነቷ ተመሥርቶ ከሶስት ወይም ከአራት ዓመታት በኋላ ነፃነቷን እንድታገኝ፣ ሱማሌም ለነፃነት ብቁ ለመሆን እስከምትችል ድረስ፣ ለተወሰነ ጊዜ በጣልያንሞግዚትነት እንድትተዳደር፥ የአሜሪካ መንግሥት እምነትና ድጋፍ መሆኑን ገለጸ::

የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኧርነስት ቤቨንም ባደረገው ንግግር፥ ምንም እንኳን የሊቢያን አንድነት በመመሥረት ጉዳይ፣ ከወዳጁ ከአሜሪካ የተለየ አስተያየት ቢኖረውም፥ ኤርትራንና ሱማሌን በሚመለከት፥ ዲን አቸሰን ያቀረበውን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ እንደሚስማማበት አስታወቀ::

ከኃያላን መንግሥታቶች አንዷ የሆነችው ፈረንሣይ፥ ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መፍትሔ፣ ከንደኛዋ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ጋር የሚስማማ አስተያየት ያላት ሱማሌ በጣልያን ሞግዚትነት እንድትተዳደር በቀረበው ሀሳብ ላይ ብቻ ነበር:: በተቀሩት፥ በኤርትራና በሊቢያ ጉዳይ ግን፣ አስተያየቷ በተጣራ እቋም ላይ ያልተመሠረተ እና የተወሳሰበ ሆኖ ታይቷል:: የፈረንሣይ መልዕክተኛ ሞሪስ ኩቭ ደ-ሙርቪል (MAURICE COUVE DE MURVILLES) ሲናገር፣ « ለኤርትራ የሚዘጋጀው መፍትሔ ኢትዮጵያን በሚያረካ መልክ ብቻ ሳይሆን፣ የኤርትራም ሕዝብ ምርጫና ፍላጐት በጥንቃቄ እንዲደመጥ፣ በኤርትራም ያለው የጣልያን ጥቅም እንዲጠበቅ፣ በአገሩ ለሚኖሩትም የጣልያን ዜጐች መብት ዋስትና እንዲሰጥ » በማለት፥ ቀላልፎ ያቀረበው ሀሳብ፣ የውሳኔ ረቂቅ ለሚያዘጋጁት ኤክስፐርቶች ግልጽ አልነበረም:: እንደዚሁም ለሊቢያ ጉዳይ ከፈረንሣይ የቀረበው ሀሳብ፣ ለየትኛውም ወገን የሚያረካ ሆኖ አልታየም:: ለሊቢያ መፍትሔው፣ በመሠረቱ ነፃነት መስጠት መሆኑን የሚደግፍ ይመስልና፣ ይህንን ለመፈጸም ጊዜው መቼ እንደሆነ ዛሬ መወሰን አይቻልም በሚል ቃል ያደፈርሰዋል:: ወዲያው ከዚሁ ጋር አያይዞ፣ ሶስቱም የሊቢያ አውራጃዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን፣ ለእያንዳንዳቸው መንግሥት እንዲቋቋምላቸው ሲጠይቅ፣ ዓረቦቹና እሥያውያኖቹ በጣም የሚፈልጉትን የሊቢያን አውራጃዎች በአንድ መንግሥት ጥላ ሥር እንዳይሰበሰቡ መቃወሙን ያሳያል:: ከዚሁ ይቀጥልና ደግሞ፣ ጣልያን በትሪፖሊታንያ ላይ ያላት ጥቅም እንዲጠበቅላት ያስፈልጋል የሚል ሀሳብ ሲሰነዝር፥ ኮሎኒያሊስት ጓደኛውን ለማስደሰት የሚጥር መሆኑን ያመለክታል:: በጠቅላላው ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መፍትሔ ይሆናል በማለት፣ ከፈረንሣይ በኩል የቀረበው አስተያየት፣ <u>የተዘበረቀ እጅብ የበዛበት ሙሽሬ</u> ስለመሰለ፣ ከተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች መካከል ሀሳቡን የሚከተል አልተገኘም::

በዚህ አኳኋን፣ ዳኞች በመብዛታቸው ምክንያት ፍርድ የዘገየባቸው፥ እነዚህ ያልታደሉ የቀድሞ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች፣ የተባበሩት መንግሥታት አራተኛው ዓመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ ሲጀመር፣ አሁንም የወደፊት ዕድላቸው በቀላሉ የሚወሰን መስሎ አልታየም:: ከአራቱ ኃያላን መንግሥታት ከተገለጹት ሀሳቦች በስተቀር፣ ከየአባል አገሮች እየተዘጋጁ የሚቀርቡት መፍትሔዎች፥ ቁጥራቸው ስለበረከተና

ሁኔታዎቹም ባለፈው ግንቦት ወር ከነበሩበት በይበልጥ የተወሳሰቡ በመሆናቸው፣ በፖለቲካ ዋና ኮሚሲዮን ተጣርተው ለውሳኔ እንዲቀርቡ ጠቅላላው ጉባኤ አዘዘ::


ከሚያዝያ 5 እስከ ግንቦት 18 ቀን 1949 ዓ.ም ድረስ፣ በኒውዮርክ የተካሄደው የሶስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ፣ ለእነዚሁ አገሮች ጉዳይ ተጠንቶ ለውሳኔ እንዲቀርብ ያደረገው፣ በዚሁ በድርጅቱ የፖለቲካ ዋና ኮሚሲዮን እንደነበረ ይታወሳል:: እነዚህ ዶሴዎች፣ አሁንም እንደገና ተመልሰው እንዲመረመሩና ተጣርተው ለውሳኔ እንዲቀርቡ፣ ወደ ፖለቲካው ኮሚሲዮን የተላለፉት፣ ጣልያን ባከማቸው ተንኮል ምክንያት ስለሆነ፣ ለኢትዮጵያ መልዕክተኞች ድርጊቱ የሚያሳዝንና የሚያበሳጭም ነበር::

# የኤርትራ ጉዳይ በዋናው ኮሚሲዮን፤

ከጠቅላላው ጉባኤ የተላለፈለትን የኤርትራን፣ የሊቢያንና የሱማሌን ጉዳዮች ለማጥናት ዋናው ኮሚሲዮን የሥራው መክፈቻ ያደረገው፣ የእነዚህ አገሮች ቅኝ ገዢ የነበረው የጣልያን መንግሥት የሚያቀርበውን ሀሳብ በማዳመጥ ነበር:: የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኮምት ካርሎ ስፎርዛ፣ ከአራት ወራት በፊት በተካሄደው የተባበሩት መንግሥታት ሶስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ካደረገው ንግግር፣ በአሁኑ በአራተኛው ስብሰባ፣ ምን የተለየ አዲስ ሀሳብ ይዞ እንደሚቀርብ ለመስማት የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ተዘጋጅተው ጠብቀዋል::

አዲሲቷ ሬፑብሊክ የተባለችው ጣልያን፣ ለቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶ
ደህንነትና ሠላም፣ ዕድገትና ብልፅግና ከማሰብ አለማቋረጧን ከገለጸ በኋላ፣ ኮምት ካርሎ ስፎርዛ ባቀረበው አዲስ መፍትሔ፣ « ... ለሊቢያና ለኤርትራ አሁኑኑ « ነፃነት » እንዲሰጣቸው፤ ሱማሌም ለነፃነት ደረጃ እስከምትበቃበት ጊዜ ድረስ፣ በጣልያን ሞግዚትነት እንድትተዳደር ያስፈልጋል .. » አለ:: ንግግሩንም በመቀጠል፣ « .. የኤርትራ ሕዝብ ራሱን ችሎ ለማደር መብሰሉንና በኤኮኖሚም ረገድ በቂ ሀብት ያለው መሆኑን የጣልያን መንግሥት ስለሚያረጋግጥ፣ የግዛቱ አንድነት ተጠብቆለት፣ ነፃነቱን ከመስጠት በስተቀር የተባበሩት መንግሥታት ሌላ አማራጭ መፍትሔ አይኖረውም ...... » ሲል፣ ካርሎ ስፎርሳ በአዲስ መልክ የተወጠነውን የጣልያን ፕላን በዋናው ኮሚሲዮን ገበታ ላይ በኦፊሴል አቀረበ::

ዓረቦቹንና የእስላም አገሮቹን ለመማረክ ስለ ሊቢያ የወደፊት ዕድል ሲናገር፣ « ...... ትሪፖሊታንያ እና ሲሬናይክ ነፃነታቸውን እንዲያገኙ ጣልያን አጥብቃ የምትጠይቅ መሆኗን ካስታወቀ በኋላ፣ የሁለቱ ዋና ዋና አውራጃዎች ነፃነት በሚሰጥበት ጊዜ ለወደፊቱ የጋራ ጥቅማቸው በማሰብ፣ በፌዴራል ሆነ ወይም በሌላ በሚመች መልክ አንድነታቸው የሚመሠረትበት ዘዴ አብሮ መሰናዳት አለበት ...... » የሚል አስተያየት ሰነዘረ:: በዚህ በሊቢያ ጉዳይ፣ የስፎርሳ አነጋገር ዓረቦቹን ለማሞኘት በሚመች መልክ የቀረበ ሲሆን፣ የምኞቱ ትክክለኛው ትርጉም፣ የሊቢያ አንድነት ከመመሥረቱ በፊት ትሪፖሊታንያ እና ሲሬናይክ ለየብቻቸው ነፃነታቸው እንዲሰጣቸውና፣ ጣልያንም የትሪፖሊታንያ የነፍስ አባት ሆና መንግሥቱን ለመምራት እንዲያስችላት ነው:: ከአራት ወራቶች ወዲህ የጣልያን መንግሥት በሚነዛው ፕሮፓጋንዳ፣ ከእንግሊዞች ሀሳብ የተሻለ መስሎ ዓረቦቹን ሲያታልል የቆየው፣ የሊቢያ አንድነትና ነፃነት አሁኑኑ እንዲወሰን እደግፋለሁ እያለ ነበር:: አሁንም ቢሆን በኮምት ስፎርሳ ንግግር ላይ እንደተጠ ቀሰው፣ የጣልያን አቋም ሽርተት ማለቱ ለዓረቦቹ ግልጽ ሆኖ አልታያቸውም::



ካርሎ ስፎርሳ (የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር)

1. « ...... ኤርትራ ወደ ጣልያን ካልተመለሰች ሕይወት የላትም ...... » (ሚያዝያ 1949)

2. « ...... ኤርትራ ነፃ መንግሥት ሆና መቋቋም አለባት ...... »

(ጥቅምት 1949)

« ..... ለሊቢያ ነፃነት ሲሰጥ፣ የወደፊቱም አንድነት የሚመሠረትበት ዘዴ አብሮ መሰናዳት አለበት ...... » የሚለው ቃል ስለአረካቸው፣ ዓረቦቹ ለጣልያን የሚሰጡትን ድጋፍ ለመቀጠል እንጂ ለማቆም አላሰቡም:: ኤርትራ ነፃነቷ አሁኑኑ እንዲሰጣት፣ ለሊቢያም ነፃነቷ ከወደፊቱ አንድነቷ ጋር እንዲዘጋጅላት፣ የሮማ መንግሥት ያቀረበው ሀሳብ፣ ለጋስ አስተያየት መስሎ ስለተቆጠረ፣ ተገቢውን ዋጋ ለማግኘት ሱማሌ ላልተወሰነ ጊዜ በጣልያን ሞግዚትነት እንድትተዳደር፣ ዓረቦቹና እስያውያኖቹ የተጠየቁትን ድጋፍ እንደሚፈጽሙ በአዲሲቷ ሬፑብሊክ ዘንድ ሙሉ ተስፋ ተደርጓል::

ከጣልያን እንደራሴ ቀጥሎ ለመናገር፣ ድምፁ ማጉሊያውን የጨበጠው፣ የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና የመልዕክተኞች መሪ ሰር ዛፍሩላህ ካን (SIR ZAFRULLAH KHAN) ነበር:: ባለፉት የሐምሌና የነሐሴ ወራቶች፣ ከእሲያ ግሩፖች ውስጥ የጣልያን ጠበቃ እንዲሆን የተመለመለ ሲሆን፣ ወዲያውኑ ተነስቶ በሰጠው መግለጫ፣ « ..... አሁን ከኮምት ስፎርሳ የሰማነው ንግግርና የቀረበልን ሀሳብ፣ ሰብዓዊ መንፈስ የተዋሀደው ነው .... » ሲል በአክብሮት አሞገሰ:: ቀጥሎም ለሊቢያና ለኤርትራ አገሮች በቀጥታ ነፃነት እንዲሰጣቸው፣ በጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የቀረበውን ሀሳብ የፓኪስታን መንግሥት የሚስማማበት መሆኑን፣ ዛፍሩላህ ካን በጋለ ስሜት አረጋገጠ::

ከፓኪስታኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቀጥሎ የተነሱት ተናጋሪዎች፣ በተለይም የላቲን አሜሪካ ግሩፖች በኮምት ስፎርሳ የተሰጠውን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ መደገፋቸውን በድምፃቸው ሲያስተጋቡ፣ ከዓረብ አገሮችም ብዙዎቹ፣ ለሊቢያ ብቻ ሳይሆን ለኤርትራም ነፃነት እንዲሰጥ፣ በጣልያን የታቀደውን ፕላን እንስማማለን አሉ:: በዚህ ሁኔታ የዋናው ኮሚሲዮን ሥራ አጀማመር የሚያመለክተው፣ የኤርትራ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ጥያቄ እየወጣ፣ ጣልያን በተሰጠው መንገድ እያመራ ስለሆነ፣ በተቻለ መጠን ይህን በጣላት የተቀመመ አዲስ ሀሳብ ለማክሸፍና፣ ባለፈው ግንቦት ወር ወደነበረበት ቦታው ለመመለስ፣ የቆራጥ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰፊ ንግግር አደረጉ::

## ያቶ አክሊሉ መግለጫ

« ...... የኮምት ስፎርሳን ንግግር በሚገባ አዳምጠናል:: እንደሚታወቀው በመንግሥታት ግንኙነቶች መካከል፣ ከወዳጅ አገር ከሚገለጽ የሙገሳ አስተያየት ይልቅ፣ ከጠላት የሚነገረውን በጥንቃቄ ማዳመጥ ያስፈልጋል::

...... እኔ እንደተረዳሁት፣ የኛም ሆነ ከእኛ ቀጥሎ የሚመጣው ትውልድ፣ ስለ ኮሎኒያሊዝም ታሪክ በሚመራመርበትና በሚጽፍበት ጊዜ፣ ጣልያን ከሌሎቹ ጓደኞቿ የተለየች፣ በዴሞክራሲና በሰብዓዊ እምነቷ ለቀኝ ግዛቶቿ የታገለች፣ ለሕዝቦቿም ደህንነትና የወደፊት ዕድል በቅን መንፈስ የተጨነቀች ተብላ፣ በዓለም ቤተሰብ ውስጥ ለመደነቅና ለመከበር ከፍ ያለ ምኞት የዘረጋች ይመስለኛል::

...... የሕዝቦችን ነፃነትና የእኩልነት መብት ለማስከበር ሬቮሉሲዮን የሚያካሂደው የሶቪየት ሕብረት መንግሥት፣ ኤርትራ፣ ነፃነት ለመቀበል የሚያስችል አቅም ስለሌላት፣ ከነፃነት በፊት በሞግዚት አስተዳደር መቆየት



ዛፍሩላህ እና ኤፍሬም

« ...... ኢትዮጵያ የሀይማኖትና የዘር ጭቆና የሚካሄድባት አገር ስለሆነች፡ የሰውን ልጅ እኩልነትና መብት ታከብራለች ተብሎ አይጠበቅም ....... »

(ዛፍሩላህ ካን)
ኒውዮርክ 1949

« ...... በኢትዮጵያ የሀይማኖትና የዘር ልዩነት እንደማይደረግ፡ የሰው ልጅ ነፃነትና መብት እንደሚከበር፡ በነብዩ መሐመድ የተመሰከረ መሆኑን፡ የፓኪስታን መልዕክተኞች መሪ ባለማወቃቸው እናዝናለን ...... »

(ኤፍሬም ተወልደመድህን)
ኒውዮርክ 1949

የሚያስፈልጋት መሆኑን አጠንክሮ ሲያሳስበን፡ ... የለም፡ ኤርትራ ዛሬውኑ ነፃነቷን ለመቀበል ዝግጁ ናት ብላ የምትሞግተን ኮሎኒያሊስቷ ጣልያን ሆናለች።

...... ታሪክ በየጊዜው የሚለዋወጥና፣ የጊዜውን **ሁኔታ** እየተከተለ የሚጓዝ መሆኑን ሁላችንም እናምናለን። ይሁን እንጂ የአንድ **አገር** እውነተኛው ታሪክ፣ ያለፈውንና የዛሬውን አጣምሮ የሚይዝ እንጂ፣ **የቀድሞውን** የግፍ ተግባሩን ከገጹ ላይ በቀላሉ ደምስሶ፣ አዲስ በሚፈጥረው የ**ፕሮፓጋንዳ** ታሪክ፣ መልኩን ለመለወጥና ቅዱስ ለመሆን አይችልም። እኛ ኢትዮጵያውያኖች፡ ደህና አድርገን የምናውቃት ጣልያን፣ ኮሎኒያሊስትነቷንና ፋሺስታዊ ድርጊቷን፣ በተጨማሪም ግፈኛነቷንና ጨካኝነቷን ስለሆነ፣ እነዚህን ዝነኛ **ስሰሎቿን ምንጊዜም** ከታሪካችን ገጽ ላይ እንደማናጠፋላት እናረጋግጥላታለን።

...... ወደ ኋላ ጥቂት መለስ ብለን፣ ከዛሬ **አራት ዓመት** ጀምሮ፣ ጣልያን የቀድሞ ኮሎኒዎቿ ካልተመለሱልኝ ብላ ትወተውት **የነበረውን** አስልቺ ጥያቄ፣ ማስታወሱን ብንተወው እንኳን፡ የዛሬ አራት ወር **በዚሁ አዳራሽ** ውስጥ፣ ኤርትራ ለጣልያን ካልተሰጠች ሕይወት አይኖራትም እያለ፡ **የዞሞት ስርር**ሳ የመልዕክተኞች ቡድን ያደነቁረን እንደነበረ መዘንጋት **የለብንም**። ...... ሁላችንም እንደምናስታውሰው፣ እስከ ዛሬ ድረስ ከጣልያን **መንግሥት** ያለማቋረጥ ይዘንብ የነበረው ፕሮፓጋንዳ፣ አንድም ጊዜ ኤርትራ **ነጻነት ተሰጥቷት** ራሷን ችላ ትኖራለች፡ የሚል ሀሳብ ተሰንዝሮ **አያውቅም**። **ፕሮፓጋንዳው** እየደጋገመ ይናገር የነበረው፣

-- ኤርትራ ያለ ጭግዚት፣ ብቻዋን **መቆም እንደማትችል**፣

-- ወደ ኢትዮጵያ ከተቀላቀለች፣ በጭለማ **ሕይወት እንደምትሰቃይ**፣
-- ለጣልያን ከተሰጠች፣ የገነት ሕይወት **እንደሚጠብቃት**፣ ብቻ ነበር።

እንግዲህ በዚህ ሁኔታና በዚህ መልክ በጣልያን **ዲስኩር**፣ በዓለም አደባባይ ሲነገርላት የቆየችው፣ ያቺ፡ ያለ ጣልያን እርዳታ **ብቻዋን ለመቆም** የማትችለውና ያለ ጣልያን አስተዳደር ሕይወቷ አይንቀሳቀስም **የተባለችው** ኤርትራ፡ በአራት ወራት ውስጥ በተዓምር ተለውጣ፡ ነፃነቷን **ለመቀበል** የተዘጋጀች፡ በኤኮኖሚዋ ራሷን ችላ ለመኖር ብቁነቷን ያረጋገጠች አገር ሆና መገኘቷን፣ ከምት ስርርሳ በዛሬው ዕለት አዲሱን ፕሮፓጋንዳ በአፊሴል አቅርቦልናል።

..... በኢትዮጵያና በንጉሠ ነገሥቷ ስም ሆኜ፣ ለተከበራችሁ የመንግሥታት እንደራሴዎች የማሳስበው፡ ዛሬ የኮሎኒያሊስት ጣልያን መንግሥት ሀፍረት ሳይሰማው፡ ሕሊናው ሳይወቅሰው፣ ይህን የማታለያ ዲስኩር ያቀረበልን፣ እኛ የየመንግሥታቱ መልዕክተኞች፣ የትናንትናውን የማናስታውስ፡ ከዛሬው ጋር ልዩነቱን የማናተኩር፣ የወደፊቱ ግቡ ምን እንደሆነ መረዳት የማንችል፡ በምንሰማው ብቻ ተመርተን የምንፈርድ አድርጎ በመገመት ስለሆነ፣ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ሁላችንም ልናወግዘው የሚገባ መሆኑን ነው።

...... የተባበሩት መንግሥታት ድርጅታችን ለዓለም ሠላምና ደህንነት፣ ዋስትና ለመስጠት የሚጥር እንጂ፣ አንዳንድ ግፈኞች ለጥቅማቸው ማጻበሪያ የሚያቀርቡለትን አሳሳች መፍትሔ የሚቀበል አይደለም።

...... የተባበሩት መንግሥታት ድርጅታችን ለሕዝቦች መብትና ለአገሮች ነፃነት ትክክለኛ ፍርድ የሚዘጋጅበት ሸንጎ እንጂ፣ ውሸትና ማጭበርበር የሚመረትበት ፋብሪካ አይደለም።

ከዚህ በላይ ደግሞ በዓለም ላይ በፈጸመው ወንጀል የተጣለበትን ቅጣት ያልጨረሰና፣ የድርጅታችን የአባልነት መብት ያልተሰጠው መንግሥት፣ በአንዳንድ ጉዳይ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ሲፈቀድለት፣ የውሳኔ መምሪያ ነድፎ « ሌላ ምርጫ የላችሁም » እያለ መምከር አይገባውም። የጣልያን መንግሥት አዲሱ ታክቲክ፣ ምን እንደሆነ ደህና አድርገን አውቀነዋል። ያረጀውን የኮሎኒያሊስት አቀራረብና አነጋገር፣ አብዛኞዎቻችን በዛሬው ሰዓት የማንቀበለው ስለሆነ፣ « በኔዎ ኮሎኒያሊዝም» ዘዴ አጭበርብሮ ለመጠቀም የጣልያን ምኞት መሆኑን የሚያሳዩን ማስረጃዎች አሉ።

..... ኤርትራ ነፃ መንግሥት ሆና እንድትቋቋም ስንናገር፣ ከኢትዮጵያ ጋር ለመዋሀድ ፍላጐቱን የገለጸውን ሕዝብ አስከድተን፣ ወደ ጣልያን እንመልስዋለን። በአገሩም ላይ ያሉት ዜጎቻችን ሀብቱ በእጃቸው ስለሆነ፣ የሚቋቋመውን አዲስ መንግሥት እንዲመሩት እናደርጋለን።

....... ለሊቢያም አሁኑኑ ነፃነት ይሰጣት ስንል፣ ጽኑ ምኞታችን አንድነቷ እንዲመሠረት ሳይሆን፣ ትሪፖሊታንያ ለብቻዋ ነፃ መንግሥት እንድትሆንና ከእኛ ጋር ተሳስራ በእኛው እንድትመራ እናደርጋታለን። ...... ሱማሌን የሞግዚት አስተዳዳሪ ሆነን ስንረከባት፣ እንደተለመደው ለአራተኛ ጊዜ ኢትዮጵያን ለማጥቃት የጦር ማደራጃና ማሸጋገሪያ እንድትሆነን እንጠቀምባታለን። ....... የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባደረገው ዲስኩር የተናገረው፣ ቃል በቃል እንደዚህ ነው ብዬ መጥቀሴ ሳይሆን፣ <u>የኮምት ስፎርሳን ሀሳብ ትክክለኛ ትርጉም</u> ጉባኤው እንዲገነዘበው መሆኑን እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ።

የተከበራችሁ መልዕክተኞች፣

በንግግሬ መጨረሻ ላይ ለዚህ ኮሚሲዮን የጠበቀ ማሳሰቢያ የማቀርበው፣ ኤርትራ ነፃ መንግሥት ሆና መኖር ትችላለች በሚለው በጣልያን አታላይ ዲስኩር ተመርቶ፣ ትልቅ ስህተት ላይ እንዳይወድቅ ነው። እውነትን ለመሸፈንና ለማሳሳት በቀረበው በጣልያን አታላይ ሀሳብ፣ ይህ ኮሚሲዮን የሚማረክ ከሆነ፣ ውጤቱ ለአካባቢው አገሮች ሠላምንና ጸጥታን የሚያደፈርስ፣ ብጥብጥና እልቂት የሚያስከትል መሆኑ መታወቅ አለበት። መላው የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች እንዲያውቁት የሚያስፈልገው፣ <u>ለኤርትራ ነፃነቷ ኢትዮጵያነቷ</u> መሆኑን ብቻ ነው። ...... »

የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ለዋናው ኮሚሲዮን ካደረጉት ሰፊ ንግግር፣ ፍሬ ነገሩ ባጭሩ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው፣ የጣልያን መንግሥት ኢትዮጵያን በድሎ ራሱን ለመጥቀም የፈጠረውን አዲስ ፕላን ለማራከስና አቀራረቡንም ለማዋረድ በሰፊው ጥረዋል። ካለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ የጣልያን መንግሥት፣ በኤርትራ ጉዳይ በየጊዜው እየቀላመደ የሚያቀርበውን የተለያየ ሀሳብ፣ ከነ ማስረጃው በመዘርዘርና ግቡም ምን እንደሆነ አብራርተው ሲያስረዱ፣ የብዙዎቹን መልዕክተኞች ድጋፍ ለማግኘት ተስፋ በማድረግ ነበር። ነገር ግን ንግግራቸውን በአድናቆት ያዳመጡላቸውና በኃላ ጭብጨባ ደስታቸውን

የገለጹላቸው ከአፍሪካ ላይቤሪያ፣ ከምሥራቅ አውሮፓ ዩጐዝላቪያ እና ከእስያ ፊሊፒን ብቻ ነበሩ::

አቶ አክሊሉ ጣልያንን በኮሎኒያሊስትነቱ ለማጥቃት የጠቀሷቸው አስተያየቶች፣ በሌላ መንገድ ረዳታቸውን እንግሊዝንም የሚነካ በመሆኑ፣ መስኮብና ሳቴሊቶቹ ሲያጨበጭቡላቸው፤ ከምዕራባውያን መንግሥታቶች ሠፈር የፈገግታ ምልክት እንኳን አልተሰጣቸውም:: እንደ እውነቱም ከሆነ፣ ገና ለገና እንግሊዞችን ቅር ይላቸዋል ብለው የጣልያንን ኮሎኒያሊስትነት ከማስረዳትና ከማውገዝ ቢቆጠቡም ኖሮ፣ ለኢትዮጵያ የተለየ ውጤት እንደማይገኝ የታወቀ ነበር::

የኮምት ስፎርሳ መልዕክተኞች፤ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ንግግር ለጉባኤው ሀሳብ የቀረበበት ሳይሆን ጣልያንን ለመዝለፍ ብቻ የተዘጋጀ ነው በማለት " TONO AGRESSIVO " እያሉ ቢበሳጩም፤ የአቶ አክሊሉ ዲስኩር ሲፈጸም፣ የአሜሪካና የእንግሊዝ መልዕክተኞች የጭብጨባ የድጋፍ መልክ አለማሳየታቸው አስደስቷቸዋል:: ወዲያውም የጣልያን መልዕክተኛ ባደረገው ንግግር፣ ከኢትዮጵያ ሚኒስትር የቀረበውን ወቀሳ በየመልኩ እየዘረዘረ መልስ መስጠት የሚያዋጣ መስሎ አልታየውም:: በመቀጠለም የጣልያን መንግሥት በቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ ስለአቀረበው መፍትሔ፣ ከኢትዮጵያ በኩል የተነገረው ሁሉ ትክክል አለመሆኑን ሲያስረዳ፤ « ..... የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የራሱን አቋም በማስረዳት ብቻ ሳይወሰን፣ ሌሎች መልዕክተኞች የሚያደርጉትን ንግግር እየተረጐመ ለጉባኤው ለማብራራት በራሱ ኃላፊነት እርምጃ ወስዷል:: በዚህም መሠረት ከጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የተሰጠውን መግለጫ የየመንግሥታቱ መልዕክተኞች እንዳልገባቸው አስመስሎ፤ ትክክለኛው ትርጉም እንዲህ ነው እያለ ለማስረዳት ሲጥር ታይቷል:: የትርጉም ሥራ የተለየ ሞያን የሚጠይቅ ስለሆነ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ የኮምት ስፎርሳን ዲስኩር ሲተረጉም፣ በጣም መሳሳቱን ጉባኤው እንዲያውቀው ከማረጋገጥ በስተቀር ሌላ የምጨምረው የለም ....... » አለ:: ይህ የጣልያን አሽሙር በአስቂኝ መልክ የቀረበ ስለሆነ፣ በጣልያን ደጋፊዎች በተለይም በነ « ሆሲ አርሲ » ሠፈር አንድ ዓይነት የማውካካት ድምፅ ተሰምቷል::

ከኮምት ስፎርሳና ካቶ አክሊሉ መግለጫዎች በኋላ፣ አርጀንቲና እና ፓኪስታን የኮሚሲዮኑን መድረክ እየተቀባበሉ፣ ከጣልያን የቀረበውን ሀሳብ አምታተው ለማስወሰን ብዙ ቢደክሙም፣ ከአሜሪካና ከእንግሊዝ፣ እንዲሁም ከሶቪየት ሕብረት የገጠማቸው ተቃውሞ ስለጠነከረባቸው፣ ምኞታቸውን ማስፈጸም አልቻሉም::

-- የሶቪየት ሕብረት መንግሥት፤ ለሊቢያ አሁኑኑ ነፃነት፣ ኤርትራና ሱማሌ ከአምስት ዓመታት የሞግዚት አስተዳደር በኋላ ራሳቸውን እንዲችሉ ይደረግ፤ ሲል ያቀረበውን ሀሳብ ለማስወሰን፤ ሳቴሊቶቹን እነ ፖላንድን እና ቼኮስሎቫኪያን ይዞ ጥረቱን ቀጠለ::

-- ዩናይትድ ስቴትስና ታላቋ ብሪታንያ፤ ኤርትራ ከምዕራቡ ቆላ በስተቀር ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀድ፤ ባለፈው ስብሰባ በቂ ድጋፍ ያገኘው ውሳኔ እንዲጸድቅ ያስፈልጋል አሉ::



እነ ጁሴፔ ብሩዛስካ የጣልያን የበጐ ፈቃድ መልዕክተኞች፣ ለላቲን አሜሪካ መሪዎች ገጸ በረከት ሲያቀርቡ

(ሐምሌ 1949)

-- ላይቤሪያ፣ ፊሊፒንና ዩጐዝላቪያ፣ ለኤርትራ የሚዘጋጀው መፍትሔ የኢትዮጵያን ጥያቄ የሚያረካ መሆን አለበት ብለው በስፊው ተከራከሩ::

በዚህ ጊዜ የአርጀንቲናው መልዕክተኛ፡ የጣልያን ሀሳብ ከአባል አገሮች ሁለት ሶስተኛውን ድጋፍ ሊያገኝ እንደማይችል ሲገልፅ፣ ለጉዳዩ መፍትሔ የቀረቡትን ልዩ ልዩ ሀሳቦች አጣርቶ የሚያቀርብ «ንዑስ ኮሚቴ 17» እንዲቋቋም ያስፈልጋል አለ:: ወዲያው ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን በሰጡት መልስ፣ « ...... ባለፈው ዓመት በዝርዝር ተጠንቶ ያለቀለትን የኤርትራን ጉዳይ የአሁኑ ጠቅላላ ጉባኤ በማጽደቅ ፋንታ፣ በድጋሚ በዋናው ኮሚሲዮን እንዲታይ መደረጉ ሲያስገርመን፤ ይኸው ኮሚሲዮን ደግሞ በበኩሉ፣ ሌላ አጥኚ ንዑስ ኮሚቴ ማቋቋሙ አጅግ ያሳዝናል ........ » ሲሉ ተቃውሞአቸውን ገለጡ:: ከብላታ ኤፍሬም መግለጫ በኋላ፣ የአሜሪካና የእንግሊዝ መልዕክተኞች ኢትዮጵያን በመደገፍ፣ ዘተለይ የኤርትራ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ታይቶ ያለቀለት ስለሆነ፣ በንዑስ ኮሚቴ መጠናቱ የለበትም አሉ:: ወዲያው የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዛፍሩላህ ካን በቁጣ ተነስቶ፣ በኢትዮጵያ ላይ ያለውን ጥላቻ የሚገልጽ ከሥርዓት ውጭ የሆነ የዘለፋ ንግግር አደረገ::

« ....... ኢትዮጵያ በአማራ ዘር ተጨቁኖ የተያዘችና የዲሞክራሲንም ሥርዓት ከቶ የማታውቅ ስለሆነ፣ የሰውን ልጅ እኩልነትና መብት የምታከብር አገር ትሆናለች ተብሎ አይጠበቅም ..... » በሚል ቃል በጣልያን የፕሮፓጋንዳ ጋንፍሌቶች ውስጥ ከተጻፉት አንዱን በረፍተ ነገር በመጥቀስ፡ «ዛፍሩላህ ካን» የንግግሩ መክፈቻ አደረገው:: « .... እንግሊዞችና አሜሪካኖች እንደሰጡት አስተያየት፣ ኤርትራ ነፃ ሆና ለመኖር ብቁ ካልሆነች፣ ከእሷ ባልተሻለ ደረጃ ከምትገኘው ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል እንዴት ይታሰባል ? ..... ይህችን ችግረኛ የተባለች አገር ለባሰ ችግረኛ ለመዳረግ መሞከር የሚደግፉት አገሮች በእውነት ለኢትዮጵያ አስበውላት ይሆን ? ..... ኤርትራን እንድትረከብ የሚታሰብላት ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ ከአቅሟ በላይ ሆኖ የራሷን ነፃነት አደጋ ላይ እንደሚጥለው እንዴት አይታያቸውም ? ......» በማለት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች እየደረደረ ካፌዘ በኋላ፣ ዛፍሩላህ ካን ንግግሩን ሲፈጽም፣ « .... ለኤርትራ መፍትሔው ነፃነት መስጠት ነው:: ይህም የማይቻል ከሆነ፣ ሌላ መንገድ ይፈለጋል እንጂ፣ የኤርትራ ግዛት ተከፋፍሎ ለኢትዮጵያና ለሱዳን አይሰጥም ...... » ሲል ከጣልያን ጋር አስተያየቱን አስተባበረ::

ዛፍሩላህ ካን፣ ከጣልያን ጋር ሆኖ ኢትዮጵያን ለማጥቃት የተነሳው፣ በኤርትራ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የኦጋዴኑንም አውራጃ በሚመለከት ጉዳይ ነበር:: ጣልያንን ለመርዳት ዋና ግቡ ስለሆነ፣ የታላቋ ብሪታንያን መልካም ስሜት ለማግኘት ባደረገው ንግግር፣ « ...... በያለበት የተበታተኑት የሱማሌ ሕዝቦች በመጀመሪያ በኦጋዴን አውራጃ፡ ቀጥሎም በሌሎቹ በእንግሊዝና በፈረንሣይ የሚተዳደሩት ሁሉ ተጠቃልለው አንድ ሱማሌ የሚሆኑበት መንገድ ከአሁኑ መታሰብ አለበት ...... » አለ::

ከሥርዓትና ከዲፕሎማሲ መንፈስ አጅግ በራቀ መንገድ፣ ዛፍሩላህ ካን ኢትዮጵያን በመዝለፉ፣ ከብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን የተሰጠው መልስ ለጊዜውም ቢሆን ቅስሙን ሰብሮ አሳፍሮታል::

« ...... የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባደረጉት ንግግር፣ ኢትዮጵያ የዲሞክራሲን ሥርዓት የማታውቅ፣ የሰውን የእኩልነት መብት የማታከብር፣ የኤኮኖሚ አቅሟም ኤርትራን ለማስተዳደር የማይፈቅድላት ከመሆኑም በላይ፣ የራሷን ነፃነት አደጋ ላይ የሚጥልባት ይሆናል ሲሉ አሹፈውብናል። ይህን የመሰለው የዘለፋ አስተያየት በአገሬ ላይ መሰንዘሩ የሚያስገርም ብቻ ሳይሆን የሚያሳዝንም ነው። ...... በኢትዮጵያ የሀይማኖት እና የዘር ልዩነት የማይደረግበትና፣ የሰው ልጅ ነፃነትና መብት የሚከበርበት መሆኑን፣ የብዙ መቶ ዓመታት ታሪኮቻችን ምስክርነታቸውን አጉልተው ማሳየታቸውን፣ እጅግ የተከበሩት ሰር ዛፍሩላህ ካን ሳያስታውሱት በመቅረታቸው እናዝናለን .. » በሚል ቃል ብላታ ኤፍሬም ንግግራቸውን ጀመሩ።

« ...... የነቢዩ መሐመድ ደቀ መዛሙሮች፣ ከጠላቶቻቸው ከሚወርድባቸው መዓትና እልቂት ለመዳን፣ ነብዩ መክር የመራቸውና የተሰደዱት፣ ትክክለኛ ፍርድና ነፃነት ወደአለበት ወደ ኢትዮጵያ መሆኑን ለፓኪስታን መልዕክተኞች መሪ ማስታወስ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። ነቢዩ መሐመድ፣ የእምነት ተከታዮቹን ለስደት ወደ አገራችን ሲልካቸው፣ « ኢትዮጵያ በማንም ላይ በደል የማትፈጽም እውነትና ፍትህ የምትከተል አገር ነች » ብሎ ነግሯቸዋል። የነቢዩ ስደተኞች ኢትዮጵያ ከደረሱም በኋላ፣ ጠላቶቻቸው አሳድደው ሊይዟቸው በሞከሩ ጊዜ፣ በዘመኑ የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ « ..... እኔንና ኢትዮጵያን አምነው የመጡትን እነዚህን ስደተኞች ጋራውን የሚያለብስ ወርቅ ብታነጥፉልኝ እንኳን አሳልፌ አልሰጣችሁም ...» ሲል በቆራጥነት የተናገረው ቃል፣ የኢትዮጵያን መሠረታዊ የሆነ የትክክለኛ ፍትህ አቋም ያረጋግጣል። በመጨረሻም ነብዩ መሐመድ በሰጠው ድንጋጌ «ኢትዮጵያ እኛን ከበደሉን ከአረመኔ አገሮች መካከል የማትቆጠር ነች» ብሎ ማስተማሩን የተከበሩ ዛፍሩላህ ካን ቢያስታውሱት ኖሮ፣ ኢትዮጵያን የሰው ልጅ መብት የማይጠበቅባት አገር ነች ብለው ለመዝለፍ ባልቃጡ ነበር። ንግግሬን ከመፈጸሜ በፊት ለፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የማሳስበው ኢትዮጵያዊነቱን የሚያምነውና የሚጠይቀው፣ ባለጉዳዩ የኤርትራ ሕዝብ መሆኑን እንዲገነዘቡት ብቻ ነው ...... »

ከብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን በተሰጠው መግለጫ ውስጥ፣ ጐላ ብለው የተጠቀሱት የነቢዩ መሐመድ ድንጋጌዎች፣ የእስላም አገሮች መልዕክተኞችን መንፈስ ስለቀሰቀሰ፣ የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለአንድ ሳምንት ያህል በየስብሰባው ላይ የሚያደርገውን ማለካካት ቀንሶ ነበር። ሆኖም የበላ ሆድ ማረፍ ስለማይችል፣ ከአንድ ሳምንት በኋላ የጣሊያን ታዛዥነቱን አክብሮ በኢትዮጵያ ላይ ልፈፋውን ቀጠለ።

ይህ ሁኔታ በደረሰበት ሰሞን የእንግሊዝ መልዕክተኛ ወደ ለንደን ባስተላለፈው መልዕክት « ...... በሊቢያ፣ በኤርትራና በሱማሊ ጉዳይ፣ የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከጣልያንና ከዓረብ መንግሥታት ጋር የተልከሰከሰ ስምምነት ማድረጉን የሚያሳምን ማስረጃ አግኝተናል። ይህም ዜና ትክክለኛ መሆኑን « የሲረናይከው ኤሚር ኢድሪስ » አረጋግጠውልናል። እኛም እንደአየነው፣ ዛፍሩላህ ካን በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያን ጥያቄ ለማበላሸት፣ በሊቢያ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥት የሚቀርበውን ሀሳብ ለማሰናከል ቆርጦ የተነሣ ነው ...... » * ሲል አስታውቋል። የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኛ እንደገለጸው፣ የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለጣልያን ተገዝቶ ኒውዮርክ መምጣቱ አላጠራጠረም። የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ክምት ካርሎ ስፎርሳ

ታህሣሥ 18 ቀን 1949 ዓ.ም ለአገሩ ፓርላማ ባደረገው ንግግር፣ ስለ ዛፍሩላህ ካን የሰጠው አስተያየት ተጨማሪ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

« … ስለ ኤርትራ ጉዳይ የጣልያንን አቋም ለተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ለማስረዳትና በተለይም ከፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሰር ዛፍሩላህ ካን ጋር የቅርብ ግንኙነት ለማድረግ ባለፈው ጥቅምት ወር ኒውዮርክ ሄጄ ነበር። ….. የአንድ ትልቅ የእስላም መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆነው ዛፍሩላህ ካን፣ ከእስያ አገሮች በጣም ከተደነቁት ብልህ ሰዎች መካከል አንዱ ነው። የኤርትራን ጉዳይ መሠረታዊ ታሪኩንና አሁን ያለውንም ሁኔታ በዝርዝር አብራርቼ የሰጠሁትን መግለጫ በጥሞና ካዳመጠ በኋላ፣ ዛፍሩላህ ካን በሰጠኝ አስተያየት « …. የኤርትራ ሕዝብ በዘመናዊ ሥልጣኔ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በበለጠ የተራመደ ስለሆነ፤ ኤርትራውያኖች ኢትዮጵያን ይመሩ እንደሆነ ነው እንጂ በጣም ወደ ኋላ የቀሩት ኢትዮጵያውያኖች ኤርትራን ማስተዳደር አይችሉም … » አለኝ። …… የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይህንን የነገረኝን መልካም አስተያየት በዲስኩሩ ውስጥ ጨምሮ ለጉባኤው እንዲናገር ጠይቀው፣ ያለ አንዳች ማመንታትና በሚያስደንቅ ብርታት አስፈላጊውን ፈጽሟል። …. * »

ከዚህ በላይ እንደታየው የኮምት ስፎርሳ ንግግር የሚያስገነዝበው፣ የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለሮማ መንግሥት እንዲያገለግል በሚገባ የተመለመለ መሆኑን ነው። ዛፍሩላህ ካን ለተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ስለ ኤርትራ ጉዳይ ያደረገው ንግግር፣ ምንም እንኳን ቃል በቃል ኮምት ስፎርሳ እንዳቀረበው ባይሆንም፣ መሠረታዊውን ሀሳብ የለቀቀ አይደለም። « ….. ኤርትራ በነፃነት ራሷን ችላ ለማደር ብቁ ካልሆነች ከእሷ በባሰ ደረጃ ላይ የምትገኘው ኢትዮጵያ፣ ኤርትራን ብትወስድ ከአቅሟ በላይ ሆና ነፃነቷን አደጋ ላይ አይጥለውም ወይ ? …… » ሲል፤ በማሾፍ ያቀረባቸው ጥያቄዎች የጣልያንን አስተያየት በመመርኮዝ መሆኑ አያከራክርም።

ከመቶ ሀምሣ ዓመታት በላይ በኮሎኒያሊስቶች ሲገዛ ከኖረ በኋላ፣ ነፃነቱ ከተሰጠው ሁለት ዓመት ያልሞላው አገር የዲፕሎማሲ መሪ፣ ለኮሎኒያሊስት ጣልያን መሣሪያ ሆኖ፣ ኢትዮጵያን ለመጉዳት መምከሩን ብዙዎቹ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች በትዝብት ተመልክተውታል። በዚያን ዘመን ሀይማኖትን በመመርኮዝ የሕዝቦችን አንድነት አፍርሰው፣ በዓለማ ዓለም ውስጥ ከሚደናበሩት አገሮች መካከል፣ በግንባር ቀደም የሚታወቀው ማን እንደሆነ፣ ዛፍሩላህ ካን አያውቅም አይባልም። ኢትዮጵያ ግን፣ ሌላው ቢቀር ለሕዝቧ ነፃነትና ክብር፣ ከኮሎኒያሊስቶች፣ በተለይም የዛፍሩላህ ወዳጅ ከሆነው ከጣልያን ጋር ያደረገችውን አስደናቂ ተጋድሎና ያገኘችውን ድል ዓለም ያከበረው ስለሆነ፤ እነዚህ ለጥቅም የተደለሉ ሰዎች የሚያደርጉት ወሽካታ ዲስኩር የሚያኮራ ታሪኳን ሊያጉድፈው አይችልም። ይሁን እንጂ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ ፍርድ የሚከናወነው በአባል አገሮች የድምፅ ብልጫ ስለሆነ፣ ገንዘብ ያለው ጠላት፣ ብዙ ድምፅ እየገዛ፣ ኢትዮጵያን እንደሚበድላት የታወቀ ነበር። የነፓኪስታንና የነ አርጀንቲናም ጩኸት ግቡ፣ ፍርዱን ለጣልያን ማስገኘት መሆኑን ያልተረዳ የለም።

ዋናው ኮሚሲዮን፤ በአንድ በኩል እነ ዛፍሩላህ ካን እና እነ ሆሴ አርሴ በሚደልቁት የጣልያን ከበሮ እየደነቀረ፤ በሌላ በኩል ከየአቅጣጫው የሚጉርፉት የተወሳሰቡ መፍትሔዎች እያዋከቡት፤ ጠቅላላው ጉባኤ የጠየቀውን፤ የሁሉንም ሀሳብ በአንድ መልክ የሚያስተባብር ረቂቅ ውሳኔ ለማዘጋጀት የማይችል ሆነ።

በዚህ ጊዜ አብዛኛዎቹ የኮሚሲዮኑ አባሎች፡ ንዑስ ኮሚቴ እንዲቋቋም ቀደም ሲል ከአርጀንቲና መልዕክተኛ የቀረበውን ሀሳብ ወደ መደገፍ አዘነበሉ። የጣልያን ዋና አፈ ጉባኤ የሆነው አምባሳደር ሆሴ አርሴ፡ ይህችን ምልክት ሲያገኝ፡ ወዲያውኑ ላቲኖቹን፣ ዓረቦቹንና እስያውያኖቹን አስተባብሮ ከፍ ያለ የድጋፍ ድምፅ በማሰባሰብ የሚፈልገው ንዑስ ኮሚቴ እንዲቋቋም ተወሰነለት። የሆሴ አርሴ ደስታ፣ <u>ንዑስኮሚቴው በመቋቋሙ ብቻ ሳይሆን፡ ከብዙ ንትርክ በኋላ ከተመረጡትም ሀያ አንድ አባሎች መካከል፣ አብዛኛዎቹ፡ የጣልያን ባለሚሎች እንዲሆኑ በማስደረጉ፣ተጨማሪ ድል በማግኘቱ ነው።</u> የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ አቶ

*(FO-317-37899) *(ARCHIVO DIPLOMATICO ROMA DEC . 1949)

አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ከብስጭት የተነሣ ለዚሁ ንዑስ ኮሚቴ አባሎች ምርጫ ለአንድ ጋዜጠኛ ስሜታቸውን ሲገልጹ፣ « የጣልያንያን ኮሚቴ » ተብሎ እንዲሰየም ያስፈልጋል እስከ ማለት ደርሰው ነበር። « ንዑስ ኮሚቴ 17 » በተመረጡት 21 አባሎች ጥናቱን ሲጀምር፣ ዋናው ኮሚሲዮን በበኩሉ፣ በቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛት አገሮች ውስጥ ያሉት፣ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች የሚሰጡትን መግለጫ ለማዳመጥ ወሰነ።

በንዑስ ኮሚቴ አሥራ ሰባት (17) ከተመረጡት ሀያ አንድ (21) አባሎች መካከል፣ ለኢትዮጵያ ጥያቄ ድጋፋቸውን የሚሰጡት አገሮች አራት ብቻ ሲሆኑ፡ የጣልያንን ዕቅድ የሚቃወሙት ደግሞ ሰባት ናቸው። እነዚህም፡

| ኢትዮጵያን የሚደግፉ አገሮች፡ | የጣልያንን ዕቅድ የሚቃወሙ፡ |
|---|---|
| 1. ታላቋ ብሪታንያ | 1. ሶቪየት ሕብረት |
| 2. ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ | 2. ፖላንድ |
| 3. ላይቤሪያ | 3. ቼኮስሎቫኪያ |
| 4. ዳንማርክ | |

ከሌሎቹ አሥራ አራት አገሮች መካከል፡ ከሕንድ የአብስቴንሽን አቋም በስተቀር፡ አሥራ ሶስቱ አባሎች በአርጀንቲና እና በፓኪስታን መሪነት፡ የጣልያንን ኀሳብ እንደሚደግፉ የታወቀ ነበር።

# ኤርትራ በኢብራሂም ሡልጣን አስተያየት

አርብ ጥቅምት 7 ቀን 1949 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በፊት በአራት ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ በካናዳ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሚስተር ሌስተር ፒርሰን (LESTER B. PEARSON) ሊቀመንበርነት፣ ዋናው ኮሚሲዮን ሥራውን ሲጀምር፣ የመጀመሪያው ተናጋሪ በቅርቡ በጣልያን መንግሥት በጀት አዲስ የተፈጠረው

የኤርትራ ነፃነት ጠያቂዎች ግንባር የተባለው ድርጅት፣ (BLOCCO INDIPENDENTE) ዋና ፀሐፊ፣ ግራዝማች ኢብራሂም ሡልጣን ነበር::

የኤርትራ ሕዝብ ከነፃነት በስተቀር ሌላ መፍትሔ እንደማይቀበል፣ የአራተኛውን የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ለማሳመን፣ በጣልያን መሪነት በኒውዮርክ ሀሳቡ ተጸንሶ፣ በሮማ ጸድቆ የተመረቀው፣ ይህ የነፃነት ጠያቂዎች ግንባር፣ በኤርትራ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ የሚያጠቃልል ትልቅ ድርጅት እንዲሆን፣ የደጋፊዋ መንግሥት ብዙ ደክሞበታል::

ለዚህ ለትልቁ ድርጅት መሪነት በጣልያን የተመለመለው ኢብራሂም ሡልጣን፣ ፓርቲውን ለማደራጀት በሮማ ከተማ በሚንፈላሰስበት ሰሞን፣ ስለ አዲሉ ዕቅድ ከደጋፊዎቹ ጋር በቅድሚያ መመካከር፣ ከድርጅቱ ውስጥ ይዋሀዳሉ ከተባሉትም ፓርቲዎች ጋር ውል መደራደር፣ አስፈላጊ መስሎ አልታየውም:: ዕድሜ ለጣልያን መንግሥት እንደልብ የሚፈስ ሊሬ ስለአለ፣ በኤርትራ ያሉትን ዋና ዋና የተቃዋሚ ፓርቲዎች በነፃነት ግንባር ሥር ለአንድነት ለማዋሀድ ችግር አይኖርም የሚል ዕምነት አደረበት:: ነገር ግን በነፃነት ግንባር ውስጥ ወዲያውኑ ይጠቃለላል የተባለው « የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ » ፓርቲ ተከታዮች፣ ኢብራሂም ሡልጣን ከጣልያን ጋር የሚፈተፍተው ምሥጢሩ ምን እንደሆነ ለመረዳት ጊዜ አልወሰደባቸውም:: ሀሳቡ የጣልያን፣ ዝግጅቱ የጣልያን፣ ገንዘቡ የጣልያን፣ ጥቅሙ ለጣልያን መሆኑ ወዲያው ስለተገለጠ፣ ሼህ አሊ ራዳይ በምዕራቡ ቆላ፣ ቃዲ መሐመድ ዑመር በምሥራቁ ቆላ፣ የኢብራሂም ሡልጣንን ድርጅት አውግዘው በየክፍላቸው አዳዲስ የእስላም ሊግ ፓርቲ መሠረቱ::

አዲሱ « የነፃነት ግንባር » በነዚህ በምዕራቡና በምሥራቁ አውራጃዎች በተቋቋሙት ሁለት ፓርቲዎች ኃይል ድራሹ ከመጥፋቱ በፊት፣ ኢብራሂም ሡልጣን በቂ ገንዘብ ስለ አለው፣ (ዕድሜ ለጣልያን) መልዕክተኞች አስልፎ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ስፊ ዲስኩር ለማድረግ ኒውዮርክ መጣ:: ከዚህ የነፃነት ግንባር በጣልያንኛ (BLOCCO INDIPENDENTE) ከተባለው የፖለቲካ ፓርቲ የሚቀርበው ሀሳብ፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዘንድ የጠቅላላው የኤርትራ ሕዝብ ፍላጐት ነው ተብሎ እንዲደመጥና፣ የሚጠየቀውም ነፃነት እንዲሰጥ፣ በጣልያን መንግሥት በኩል ያልተደረገ ጥረት አልነበረም:: ለምሣሌም ያህል፣ ከአንድነቶች ፓርቲ ዋና ፀሐፊ ከአቶ ተድላ ባይሩ በፊት፣ በዋናው ኮሚሲዮን ላይ የኢብራሂም ሡልጣን ዲስኩር እንዲቀድም መደረጉ፣ አንድ ማስረጃ ነው::

ጥቅምት 7 ቀን 1949 ዓ.ም የኤርትራ የነፃነት ግንባር ዋና ጸሐፊ፣ ለዋናው ኮሚሲዮን ያደረገው ንግግር፣ ቀደም ሲል የጣልያን መንግሥት በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያን ጥያቄ ለመቃወም፣ በአስራጫቸው የፕሮፓጋንዳ እትሞች ላይ የተጠቀሱትን ሀሳቦች የተመረከዘ ነበር:: የነፃነት ግንባር አጠቃልሏቸዋል በተባሉት ልዩ ልዩ ፓርቲዎች አማካይነት፣ ከመቶ ዘጠናውን የኤርትራ ሕዝብ እወክላለሁ ብሎ የሚፎክረው ኢብራሂም ሡልጣን፣ ከሰጠው መግለጫ ዋና ዋናዎቹ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው::

« ...... ኤርትራና ኢትዮጵያ አንድም ጊዜ አብረው ያልኖሩ የኢትዮጵያም ነገሥታቶች ወደ ኤርትራ ዘልቀው የማያውቁ፣ ሁለቱም ሕዝቦች የቋንቋ ሆነ የባሕል፣ የታሪክ ሆነ የሀይማኖት፣ ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው ናቸው:: ...... በጥንታዊው የአባሲዶች (LES ABASIDES) ዘመን፣ በባግዳድ ካሊፋ

ከሚተዳደሩት የዓረብ አገሮች አንዷ ኤርትራ ነበረች። ..... የአባሲዶች ዘመን አልቆ የካሊፋ ሥልጣን ሲበታተን በየአገሩ የኢሚሮች ሥልጣን ተመሠረተ። ...... ከኤርትራ ግዛት አንደኛው ክፍል በአንድ ኢሚር ሥልጣን ተይዞ ሲቆይ፣ ሌላው ክፍል ደግሞ በአንድ የኤርትራ ተወላጅ በሆነ የእስላም መሪ ይተዳደር ነበር።

..... ከፖርቱጋሎች ቀጥሎ፣ ቱርኮች ወደ ኤርትራ መጥተው ሥልጣናቸውን ከዘረጉ በኋላ፣ አገራችን በጣልያን ኮሎኒያሊስት እስኪተያዘችበት ዘመን ድረስ (ማለት እስከ 1885 ዓ.ም ድረስ) በግብፅ ካዲዎች ስትተዳደር ቆይታለች። ...... የጣልያን መንግሥት ኤርትራን በቅኝ ግዛት የወሰደው ከግብፆች እጅ ነው እንጂ ከኢትዮጵያ አለመሆኑ በታሪክ የተረጋገጠ ነው። ..... ባሕር ነጋሽ የተባለውም የኤርትራ አስተዳዳሪ ታማኝነቱ ቀደም ሲል ለቱርኮች፣ ቀጥሎም ለግብፆች ነው እንጂ የኢትዮጵያን ነገሥታቶች አይመለከትም። ...... ስለዚህ የጣልያን ኮሎኒያሊስት የምናስተዳድረውን አገር ወስደብን ዘለው፣ መናገርና መከራከር የሚገባቸው ግብፆች ናቸው እንጂ፣ ኢትዮጵያውያኖች አለመሆናቸው መታወቅ አለበት።

...... ባለፉት አራት ወራቶች የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት ተብሎ፣ ከኤርትራ ግዛት የደጋው ክፍል በሙሉ ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ የታሰበው ሳይወሰን በመቅረቱ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከአንድ ትልቅ ስህተት በተዓምር ድኗል። የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት፣ የኤርትራን ሕዝብ ለምን ጊዜውም የማያበጣብጥና ሠላም የማይነሣ ትልቅ ጠንቅ ነበር። የደጋው ክፍል የኤርትራ ግዛት፣ ክርስቲያኖች የሚኖሩበትና በባሕልም በቋንቋም፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው የተባለው ፍፁም ውሸት ነው። ....... በሠራዬና በሀማሴን ያሉት ነዋሪዎች፣ እንደ ምፅዋዎቹ ሁሉም እስላሞች ናቸው። በመካከላቸው ጥቂት ክርስቲያኖች ቢኖሩም፣ ከጠቅላላው ነዋሪ ሕዝብ አሥር በመቶ ቢሆኑ ነው። ...... በኢትዮጵያ ነገሥታቶች በግዴታ ተነጥቆ የተወሰደው የትግራይ ሕዝብ፣ በባሕሉ፣ በዘሩና በቋንቋው አንድ ዓይነት ከሆነው ከኤርትራ ሕዝብ ጋር መቀላቀል አለበት። ...... » ካለ በኋላ፣ መላው የኤርትራ ሕዝብ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን የሚጠይቀው፣ ነፃነትን ብቻ መሆኑን አጠንክሮ በመግለጽ፡ የነፃነት ግንባር ድርጅት መሪ ንግግሩን ፈጸመ።

## 'ኢብራሂም ሡልጣን ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች ጋር*

የዋናው ኮሚሲዮን የውስጥ ደንብ እንደሚፈቅደው፣ የየአገሩ የፖለቲካ መሪዎች መግለጫቸውን ከሰጡ በኋላ፣ የስብሰባውን አዳራሽ ከመልቀቃቸው በፊት፣ ከየመልዕክተኞቹ ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች መልስ መስጠት አለባቸው። የኤርትራ « የነፃነት ግንባር » ተብሎ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተፈጠረው ድርጅት ዋና ጸሐፊ፣ ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ የቀረቡለት ጥያቄዎችና፣ ግራዝማች ኢብራሂም ሡልጣን የሰጣቸው መልሶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

* (በአዳራሹ የነበሩት አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን፣ ብላታ ዳዊት ዕቁባእግዚእ፣ አቶ ገብረመስቀል ክፍለ እግዚእ፣ አቶ ጉይቶም ጴጥሮስ)

ኢትዮጵያ፣

...... በአባሲዶች የሥልጣን ዘመን የባግዳዱ ካሊፋ ካስተዳደራቸውአገሮች አንዱ ዛሬ ኤርትራ የምትባለው አገር ከሆነች፤ በዚያን ዘመን ይህች አገር የመጠሪያ ስሟ ማን ይባል ነበር ?...... ቀጥሎም የባግዳዱ ካሊፋ ሥልጣን ከተበታተነ በኋላ፣ በኤሚሮች ዘመን በከፊል የኤርትራን ግዛት ይመራ የነበረው እስላሙ ኤርትራዊ ማን ይባላል ? ....

ኢብራሂም ሡልጣን፣

..... እኛ ወደ ኒውዮርክ ስንመጣ የጥንት ታሪካችንን የሚያስረዳውንትልቁን መጽሐፍ ይዘን አልመጣንም:: ለተባበሩት መንግሥታት የተናገርነው ዋና ዋናውን ታሪካችንን ነው:: ዝርዝር ነገር ማወቅ ከተፈለገ፣ በዓለም ታሪክ ውስጥ ፈልጎ ማግኘት ይቻላል::

በአዳራሹ ውስጥ፣

...... ሳቅ .......

ኢትዮጵያ፣

...... ላቀረብኩት ጥያቄ መልሱን አላገኘሁም:: ግራዝማች ኢብራሂም መልሱን ያልሰጡበት ምክንያት፣ ያነበቡልንን ታሪክ ከልባቸው ስለማያምኑበት ወይም በሚገባ ስላላጠኑት ይመስለኛል:: ...... በመሠረቱ ግራዝማች ኢብራሂም ያደረጉት ንግግር፣ የጣልያን መንግሥት ኢትዮጵያን ለመጉዳት የሚነዛው የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ተደጋግሞ የታተመውን ቃል ስለሆነ፣ በጠቅላላ አቀራረቡ አዲስ ነገር አላየንበትም:: ይሁን እንጂ ስለ ጥንታዊ ታሪካችን ሲጠቀሱ « ...... በአባሲዶች ዘመን ...... ኤርትራ በባግዳዱ ካሊፋ ከተገዙት አገሮች አንዷ ነች .....» ብለው ስለተናገሩ፣ የዚህ ታሪክ ትክክለኛው ጊዜ መቼ እንደነበረና፣ በዚያንም ዘመን ኤርትራ ማን ተብላ ትጠራ እንደነበረ፣ እንዲገልጹልን ጥያቄ ያቀረብንላቸው፣ ማስረጃው ለሁላችንም ግልጽ ሆኖ እንደታየን በማሰብ ነበር:: ነገር ግን የነፃነት ግንባር ድርጅት መሪ፣ ጥንታዊ ታሪካችንን የሚያሳንስ ቅጥፈት አበላሽተው ሲናገሩ፣ማስረጃውን ለማቅረብ ባለመቻላቸው እርምት መስጠት መብታችንም ግዴታችንም ይሆናል::

...... በስምንተኛው መቶኛ ዓመት አባሲዶች የተባሉት የነቢዩ መሐመድ ቤተሰቦች ሥልጣናቸውን ባግዳድ ላይ መሥርተው፣ በመላው ዓረብ አገሮች ላይ በነገሡበት ዘመን፣ ከቀይ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ያለው የኢትዮጵያ ግዛት የሚተዳደረው፣ መንበራቸው አክሱም ላይ በሆነው የኢትዮጵያ ነገሥታቶች መሆኑን ትክክለኛው ታሪክ ያረጋግጣል:: ..... ስለዚህ፤ ግራዝማች ኢብራሂምና መሪያቸው የጣልያን መንግሥት፣ አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ ሲያቋቁሙ፣ ለኤርትራ አዲስ ታሪክ ፈጥሮ ለማሳሳት የሚያደርጉት ሙከራ ከንቱ መሆኑን እንዲያውቁት እናስጠነቅቃቸዋለን::

ኢብራሂም ሡልጣን፣

..... የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የኤርትራን ሕዝብ የሚወክለውን ፓርቲ መሪ፣ የአገሩን ታሪክ አያውቅም እያሉ ለመዝለፍ አይፈቀድላቸውም:: ከዚህ ቀደም እሳቸው በፈለጉት ዓይነት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ውጭ ታሪክ የላትም እያሉ የፈጠራ ታሪክ ሲናገሩ፣ እኛ እየታዘብን መልስ አልሰጠናቸውም:: አሁን ጊዜያችንን ከማጥፋት ስለ አገራችን ስለ ኤርትራ ታሪክ፣ በዝርዝር ማወቅ



*የኤርትራ የነፃነት ግንባር መሪ ኢብራሂም ሡልጣን በU.N ንግግር ሲያደርግ፣*
*« .... በአባሲዶች ዘመን ኤርትራ በባግዳድ ካሊፋ የምትተዳደር የዓረብ አገር የነበረች ነች ...... »*

(ጥቅምት 1949)

(ፎቶ U.N)

የሚፈልጉትን በጽሑፍ ቢያቀርቡልን፣ መልሱን አዘጋጅተን በቶሎ እንሰጣቸው ነበር።

ኢትዮጵያ፣

...... ላቀረብኳቸው ግልጽ የሆኑ ሁለት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስሊሰጡኝ ባለመቻልዎ አዝናለሁ።ጥፋቱ የርስዎ ሳይሆን የዲስኩሩ አዘጋጅዎች (ጣልያኖች) መሆናቸውን ተረድቻለሁ። ....... ግራዝማች ኢብራሂም ! እርስዎ ዛሬ ምንም እንኳ ለጠላታችን ለጣልያን መሣሪያ ቢሆኑም፣ ከሶስት ዓመታት በፊት ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ያገር ፍቅር እንድነት ማህበር ያደረጉትን ጥረት አንዘነጋውም። በዚህ ምክንያት እርስዎንም ደህና አድርገን እናውቅዎታለን። እኔ የተናገርኩት፣ እርስዎ ያነበቡልን በጣም የተሳሳተ ታሪክ እንዲታረም ለመጠየቅ ነው እንጂ፣ በቀጥታ እርስዎን ለመዝለፍ አይደለም። እኔም ስለ ታሪክ ስናገር የተሳሳትኩት ነገር ካለ፣ ከማስረጃ ጋር የሚቀርብልኝን እርማት የምቀበል መሆኔን አረጋግጥልዎታለሁ።

ኢብራሂም ሡልጣን፣

..... ከኢትዮጵያ በኩል፣ ሁልጊዜ ስለ ኤርትራ የሚነገረው ታሪክ፣ በሙሉ የተሳሳተ ስለሆነ፣ እኛም አስፈላጊውን መልስ አዘጋጅተን እንሰጣለን።

ኢትዮጵያ፣

...... የነፃነት ግንባር «ብሎክ ኢንዲፔንደንቴ»(BLOCO INDIPENDENTE) የተባለው ፓርቲ ስሙ እንደሚያመለክተው፤ በጣልያንኛ አስተሳሰብና ቋንቋ የተመሠረተ ይመስላል። መቼ ኖርዋል የተቋቋመው?

ኢብራሂም ሡልጣን፣

..... ባለፈው ግንቦት ወር 1949 ዓ.ም በተካሄደው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ፣ ለኤርትራ ሕዝብ መጥፎ ጠንቅ ይሆን የነበረው የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት ሲፈርስ፣ ለስብሰባው የመጣነው የኤርትራ ልዩ ልዩ የፖለቲካ መሪዎች እዚሁ ኒውዮርክ ተሰብስበን፣ ለአገራችን ችግር በአንድ ሀሳብና በአንድ ዓላማ ለመቆምና ለመታገል እንድንችል፣ ይህንን «የነፃነት ግንባር ፓርቲ» አቋቋምን። ፓርቲው የኛ የኤርትራውያን ፓርቲ ነው። የጣልያን ፓርቲ ነው እያላችሁ ፕሮፓጋንዳ የምትነዙት እናንተ ብቻ ናችሁ።

ኢትዮጵያ፣

...... የተለያዩ የፖለቲካ አቋም የነበራችሁ ፓርቲዎች፣ የየአንዳንዳችሁን ሀሳብ ለተባበሩት መንግሥታት ለማቅረብ ኒውዮርክ ከመጣችሁ በኋላ፣ የወከላችሁን ሕዝብ ፈቃድ ሳትጠይቁ እንዴት በራሳችሁ ሥልጣን ልዩ ፓርቲ ማቋቋም ትችላላችሁ ?

ኢብራሂም ሡልጣን፣

...... ሕዝቡን በቴሌግራም ጠይቀን፣ እገሩ ውስጥ በሚታተሙትም ጋዜጦች ትክክለኛውን ሀሳባችንን እንዲረዳው ካደረግን በኋላ ነው ፓርቲው የተቋቋመው። ሕዝቡም ሙሉ በሙሉ መስማማቱን ገልጾልናል።

ኢትዮጵያ፣

..... በብዙ መቶ ሺህ ለሚቆጠሩ የፓርቲ አባሎቻችሁ ቴሌግራም የላካችሁትና መልሱም የመጣላችሁ፣ እዚሁ ኒውዮርክ በቆያችሁበት ጊዜ ነው ? ወይስ ከጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፐሪ ጋር ለመመካከር ሮም በስነበታችሁበት ሰሞን ነው ?

ኢብራሂም ሡልጣን፣

..... ከሕዝባችን ጋር እንዴት እንደምንገናኝ እናንተን አይመለከትም:: ዘጠና በመቶው የኤርትራ ሕዝብ ነፃነቱን እንድናስጠው ወኪሉ አድርጎ መርጦናል::እናንተ ማወቅ የሚገባችሁ ይህን ብቻ ነው::

በአዳራሹ ውስጥ፣

..... ሳቅ .......

ኢትዮጵያ፣

...... ይህ « የነፃነት ግንባር » ፓርቲያችሁ፣ ዛሬ ምን ያህል አባሎች አሉት ?

ኢብራሂም ሡልጣን፣

...... በትክክለኛው መዝገባችን ላይ የተመለከተው የጠቅላላው የአባሎቻችን ቁጥር፣ አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሠላሳ ስምንት ሺህ (1,338.000) ነው::

ኢትዮጵያ፣

..... የአባሎቻችሁ ተመዝጋቢዎች (1,338.000) አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሠላሳ ስምንት ሺህ ከሆነ፣ ጠቅላላው የኤርትራ ሕዝብ ምን ያህል ቢሆን ነው?

ኢብራሂም ሡልጣን፣

...... የሕዝቡን ቁጥር መስጠት ያለበት ያስተዳደሩን ሥልጣን የያዘው መንግሥት (እንግሊዝ) ነው:: እኛ እስታቲስቲክ ይዘን አልመጣንም::

ኢትዮጵያ፣

..... ባለፈው ግንቦት ወር፣ ለዚሁ ኮሚሲዮን እርስዎ ቀርበው በራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ፓርቲ ስም ሲናገሩ፣ የኤርትራ ሕዝብ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሀምሣ ሺህ (1,250.000) ነው ብለው ነበር::

ኢብራሂም ሡልጣን፣

....... ታዲያ ምን ከፋ ? .....

በአዳራሹ ውስጥ፣

...... ሳቅ .......

ኢትዮጵያ፣

...... የፓርቲያችሁ አባሎች ቁጥር ከጠቅላላው ሕዝብ ቁጥር በጣም በልጦ የተገኘው፣ መግለጫችሁን በሚያዘጋጁላችሁ ባለሙያዎች ስህተት ይሆን ?

ኢብራሂም ሡልጣን፣

...... እኛ ኤርትራውያኖች በአገራችን ጉዳይ፣ የውጭ እጅ አናስገባም:: ቁጥሩ የተሳሳተባችሁ እናንተ ናችሁ::

በአዳራሹ ውስጥ፣

..... ሳቅ .......

ኢትዮጵያ፣

...... ይህ አዲሱ ፓርቲያችሁ ከመፈጠሩ በፊት « የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ» ፓርቲ አባሎች ቁጥር ምን ያህል ነበር ?

ኢብራሂም ሡልጣን፣

..... በትክክለኛው ቁጥር፣ የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ፓርቲ አባሎች ሰባት መቶ ስልሣ ዘጠኝ ሺህ (769.000) ነበሩ::

ኢትዮጵያ፣

....... ባለፈው ግንቦት ወር፣ እርስዎ ለዚሁ ኮሚሲዮን ሲያስረዱ፣ የአባሎቹ ቁጥር፣ ዘጠኝ መቶ ሀያ አምስት ሺህ (925.000) ናቸው ብለው ነበር:: ዛሬ ሲነግሩን ከአንድ መቶ ሀምሣ ሺህ በላይ ቁጥሩ ቀንሶ የተገኘው፣ ሕዝቡ እናንተን ትቶ ወደ አንድነት ፓርቲ አምርቶባችሁ ይሆን ?

ኢብራሂም ሡልጣን፣

...... « አንድነት » ከተባለው እናንተ ከምትመሩት ፓርቲ፣ ሕዝቡ እየለቀቀ ወደ እኛ ዘንድ መጣ እንጂ ከእኛ ወደ እናንተ አልሄደም::

በአዳራሹ ውስጥ፣

....... ሳቅ ......

ኢትዮጵያ፣

...... አንግዲያውስ ቁጥሩ ለምን እንደተቀነሰ ማስረዳት ይኖርብዎታል::



ኢብራሂም ሡልጣን ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች ጋር፡

*« ...... ኤርትራ እና ኢትዮጵያ አይተዋወቁም። የኤርትራ ሕዝብ ዘጠና በመቶው እስላም ነው ...... »*

(ኒውዮርክ ጥቅምት 1949)
(ፎቶ U N)

ኢብራሂም ሡልጣን፣

...... ስታቲስቲኩን ሁሉ በቃል ማስታወስ ስለማይቻል ጥያቄዎቻችሁን በጽሑፍ ብታቀርቡልን እንመልስላችሁ ነበር:: ለማናቸውም ቁጥሩን ከአንዱ ወደ አንዱ የምታማቱት እናንተ ናችሁ::

<u>በአዳራሹ ውስጥ፣</u>

....... ሳቅ .......

ኢትዮጵያ፣

....... ኤርትራ ነፃ መንግሥት ሆና ለመቋቋም የተማሩ ሰዎች እንደሚያስፈልጓት እርስዎም ያምናሉ:: አሁን **ምን ያህል** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የፈጸሙ ኤርትራውያኖች አሉ ?

<u>ኢብራሂም ሡልጣን፣</u>

...... **ኤርትራ** ያሏት የተማሩ ሰዎች ሁሉ **ነፃነታችን ስላልተገኘ** ለባዕድ አገሮች በማገልገል ላይ ይገኛሉ:: የእናንተ **መንግሥት ደጋግሞ** እንደተናገረው፣ በአስተዳደራችሁ ሥልጣን ላይ **ያሉት** እንድ ሸህ ስድስት መቶ ኤርትራውያኖች (1.600) **ኤርትራ ነፃ ስትወጣ** ወደ አገራቸው ይመለሳሉ::

<u>የላይቤሪያ መልዕክተኛ</u> ጥያቄ፣

..... ባለፈው ስብሰባ ላይ በሰጡት መግለጫ፣ **የኢትዮጵያ** መንግሥት በሥልጣን ላይ ካስማራቸው ኤርትራውያን **ውስጥ**፣ አንድም እስላም የለም ብለው አውግዘው ነበር:: አሁን **ደግሞ ኤርትራ** ነፃ ስትወጣ እነዚህ ኤርትራውያኖች ከኢትዮጵያ ለቅቀው አገራ**ቸውን ለማገልገል** ይመጣሉ ብለዋል:: እዚህ ላይ በሀይማኖት ምክንያት **አዝሎበት** የነበረውን ጉዳይ፣ አሁን ካቀረቡት ሀሳብ ጋር እንዴት አድርገው ያስታርቁታል ?

ኢብራሂም ሡልጣን፣

...... እኛ የተናገርነው ያሉን የተማሩ ኤርትራ**ውያኖች** እንኳንስ ለአገራቸው ለኤርትራ ቀርቶ ለኢትዮጵያም አስተዳደር የተረፉ **መሆናቸውን** ለማስረዳት ነው:: ሌላው ቢቀር አሁን በዚህ አዳራሽ ውስጥ **የኢትዮጵያ** መልዕክተኞች ሆነው የተደረደሩት፣ ዘጠና ዘጠኝ በመቶው ኤርትራ**ውያን መሆናቸውን** ማየት በቂ ማስረጃ ነው:: እኛ በአዲሱ ፓርቲያችን ዓላማ **ኤርትራውያን**ነታቸውን ካረጋገጡ፡ ክርስቲያኖች ናቸው ብለን አናርቃቸውም:: በ**ፓርቲያችን** ውስጥ ጥቂቶች ይሁኑ እንጂ፣ ክርስቲያኖችም አሉ::

ኢትዮጵያ፣

...... በኢትዮጵያ መንግሥት ውስጥ ለከፍተኛ ኃላፊነት የተመደቡት የኤርትራ ተወላጆች ለኢትዮጵያዊነታቸው ጥያቄ ስለሌለው፣ እነሱ እናንተን ተከትለው ያገራቸውን መሠረታዊ ታሪክ እንደማይለውጡ ማወቅ አለባችሁ::

<u>ኢብራሂም ሡልጣን፣</u>

..... ይህን የምትሉት እናንተ ናችሁ:: <u>እነሱ ግን በኤርትራ ነፃነት ጉዳይ፣ ልባቸው ከእኛው ጋር ነው::</u>

<u>የፓኪስታን መልዕክተኛ፣</u>

..... ለፓርቲ መሪዎች ጥያቄ በማቅረብ ፋንታ ንትርክ መፍጠር የኮሚሲዮኑን የሥራ ጊዜ ማባከን ነው::

<u>የኮሚሲዮኑ ሊቀመንበር፣</u>

...... የሚደረጉት ጥያቄና መልሶች በተቻለ መጠን አጫጭር እንዲሆኑ እጠይቃለሁ::

<u>ኢትዮጵያ፣</u>

...... ለግራዝማች ኢብራሂም ሡልጣን አንድ የመጨረሻ ጥያቄ ማቅረብ እፈልጋለሁ:: በዛሬው ሰዓት በኤርትራ ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የጨረሱ ስንት ሰዎች አሉ ? መቼም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የተማሩ አሉ ወይ ? ብዬ አልጠይቅም::

<u>ኢብራሂም ሡልጣን፣</u>

..... ኢትዮጵያ ራሷ ነፃ መንግሥት የሆነች፣ በአገሯ ውስጥ አንድም ዩኒቨርሲቲ የላትም:: እንግዲህ ነፃ የተባለችው ኢትዮጵያ የሌላትን፣ በኮሎኒ አስተዳደር ተጨቁና የኖረች ኤርትራ እንዴት ዩኒቨርሲቲ ሊኖራት ይችላል ?

<u>ኢትዮጵያ፣</u>

..... የኔ ጥያቄ ስለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ነው::

<u>ኢብራሂም ሡልጣን፣</u>

(በግልፍታ) ...... ኤርትራ ኮሎኒ ሆና ተጨቁና የተገዛ አገር ስለሆነ፣ የለም ..... የለም ..... ብያለሁ::

<u>ኢትዮጵያ፣</u>

...... ይበቃኛል መልሱን አግኝቻለሁ:: ጣልያን የኤርትራን ሕዝብ ለሃምሣ ዓመታት ጨቁኖ ሲገዛ፣ ኤርትራውያኖች በገዛ አገራቸው ከአራተኛ ክፍል በላይ እንዲማሩ አይፈቀድላቸውም ነበር:: <u>ግራዝማች ኢብራሂም ! እርስዎ ራስዎ ትምህርት ሳያገኙ ጊዜው ያለፈብዎ በግፈኛው የጣልያን አስተዳደር ምክንያት ነው::</u> ጣልያን ይህን ሕዝብ ምን ያህል እንደጐዳው ሁላችንም ደህና አድርገን እናውቃለን:: ዛሬም ቢሆን ጣልያን የኤርትራን ዕድል ለማሰናከል ከመጣር አላረፈም:: እኛ ኢትዮጵያውያን ጣልያንን እስከ መጨረሻው ለመቋቋም ተዘጋጅተናል:: የኤርትራም ሕዝብ ከእኛ ጋር ነው:: የምናዝነው፣ አንዳንድ በገንዘብ ተገዝተው የኤርትራን ጥቅም ለመሸጥ የሚጥሩ በመኖራቸው ብቻ ነው::

<u>የኮሚሲዮኑ ሊቀመንበር፣</u>

...... የኢትዮጵያ መልዕክተኛ! ቀደም ሲል ለጥያቄዬ መልሱን አግኝቻለሁ ስላሉ፣ ንግግርዎን እዚሁ ላይ እንዲያቆሙልን እጠይቃለሁ ..... »

-- ድንቁርና ለድፍረት፣ ፍቅረ ንዋይ ለክህደት፣ ይመቻል እንደተባለው፣ ኢብራሂም ሡልጣን በጣልያኖች ሊሬ ተሸዋንሙኖ፣ የኤርትራን መሠረታዊ ታሪክ ከኢትዮጵያ ነጥሎ፣ የዓረቦች ተገዥ የነበረች አድርጐ ሲያቀርባት ሕሊናው አልወቀሰውም።

-- የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ምንም ዓይነት የባሕል ሆነ የታሪክ ግንኙነት የሌላቸው፣ የማይተዋወቁ ባዕዶች ናቸው ብሎ ሲናገር አላፈረም። ከሶስት ዓመት በፊት ግን የኤርትራና-ያኢትዮጵያ አንድነት አባል ሆኖ ለኢትዮጵያዊነት ሲጨፍር እንደነበረ ትዝ አላለውም።

-- በኮሎኒው ዘመን በቅን ያገለገለ ነው ብለው፣ ገዥዎቹ የግራዝማችነት ማዕረግ የሰጡት፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚያከብሩት ባሕልና ወግ መሠረት መሆኑን ኢብራሂም ሡልጣን አላሰበውም።

-- በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጉባኤ ላይ ቀርቦ፣ ጣልያኖች ያዘጋጁለትን ዲስኩር ሲናገር፣ ደህና አድርጐ ለማንበብ መጣሩን ነው እንጂ፣ ከኢትዮጵያና ከሌሎቹም መልዕክተኞች፣ ጥያቄዎች እየጐረፉለት መልሱ እንደሚያስጨንቀው ጨርሶ አልጠበቀም።

በአባሲዶች ዘመን በባግዳዱ ካሊፋ አመራር ሥር የነበረችው ኤርትራ፣ በዚያን ዘመን ስሟ ማን ይባል እንደነበረ፣ እንዲሁም ከካሊፋው ሥልጣን መበታተንም በኋላ፣ የኤርትራን ግዛት በከፊል ይመራ የነበረው እስላሙ ኤርትራዊ ስሙ ማን እንደሚባል፤ ኢብራሂም ሡልጣን እጠየቃለሁ ብሎ አላሰበም። ይህንን የፈጠራውን ታሪክ ያዘጋጁለት የፋሽስት ሊቃውንቶች እነ ኤንሪኮ ቸሩሊ፣ ለመስቀልኛ ጥያቄዎች የሚያገለግሉትን መልሶች፣ አዘጋጅተውለት ቢሆን ኖሮ፤ ኢብራሂም፣ ባለው የተፈጥሮ የማጭበርበር ብልሀት፣ ጥያቄዎቹን በፍጥነት እየተቀበለ ወዲያውኑ ይመልስ ነበር። ሌላው ደግሞ በኢብራሂም ሡልጣን ላይ የወደቀው ችግር፣ ባለፈው ግንቦት ወር በስስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ የሰጠውን ዝርዝር መግለጫ አለማስታወሱ ነው። በዚያን ጊዜ የኤርትራ ሕዝብ በጠቅላላው አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሀምሣ ሺህ (1,250.000) መሆኑንና፣ ከዚህም ውስጥ ዘጠኝ መቶ ሀያ አምስት ሺህ (925.000) የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ፓርቲ አባሎች ናቸው ብሎ፤ ለዚሁ ዋና ኮሚሲዮን የተናገረው ቃል እንደሚመዘገብ አላወቀም። ኢብራሂም ሡልጣን ይህንን ስታቲስቲክ ካቀረበ በኋላ፣ በጣልያን ገንዘብ የተቋቋመው «የነፃነት ግንባር» ፓርቲ፣ አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሠላሣ ስምንት ሺህ (1,338.000) የተመዘገቡ አባሎች መኖራቸውን ሲናገር፣ ከጠቅላላው የኤርትራ ሕዝብ ቁጥር በልጠው መገኘታቸው አልታየውም።

በስስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ላይ፣ በራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ስም፣ አሁን ደግሞ በአራተኛው ጉባኤ በነፃነት ግንባር ስም ሲናገር ያዳመጡት ብዙዎቹ መልዕክተኞች፤ ሡልጣን እሊ፣ እንኳንስ ዘጠና በመቶውን የኤርትራ ሕዝብ ይቅርና፣ ራሱንም ቢሆን በትክክል የሚወክል አለመሆኑን ከተረዱለት በኋላ፣ ከኮሚሲዮኑ ሊቀመንበር ተስናብቶ ከስብሰባው አዳራሽ ወጥቷል።




የኢትዮጵያ መልዕክተኞች በከፊል፣

ከግራ ወደ ቀኝ፤ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የመልዕክተኞች መሪ፤
ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን -- መልዕክተኛ
አቶ ገብረመስቀል ክፍለእግዚእ -- መልዕክተኛ

(OCT. 1949)
(ፎቶ U.N)

## የኢብራሂም ሡልጣን የፖለቲካ ታሪክ

1. በ1941 ዓ.ም የማህበረ ፍቅሪ ሀገር ተመሥርቶ ክርስቲያኑም ሆነ እስላሙ «ኢትዮጵያ ወይ ሞት» እያለ አንድነቱን ሲያስተባብር፣ ኢብራሂም ከመጀመሪያዎቹ አባሎች አንዱ የነበረና፤ የማህበሩን ዕድገት ለመግፋት ከሚጥሩት መካከል ሲሮጥ የታየ ሰው ነበር።

2. የ «ፍቅሪ ሀገር» አንድነት ማህበር መስፋፋትና መደርጀት እንግሊዞችን ስለአስጋቻው፣ የማህበሩን እርምጃ ለማዳከም የተቃዋሚ ፓርቲ ሲያዘጋጁ፣ ኢብራሂም ሡልጣን የተሻለ ጥቅም አገኛለሁ ብሎ ጥሩ መሣሪያ ለመሆን ቀረበላቸው።

3. የአንድነቶችን ማህበር ለመቃወም የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ (MOSLEM LEAGUE) ፓርቲ የተቋቋመው፣ ምንም እንኳን በታወቁትና እጅግ በተከበሩት የእስላም ሀይማኖት መሪ በሰይድ አቡበከር ኤልሞርጋኒ ሊቀመንበርነት ቢሆንም፣ በእንግሊዞች ድጋፍ ኢብራሂም ሡልጣን የፓርቲው ዋና ጸሐፊ ሆነ።

4. የአንድነቶች ማህበር አባል ሆኖ ለኢትዮጵያዊነት ካልሞትኩ ብሎ ይጋበዝ የነበረው ኢብራሂም ሡልጣን፣ በአንድ ጊዜ ተለውጦ፣ ..... <u>ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ዓይነት የዘር ሆነ የባሕል፣ የታሪክ ሆነ የአስተዳደር ግንኙነት ኖሯት አያውቅም</u> ..... ብሎ ካደ። ...... በራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ፓርቲ ስም፣ ስለ ኤርትራ የወደፊት ዕድል ሲናገር፣ ...... ኤርትራ ከነፃነት በፊት ከአሥር እስከ አሥራ አምስት ዓመት ድረስ በታላቋ ብሪታንያ መንግሥት አስተዳደር መሠልጠንና መዘጋጀት አለባት ..... ሲል እንግሊዞችን ለማስደሰት ሞክሮ ነበር።

5. በ1949 ዓ.ም እንግሊዞች፣ ከኤርትራ ግዛት የምዕራባዊው ቆላ ወደ ሱዳን እንዲቀላቀል የምሥራቁና የደጋው ክፍል ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀድ መፍትሔ ሲያሰናዱ፣ ኢብራሂም ሡልጣን በመጀመሪያ በዚህ ሀሳብ ከእንግሊዞች ጋር መቆም ጀመረ። እያደር ሲያየው ጥቅም የማይሰጠው ሲመስለው፣ እንግሊዞቹን ትቶ ወደ ጣልያኖች ተዛወረ።

6. የኤርትራ ግዛት መከፋፈል የለበትም። ለኤርትራ መፍትሔው ነፃነትን መስጠት ነው። አገሩ ነፃነትን ለመቀበል አልደረሰም ከተባለ፣ የተባበሩት መንግሥታት በሚወስነው የሞግዚት አስተዳደር እንዲደረግልን እንጠይቃለን ሲል በራቢጣ ኤል ኢሥላሚያ ፓርቲ ስም ለሶስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ አመለከተ። ...... ኢብራሂም ሡልጣን ይህንን ሀሳብ የወረወረው፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጣልያን ኤርትራን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድር ይመደባል በሚል ተስፋ ነበር።

7. የሞግዚት አስተዳዳሪ ለመሆን ጣልያን ምንም ዓይነት ዕድል የሌላት መሆኑ ሲታወቅ በሮማ መንግሥት ገንዘብ "BLOCCO INDIPENDENTE ERITREO" የተባለ የነፃነት ጠያቂዎች ግንባር ተቋቋመ። ኢብራሂም ሡልጣን የዚህ አዲስ ፓርቲ ዋና ጸሐፊ ሆኖ በጥቅምት 1949 ዓ.ም በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ላይ ለኤርትራ አሁኑኑ ነፃነት እንዲሰጥ ጠየቀ።

8. የነፃነት ግንባር ፓርቲ በጣልያን ገንዘብ መቋቋሙንና ግቡም ለጣልያን ጥቅም መሆኑን ሕዝቡ እየተረዳው ሲሄድ፣ ኢብራሂም ሡልጣንና ወገኖቹ ብዙ

ተቃዋሚዎች ገጠሟቸው:: በሼህ ጊዜ ራዳይ የሚመራው የምዕራቡ አውራጃ የእስላሞች ማህበር እና፣ በመሐመድ ዑመር ቃዲ ምፅዋ ላይ የተደራጀው የምሥራቅ እስላሞች ድርጅት፣ የኢብራሂም ሡልጣንን የነፃነት ግንባር ፓርቲ ባዶ ቀፎ እንዲሆን አደረጉት።

9. በታህሣሥ 1950 ዓ.ም ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከወሰነ በኋላ፣ የፌዴሬሽኑ ሕገ መንግሥት በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ ኢብራሂም ሡልጣን እንግሊዞችን ተለማምጦ የሕገ መንግሥት አደራጅ ምክር ቤት (CONSTITUENCY ASSEMBLY) አባል ሆኖ ተመረጠ።

10. ዘላኑ ፖለቲከኛ ኢብራሂም ሡልጣን፣ ከአንድነት ማህበር ወደ ራቢጣ ከራቢጣ ወደ ነፃነት ግንባር፣ አንድ ጊዜ ለእንግሊዞች፣ ሌላ ጊዜ ለጣልያኖች፣ ሲያሸረግድ ከኖረ በኋላ፣ በመጨረሻም አንዱም ሳይሳካለት ባዶ እጁን ቀረ። በ1956 ዓ.ም በአስፍሐ መንግሥት ጊዜ በተደረገው የሁለተኛው የኤርትራ ፓርላማ ምርጫ ኢብራሂም ሡልጣን የሚመርጠው አጥቶ፣ በኤርትራ ውስጥ የፖለቲካ ሕይወቱ ማክተሚያ ሆነ።

## ሕዝቡ የጠየቀው ኢትዮጵያዊነት ነው

### ተድላ ባይሩ

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት « የኤርትራ የነፃነት ግንባር » ተብሎ በጣልያን የተቋቋመው ድርጅት ወኪል፣ ያደረገውን ስፊ ዲስኩር ካዳመጠ ከሶስት ቀናት በኋላ፣ ጥቅምት 10 ቀን 1949 ዓ.ም የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ ዋና ጸሐፊ የሚሰጡትን መግለጫ ለመስማት ወሰነ።

አቶ ተድላ ባይሩ በንግግራቸው መግቢያ ላይ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በኤርትራ ጉዳይ የአብዛኛውን ሕዝብ ፍላጐትና ጥያቄ፣ የአገሩን መሠረታዊ ታሪክና የኤኮኖሚ ሕይወት በሚገባ ተመልክቶ፣ በዴሞክራሲ ሥርዓት ትክክለኛ ፍርድ እንደሚሰጥ፣ ያላቸውን ጽኑ ተስፋ አስቀድመዋል። የአንድነት ፓርቲ ዋና ጸሐፊ ከዚሁ አያይዘው የሰጡት መግለጫ፣ ኤርትራ በኮሎኒያሊስት ጣልያን ከመያዟ በፊት የኢትዮጵያ አካል የነበረች አገር መሆንዋን ታሪኩን ተንትነው በማስረዳት ነበር። ቀጥሎም እነ ኢብራሂም ሡልጣን የሮማ መንግሥት መሣሪያ በመሆን፣ የኤርትራ እውነተኛ ታሪኳ ተደምስሶ በአዲስ የፈጠራ ታሪክ እንዲለወጥ፣ የኤርትራ ሕዝብ ፍላጐት ተሰርዞ፣ የጣልያን ምኞት እንዲፈጸም የሚያደርጉትን ጥረት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንዲገነዘበው አጥብቀው ጠይቀዋል። ተድላ ባይሩ፣ በረዥሙ ከገለጿቸው ሀሳቦች ዋና ዋናዎቹ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው።

1. ...... በጨካኝነቱና በግፈኛነቱ አጅግ በታወቀው በጣልያን ኮሎኒ አስተዳደር ለሃምሣ ዓመታት ሲሰቃይ የኖረው የኤርትራ ሕዝብ፣ ነፃነቱንና ሠላሙን የሚያገኘው ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር ሲቀላቀል ብቻ ነው። ....... ይህ አስተያየት የአብዛኛውን የኤርትራን ሕዝብ ስሜትና ፍላጐት የሚገልጽ መሆኑን፣

የኃያላን መንግሥታቶች መርማሪ ኮሚሽን በስጠው ራፖር የተነገረ ስለሆነ፣ ዝርዝሩ ውስጥ በመግባት ጊዜያችሁን አልወስድም::

2. ...... በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዘመን፣ የፋሽስትን ሥልጣን ከምሥራቅ አፍሪካ ለማባረር፣ የታላቋ ብሪታንያ ጦር በአገራችን ላይ ውጊያውን ባካሄደ ጊዜ፣ ሠላም ሲመለስ « ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ትቀላቀላለች » ብሎ የሰጠውን ቃል ሕዝባችን በጋለ መንፈስ ተቀብሎ፣ ከእንግሊዝ ጦር ሠራዊት ጋር በመሰለፍ የተጠየቀውን በሚገባ ፈጽሟል:: ...... ቀጥሎም የኢትዮጵያ ነፃነት በተመለሰበት ዕለት፣ እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም (5/05/41) ይህ የአገር ፍቅር አንድነት ማህበራችን አሥመራ ላይ ተመሠረተ::

3. ..... የድርጅታችን ዋና ዓላማ፣ ከቅኝ ግዛት ጭቁና ነፃ ሆነን በዘራችንና በባሕላችን፤ በቋንቋችንና በማህበራዊ ኑሮአችን፣ አንድ ዓይነት ባሕርይና አንድ ዓይነት ታሪክ ካለን፤ ከጥንታዊት አገራችን ከኢትዮጵያ ጋር ለመዋሀድ የተመሠረተ ነው:: ...... አሁን ያሉን ሰባት መቶ ሺህ (700.000) የሚሆኑት አባሎቻችን፣ ጠላቶቻችን እንደሚያስወሩት ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ፣ ወንድሞቻችን እስላሞችም በብዛት መኖራቸውን ማረጋገጥ እንወዳለን:: ...... ለምሣሌም ያህል፣ ከእስላሞች ወንድሞቻችን መካከል፣ ዛሬ ተቃዋሚያችን ሆኖ ከጠላታችን ከጣልያን ጋር የተሰለፈው ኢብራሂም ሡልጣን፣ ከ1941 እስከ 1946 ዓ.ም ድረስ የአንድነት ፓርቲያችን አባል ሆኖ፣ ከፍ ያለ ጥረት ያደረገ የነበረ ሰው መሆኑን ሳንጠቅሰው አናልፍም::

4. ..... የአንድነት ማህበራችን ታጋይ የነበረው ደጃች ኢብራሂም ሡልጣን፣ ባለፈው ግንቦት ወር በዚሁ የስብሰባ አዳራሽ፣ በራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ፓርቲ ስም በሰጠው መግለጫ፣ ለኤርትራ ሕዝብ ከነፃነት በፊት ሞግዚት አስተዳዳሪ እንደሚያስፈልገው ማመልከቱ ይታወሳል:: ኢብራሂም፣ በዚያን ጊዜ ይህን ሀሳብ ያቀረበው ሞግዚት አስተዳዳሪው ጣልያን ሊሆን ይችላል በሚል ተስፋ ነበር::

5. ..... የጣልያን መንግሥት፤ ሞግዚት ሆኖ በሥልጣን ወደ ኤርትራ እንደማይመለስ ሲያውቀው፤ እነ ኢብራሂም ሡልጣንን በገንዘብ በመደለል፤ ኤርትራ ነፃ መንግሥት መሆን አለባት የሚል አዲስ የማታለያ ዕቅድ ዘረጋ:: ይህንንም ሀሳብ ለማስፈጸም በኤርትራ ምድር ሳይሆን፣ በኒውዮርክ ከተማ « የነፃነት ጠያቂዎች ግንባር » የሚል ፓርቲ በጥድፊያ አቋቁሞ፣ ሕዝቡ የማያውቀውንና ያልሰማውን ሀሳብ፣ በፕሮፓጋንዳ በማሰራጨት ላይ ይገኛል:: ስለዚህ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መጠንቀቅና በጥልቅ መገንዘብ ያለበት፣ ይህ « የነፃነት ግንባር » የተባለ ፓርቲ የኤርትራ ሕዝብ ያልተካፈለበትና ፍጹም ጣልያናዊ ድርጅት መሆኑን ነው:: የጣልያን መንግሥት ዋና ዓላማ፣ ኤርትራ ወደ እናት አገሯ ወደ ኢትዮጵያ እንዳትመለስ ለማገድና፣ የተባበሩት መንግሥታትን አጭበርብሮ የነፃነት መፍትሔ በማስወሰን፤ አሥመራ በሚኖሩት ዜጎቹ አማካይነት የአስተዳደሩን ሥልጣን በእጁ ይዞ የፈለገውን ለማድረግ ነው::

6. ...... የኤርትራ ሕዝብ ግን፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዴሞክራሲ አሠራርና ትክክለኛ ፍርድ ስለሚያምን፣ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል እንዲችል፣ ያቀረበው አቤቱታ ጊዜ ሳይወስድ እንዲፈጸምለት በሙሉ ተስፋ ይጠብቃል:: ...... »

አቶ ተድላ ባይሩ፣ በረዥሙ ያደረጉት ንግግር፣ መሠረት የጨበጠና የኤርትራን ጉዳይ በትክክል የሚያብራራ ስለነበረ፤ በኮሚሲዮኑ ገበታ ላይ የተሰገሰጉት የጣልያን ነገረ ፈጆች፣ የመስቀልኛ ጥያቄ እያደራረቡ ለማምታታት ዕድል አላገኙም። ከሮማ መንግሥት ከባድ አደራ የተጣለባቸው እነ አምባሳደር ሆሲ አርሲ፣ ከአንድነት ፓርቲ መሪ የተሰጠውን መግለጫ ለማራከስ ዘዴ እጥተው በሚጨነቁበት ሰዓት፣ የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዛፍሩላህ ካን፣ እንደ ምንም ብሎ አንድ ጥያቄ አቀረበ።

ጥያቄ፣
(ዛፍሩላህ ካን)

..... ለኤርትራ ነፃነት የሚጠይቀው « የነፃነት ግንባር ፓርቲ » እና ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል አለብን የሚለው የናንተ ፓርቲ፣ የሰጣችሁንን መግለጫዎች አዳምጠናል። ሁላችሁም የአብዛኛውን የኤርትራን ሕዝብ እንወክላለን ትሉናላችሁ። ..... የተባበሩት መንግሥታት የአብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ተወካይ የሆነው ፓርቲ የትኛው እንደሆነ፣ እንዴት ማረጋገጥ ይችላል ? ......

መልስ፣
(ተድላ ባይሩ)

...... የአብዛኛውን ኤርትራ ሕዝብ የሚወክለው ፓርቲ የትኛው እንደሆነ ለመለየት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፓርቲዎች መሪዎች በሚያደርጉት ዲስኩሮች ላይ መመዘን ይችላል ብለን እኛም አንጠብቅም። በእኛ አስተያየት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለም ሠላም ዳኛ ስለሆነ፣ የሚቀርብለትን በሚገባ ለመዳኘት፣ ማስረጃዎቹን መርምሮ የሚለይበት የአሠራር ዘዴ ሊኖረው ይገባል ብለን እናስባለን። ከተቋቋመ ስምንት ዓመት የሆነው የአንድነት ፓርቲያችን፤ የአብዛኛውን የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎት የያዘ ሆኑን፣ በአራቱ ኃያላን ኮሚሽን ተመርምሮ ውጤቱ ቀርቧል። ባለፈው ግንቦት ወር፣ የሶስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤም፣ ከምዕራባዊው ቆላ በስተቀር ሌላው የኤርትራ ግዛት በሙሉ፣ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል ከፍተኛ የድጋፍ ድምፅ ሰጥቶ የነበረው አለምክንያት አይደለም። አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር ለመዋሀድ የሚፈልግ መሆኑ ስለተረጋገጠ ነው።

... ዛሬ በድንገት ተነስቶ አብዛኛውን የኤርትራ ሕዝብ እወክላለሁ ብሎ የሚፎክረው ይህ « የነፃነት ግንባር » የተባለ ድርጅት፣ መቼ እንደተፈጠረ፣ የት ከተማ ወይም ቦታ ላይ እንደተመሠረተ፣ ለማን መሣሪያ ሆኖ እንደሚጥር፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሚገባ ለመረዳት ይቸገራል ብለን እናምንም። በተጨማሪም የእኛ ያገር ፍቅር አንድነት ድርጅታችን፣ እጅግ አብዛኛው የሆነውን የኤርትራን ሕዝብ እንደምንወክል ለመገንዘብ የሚያስቸግር ነገር የለም። ...... »

አቶ ተድላ ባይሩ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ መዋሃድ የአብዛኛው ሕዝብ ጽኑ ፍላጎት መሆኑን ለማሳመን የሰጡት መልስ፣ የኢትዮጵያ ጠላት የሆነውን የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ጥያቄዎቹን ከማንዛዛት እንዲገታ አድርገውታል። የአንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ መግለጫቸውን ከፈጸሙ በኋላ፣ ከዛፍሩላህ ካን በስተቀር፣ ከሌሎቹ ከላቲን አሜሪካ አገሮች ሆነ ከዓረቦቹ፣ እንዳችም ተጨማሪ ጥያቄ ሳይቀርብላቸው የጉባኤውን ሊቀመንበር ተሰናብተው ወጡ።

ከሰስት ቀናት በፊት የኤርትራ ነፃነት ጠያቂ ኢብራሂም ሡልጣን ቀርቦ በተናገረበት ጊዜ፣ ከኢትዮጵያ መልክተኞች ጋር በገጠመዉ ክርክር የኮሚሲዮኑ አጻራሽ በሳቅ ግሎ እንደነበረ ይታወሳልዕሠ:: በተድላ ቤይሩ ፕሮግራም ላይ ግን እጅግ ጸጥ ያለ መንፈስ ይታይ ነበር::

# ንዑስ ኮሚቴ «17»

ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች የቀረቡትን ልዩ ልዩ መፍትሔዎች አጥንቶ፣ ለዋናው ኮሚሲዮን ረቂቅ ውሳኔ እንዲያዘጋጅ የተቋቋመው « ንዑስ ኮሚቴ 17 » ሥራውን ሲጀምር፣ መጀመሪያ የሊቢያን፣ ቀጥሎ የሱማሌን፣ በመጨረሻ የኤርትራን ጉዳይ ለማየት ፕሮግራሙን አወጣ:: ባለፈው ግንቦት ወር በተካሄደው የሰስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ በከፍተኛ ድምፅ ብልጫ ተደግፎ የመጨረሻውን ውሳኔ የሚጠብቀው የኤርትራ ጉዳይ ስለሆነ፣ ከሊቢያና ከሱማሌ ዶሴዎች በፊት እንዲታይ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ያደረጉት ሙከራ ደጋፊዎች በማጣት ሳይሳካ ቀረ:: ይህ ንዑስ ኮሚቴ 17 ተቋቁሞ አባሎቹ በተመረጡ ጊዜ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በብስጭት መንፈስ « የጣልያን ኮሚቴ » ብለው የሰየሙት አለአግባብ አልነበረም:: የንዑስ ኮሚቴው አባሎች ከሆኑት ውስጥ፣ ኢትዮጵያን ይደግፋሉ የሚባሉት አሜሪካና ታላቋ ብሪታንያ፣ ላይቤሪያና ዴንማርክ፣ በድምሩ አራት አገሮች ብቻ ናቸው::

-- ዓረቦቹ ኢትዮጵያን ለመደገፍ ባለፈው ግንቦት ወር የሰጡትን ቃል፣ በዚህ በመስከረሙ ጉባኤ ወደ ጣልያን ስለአዛወሩት፣ ሒሳቸው አስጨንቋቸው ወደ ኢትዮጵያ ይመለሳሉ ተብሎ ተሰፋ አልተደረገም:: -- ሕንዶች፣ ምንም እንኳ እንደ ፓኪስታኑ የጣልያን « ካቫሊየሬ » (ፈረሰኛ) ሆነው ባይሰለፉም፣ ኢትዮጵያ ተበደለች ብለው ይሚገቱ ይሆናል የሚል ግምት አልተሰጠም:: -- ፈረንሣይ ለጣልያን ጥቅም ከመቆም ይልቅ ኢትዮጵያን ትረዳለች ተብሎ አይጠበቅም:: -- ደቡብ አፍሪካ በዘር ልዩነት ፖሊሲ የታወቀ ገፊኛ መንግሥት ስለሆነ፣ ለጣልያን ደጋፊ እንደሚሆን አላጠራጠረም:: -- የሶቪየት ሕብረት፣ ፖላንድና ቼኮዝሎቫኪያን አስከትሉ እሱ ራሱ ካቀረበው ሀሳብ በስተቀር ኢትዮጵያን ለመርዳት ይሞክራል ተብሎ አልታሰበም::

እንግዲህ የተመረጡት የ « ንዑስ ኮሚቴ 17 » አባሎች አቋም ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ስለሆነ፣ በአርጀንቲና አማካይነት የሚቀርበውን የጣልያንን ረቂቅ ውሳኔ የሚቃወሙት፣ ኢትዮጵያና አራቱ ደጋፊዎቿ፣ ከሰስቱ ማርክሲስቶች ጋር ሲደመሩ ስምንት አገሮች ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው:: በዚህ አኳኋን ከሃያ አንዱ አባሎች መካከል ቀሪዎቹ አስራ ሰስቱ አገሮች የሚደግፉት መፍትሔ፣ የሮማን መንግሥት የሚያረካ እንደሚሆን ስለሚጠበቅ፣ ኢትዮጵያ ከዚህ ከጣልያን ኮሚቴ ፍርድ እንደማታገኝ ገና ከጠዋቱ አውቃዋለች:: ጥቅምት 11 ቀን 1949 ዓ.ም «ንዑስ ኮሚቴ 17» ሥራውን ሲጀምር፣ በመሰብሰቢያው ጠረጴዛ ላይ የቀረቡት ሰስት ዓይነት ረቂቅ መፍትሔዎች ነበሩ::

<u>የመጀመሪያው</u>፤
ሊቢያ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ነፃ እንድትወጣ፤ ሱማሌ ለነፃነት ብቁ እስከትሆን ድረስ በጣልያን ሞግዚትነት እንድትቆይ፤ ኤርትራ ግን ከምዕራቡ አውራጃዎች በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሃዱ፤ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ተደጋግሞ የቀረበው መፍትሔ ነው።

<u>ሁለተኛው</u>፤
ሊቢያ አሁኑኑ ነፃነቷ እንዲሰጣት፤ ኤርትራና ሱማሌ ግን መስኮብ አባል በሆነበት በተባበሩት መንግሥታት በሞግዚትነት፣ ለአምስት ዓመታት እንዲቆዩ ከሶቪየት ሕብረት የቀረበው ሀሳብ ነው።

<u>ሰስተኛው</u>፤
የሮማ መንግሥት ሀሳቡን ነድፎ በታወቀው ወኪሉ በአርጀንቲና አማካይነት የቀረበው መፍትሔ፤ ሱማሌ ለጣልያን ተመልሳ፣ ሊቢያና ኤርትራ አሁኑኑ ነፃነታቸውን ይቀበሉ የሚለው ነው።

ከነዚህ ከቀረቡት ሰስት ረቂቅ ውሳኔዎች ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰው የሶቪየት ሕብረት ሀሳብ፤ ከፖላንድና ከቼኮዝሎቫኪያ በስተቀር ማንም ስለማይደግፈው፤ ንግግር ሳይደረግበት ከአጀንዳው እንዲሠረዝ ተደረገ። አርጀንቲና እና ፓኪስታን፣ ጣልያን የቀየሰላቸውን መንገድ በመከተል፣ ለዳኝነት ከመመረጣቸው በፊት ፍርዳቸውን በቅድሚያ ያዘጋጁ ስለሆኑ፣ ምንም ዓይነት እንቅፋት ሳይገጥማቸው፤ ሀ/ ሊቢያ ከሁለት ዓመት በኋላ ነፃነቷን እንድትቀበል፣ ለ/ ሱማሌ ለሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ጣልያን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድራት፤ አስፈላጊውን ሁለት ሰስተኛ ድምፅ አሰባስበው ረቂቁን ውሳኔ አሳለፉ። ወዲያው፤ በታላቋ ብሪታንያ እና በአሜሪካ ተደግፎ በድጋሚ የቀረበው የኤርትራ ጉዳይ ሲጀመር፣ የጣልያን ሠልፈኞች ነፃነት ..... ነፃነት ..... በሚል ቃል ድምፃቸውን ማስተጋባት ጀመሩ።

በዚህ በንዑስ ኮሚቴ 17 ላይ፣ ኢትዮጵያን የወከሉት ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን፣ እነ አርጀንቲና በሚያዘጋጁት የተሳሳተ ውሳኔ የተሰማቸውን ሀዘንና ቅሬታ ለኮሚቴው አባሎች ገለጹ። « ...... ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ እንዳትቀላቀል መንገዱን ዘግታችሁ፣ ጣልያን ሱማሌን መልሶ እንዲይዝ የምታቀርቡት ውሳኔ፣ በቀጥታ በኢትዮጵያ ሕይወት ላይ አደጋ መጣል መሆኑ አይታያችሁም ወይ ? ...... ጣልያን ኢትዮጵያን ወግቶ በሕዝቧ ላይ ያንን ሁሉ ዕልቂት ለማድረስ የቻለው፤ የጦሩን ዝግጅት ሱማሌና ኤርትራ ላይ አደራጅቶ መሆኑን አታስታውሱም ወይ ? ...... የውሳኔአችሁ ዓላማ ኢትዮጵያን በድሎ፣ ጠላቷ ጣልያንን መጥቀም ከሆነ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ላይ እምነት አጥታ የራሷን አቋም ብትወስድ፣ አጠፋች ብላችሁ ለመውቀስ ወይም ለመደነቅ ትሞክሩ ይሆን ? ...... ጠላታችንን ጣልያንን ለመርዳት ብላችሁ በምታደርጉት ውሳኔ፣ የሚያስከትለውን አደጋ ለማየት ካልቻላችሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ኢትዮጵያ በድጋሚ መስዋዕትነት እንደማትቀበል መገንዘብ አለባችሁ። ....... »

ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን ሕሊና ለመቀስቀስ ብለው የተናገሩትን ቃል በቁም ነገር የሚያዳምጥ መልዕክተኛ አላገኙም። በመሠረቱ ሰው ሕሊናው የሚወቅሰው ሕሊና ሲኖረው ነው። ሆሴ አርሴ፣ ወደፊት በታሪክ ተወቃሽ

እሆናለሁ ብሎ ከማስብ ይልቅ፣ የዛሬው ጥቅሙ ስለሚበልጥበት፣ የሕሊና ችግር እላደረበትም:: ዛፍሩላህ ካን፣ የቅኝ ግዛት ቀንበር የወደቀባቸው ሕዝቦች የነፃነት ምሣሌና ተስፋ ከሆነችው ከኢትዮጵያ ይልቅ፣ ኮሎኒያሊስት ጣልያንን የመረጠው ለዛሬው ጥቅሙ ስለሆነ፣ የሕሊና ወቀሣ ይደርስብኛል ብሎ አልተጨነቀም:: ሌሎቹም እንደዚሁ ናቸው:: በንዑስ ኮሚቴ 17 ውስጥ የታጐሩት እነዚህ የጣልያን ወዳጆች፣ በተለይ በሱማሌ ጉዳይ የእነ ኮምት ስፎርሳን ፍላጐት ካሟሉ በኋላ፣ ወደ ኤርትራ ዶሴ ለመሻገር ሲዘጋጁ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ዋና መልዕክተኛ አምባሳደር ጀሴፕ (JESSEP) በአራት ኤገሮች ታጅቦ ለኤርትራ መፍትሔ አዲስ ሀሳብ ይዞ ቀረበ::

## የአሜሪካኖች የፌዴሬሽን መፍትሔ

ከኤርትራ ግዛት የምሥራቁና የደጋው ክፍል ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል፣ የምዕራባዊው ቆላ ወደ ሱዳን እንዲገባ፣ አሜሪካኖች ከእንግሊዞች ጋር ተባብረው ካለፈው ሚያዝያ ወር 1949 ዓ.ም ጀምሮ ውሳኔ ለማግኘት ያደረጉት ጥረት የሚጠብቁትን ውጤት ሳይሰጣቸው ቀረ:: በተለይም « ንዑስ ኮሚቴ 17 » ከተቋቋመ ጀምሮ ላቲኖቹና እስያውያኖቹ ከዓረቦቹ ጋር አንድነት ገጥመው፣ ጣልያን እንደሚፈልገው ኤርትራ ነፃ መንግሥት እንድትሆን፣ በድምፅ ብልጫ ለማስወሰን ዝግጅታቸው እየጠነከረ መጣ:: የአሜሪካና የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች ባደረጉት ክትትል፣ ለኤርትራ ነፃነት እንዲሰጥ ከአርጀንቲና መልዕክተኛ የቀረበው መፍትሔ፣ በኮሚቴው ውስጥ ሁለት ሶስተኛውን የድምፅ ብልጫ እንደሚያገኝ መረጃ አገኙ:: እንግዲህ ምን ይሻላል ?

– የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች በንዑስ ኮሚቴ 17 የሚዘጋጀው ረቂቅ ውሳኔ፣ ለዋናው ኮሚሲዮን በሚቀርብበት ጊዜ፣ ተቃዋሚ የሚሆኑ አገሮችን እያሰናዳን፣ እንዳይጸድቅ ለማድረግ ከአሁኑ መሥራት ያስፈልጋል አሉ::

– አሜሪካኖች ደግሞ የጣልያንን እጫፋሪዎች፣ እዚሁ ንዑስ ኮሚቴው ላይ ሀሳባቸውን ካላፈረስን፤ « ለኤርትራ ነፃነት » የሚለውን ረቂቅ ውሳኔ ይዘው ዋናው ኮሚሲዮን ላይ ከቀረቡ፣ ሶቪየት ሕብረትና ሳቴሊቶቹ ተረባርበው ጉድ ሊሠሩን ስለሚችሉ፤ አሁኑኑ አንድ እርምጃ ከመውሰድ መዘግየት የለብንም ብለው ተጨነቁ::

እንግሊዞች፤ ንዑስ ኮሚቴ ስለሚሰጠው ውሳኔ ከመጨነቅ ይልቅ፣ በዋናው ኮሚሲዮን ላይ እንዳይጸድቅ ከአሁኑ ጥረታችንን እናስተባብር የሚሉትን ሀሳብ፣ አሜሪካኖች አላመኑበትም:: ስለዚህ፣ ጉዳዩ ከዚሁ ከንዑስ ኮሚቴ እጅ ሳይወጣ በራሳቸው መንገድ ለኤርትራ አንድ አዲስ መፍትሔ ለመፍጠር ወሰኑ:: ከኮሚቴው አባሎች መካከል፤ ብራዚልን እና ሕንድን፣ ላይቤሪያንና ኢራቅን አስተባብረው፣ ኤርትራን በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር የሚያስተሳስር አዲስ ፕላን ጥቅምት 19 ቀን 1949 ዓ.ም « ለንዑስ ኮሚቴ 17 » አቀረቡ:: ይህ የፌዴሬሽን ፕላን በስውር ሲዘጋጅ የሰነበተው በአሜሪካ ዲፕሎማቶችና ኤክስፐርቶች ቢሆንም፣ እነሱ



በኒውዮርክ የተባበሩት መንግሥታት በአራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ
የተካፈሉት ያገር ፍቅር አንድነት ማህበር መሪዎች፤

ከግራ ወደ ቀኝ፤ ደጃዝማች በየነ ባራኪ -- ፕሬዚዳንት፤
ሼህ ሱሌማን አልዲን አህመድ -- አባል
አቶ ተድላ ባይሩ ዋና -- ጸሐፊ፤

(ጥቅምት 1949)

(ፎቶU.N)

ብቻቸውን ያስናዱት ነው ተብለው እንዳይታሙ፤ ፕሮጄው የቀረበው በአምስት አገሮች ስም ሆኖ ነው:: የፌዴሬሽኑን መልክ ለማብራራት ለንዑስ ኮሚቴ 17 በቀረበው መግለጫ ላይ የተጠቀሱት መሠረታዊ ጉዳዮች የሚከተሉት ነበሩ::

1. ኤርትራ የግዛቶቿ አንድነት ተጠብቀውላት፣ ለውስጥ አስተዳደር ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቷት፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘውድ ሥር በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ትቀላቀላለች::

2. በፌዴሬሽኑ አቋም፣ የውጭ ጉዳዩና የመከላከያው ሥልጣን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሲሆን፣ በኤርትራ የሚቋቋመው መንግሥት ደግሞ፣ የአገሪቱን የውስጥ አስተዳደር ለመምራት ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል::

3. ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር የምትቀላቀልበትንና፣ የውስጥ አስተዳደሯን የምትመራበት ሕገ መንግሥት፣ በአንድ ልዩ ኮሚሲዮን ይዘጋጃል:: ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት፤

ሀ/ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተመርጦ የሚሾም አንድ ኮሚሽነር (የኮሚሲዮኑ ሰብሳቢ)

ለ/ በኤርትራ ውስጥ ያሉትን ክርስቲያኖቹን፣ እስላሞቹንና የጣልያን ተወላጆቹን ለመወከል የሚመረጡ ሶስት ሰዎች፣

ሐ/ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባሎች፣ የታላቋ ብሪታንያ፣ የኢትዮጵያና የጣልያን፣ የብራዚልና የኢራቅ አገሮችን የሚወክሉ አምስት ሰዎች፤

በድምሩ ዘጠኝ ሰዎች፣ የሕገ መንግሥቱ አዘጋጅ ልዩ ኮሚሲዮን አባሎች ይሆናሉ:: የሚዘጋጀው ሕገ መንግሥት በመላ ኤርትራ፣ የዘርና የሀይማኖት ልዩነትን የሚያስወግድ፣ የሕዝቦችን እኩልነት የሚያረጋግጥ፣ ሰብዓዊ መብትንና መሠረታዊ ነፃነትን የሚጠብቅ እንዲሆን ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል::

ይህንን ለኤርትራ መፍትሔ እንዲሆን በአምስት አገሮች ስም፣ (አሜሪካ፣ ብራዚል፣ ሕንድ፣ ኢራቅ፣ ላይቤሪያ) የተዘጋጀው የፌዴሬሽን ፕላን፣ ጥቅምት 19 ቀን 1949 ዓ.ም ለንዑስ ኮሚቴ 17 ሲቀርብ፣ ከዋሽንግተን የስቴት ዲፓርትመንት ባለሥልጣኖች ደግሞ፣ ሮም ባለው አምባሳደራቸው በኩል፣ የጣልያን መንግሥት እንዲያውቀውና ድጋፉንም በቶሎ ስብሰባው ውስጥ ላሉት ወዳጆቹ እንዲያስተላልፍ ጠየቁ:: አሜሪካኖች ይህንን የፌዴሬሽን መፍትሔ የፈጠሩት፣ የኢትዮጵያን ጥያቄና የጣልያንን ፍላጐት የሚያረካ፣ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ክብር የሚሰጥ፤ ለራሳቸውም ለአሜሪካኖች በኢንተርናሽናል መስክ ላይ የተለየ ዝና የሚያስገኝላቸው ይሆናል ብለው ተስፋ በማድረግ ነው:: የኤርትራ ሕገ መንግሥት ሲዘጋጅ፣ በአገሩ ላይ ያሉት የጣልያን ተወላጆች፣ ወኪላቸውን መርጠው የሚካፈሉበት ስለሆነ፤ ቀጥሎም የአስተዳደሩ መንግሥት ከውጭ ጉዳይና ከመከላከያ በስተቀር፣ በሌላው በኩል ሙሉ ሥልጣን ስለሚኖረው፤ በኢትዮጵያ መንግሥት ጥቃት ሊደርስብን ይችላል ብለው የሚሰጉበት ጉዳይ ይወገድላቸዋል::

ለኢትዮጵያ ደግሞ የኤርትራን ግዛት በከፊል ከማግኘት ይልቅ፣ መላ ኤርትራን በፌዴሬሽን መቀበል የበለጠ ጥቅም የሚሰጥ ይሆናል። ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውና የመከላከያው ኃይል ሥልጣን በእጃቸው ስለሆነ፣ በዓለም ላይ የተለየ ክብር ያገኙበታል። ከዚህም በቀር ጣልያን ወደ ኤርትራ እንዳይመለስ ኢትዮጵያ የምትስጋበትን፣ ይህ የፌዴሬሽን አስተዳደር በሩን ስለሚዘጋላት፣ ከዚህ የተሻለ መፍትሔ መጠበቅ የለባትም። የተባበሩት መንግሥታትም እየተወሳሰበ የመጣውን የኤርትራን ፕሮብሌም ለመፍታት ከማይችልበት ደረጃ ላይ ስለደረሰ፣ ይህ የፌዴሬሽን መፍትሔ ሲጸድቅ፣ ድርጅቱ ከወደቀበት ትልቅ ችግር ይገላገላል።

እንግዲህ፣ የኤርትራ ጉዳይ ለሚመለከታቸው ሁሉ፣ በየመልኩ አጥጋቢ መልስ የሚሰጥና፣ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው ዓይነተኛ መፍትሔ ነው ብለው፣ አሜሪካኖች ይህን የፌዴሬሽን ፕላን ሲያቀርቡ፣ ከሁሉ ይበልጥ አስገራሚ ሆኖ የታየው፣ እንግሊዞች በምክሩም ሆነ በዝግጅቱ ተካፋይ ሳይሆኑ መቅረታቸው ነው። ሀሳቡን ሲጸንሱና ሲያቀናብሩ፣ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታትን ኢትዮጵያን፣ እኛ የምናስብላትን መቀበል ይኖርባታል ብለው ተካፋይ እንድትሆን ባያደርጉም፣ ታላቋ ብሪታንያ የመፍትሔው ዝግጅትና የአቀራረቡ አጃቢ አለመሆኗ፣ የሁለቱን ወንድማማች አገሮች ሕብረት፣ ምን ያህል እንደሚያሻክረው አሜሪካኖች ሳያስቡበት ቀርተዋል። እንግሊዞችን ወደ ጐን ትተው፣ ከላቲን ግሩፖች ብራዚልን፣ ከእስያ ሕንድን፣ ከዓረቦች ኢራቅን፣ ከአፍሪካ ላይቤሪያን ይዘው፣ በእነሱም አማካይነት የአብዛኛዎቹን አባል አገሮች የድጋፍ ድምፅ በመሰብሰብ ድል የሚመቱ መስሎ ታይቷቸው ነበር።

ኧርነስት ቤቨን (ERNEST BEVIN) ለጓደኛው ለአሜሪካዊው ዲን አቸሰን (DEAN ACHESON) በላከው መልዕክት፣ የጠለቀ ጥናት ሳይደረግና ሳይመከርበት፣ ለኤርትራ መፍትሔ ተብሎ በድንገት የቀረበውን ሀሳብ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት እስመደገፉን ከገለጸ በኋላ፣ የሁለቱ ኃያላን መንግሥታት አንድነት ሆኖ አለመሥራት፣ ሶቪየት ሕብረት ወደ አፍሪካ እንዲገባ በር መክፈት መሆኑ መታወቅ አለበት፣ ሲል አስጠንቀቀ። የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በዚህ ብቻ አልቆመም። በተባበሩት መንግሥታት ዘንድ ላለው መልዕክተኛ በሰጠው መምሪያ፣ የታላቋ ብሪታንያ አቋም ከአሜሪካ የተለየ መሆን እንዳለበት አስታውቆታል። «.....ኤርትራን በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ለማቀላቀል ከአሜሪካ መንግሥት የቀረበው ሀሳብ፣ አስፈላጊ ያልሆኑ ብዙ ችግሮች የሚፈጥርና፣ በሥራም ላይ ለማዋል የማይመች ስለሆነ፣ ታላቋ ብሪታንያ አትስማማም። ..... እንደሰማሁት የፌዴሬሽኑ ዓላማ የኤርትራን ግዛት በአንድነት የሚያጠቃልል ስለሆነ፣ የምዕራባዊው ቆላ ከሱዳን ጋር እንዲዋሀድ ከዚህ ቀደም የተስማማንበትን ያፈርሳል። ..... በዋሽንግተን ያለው የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ አምባሳደር፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለዲን አቸሰን እስተያየታችንን በመግለጽ እንዲነጋገርበት አድርጌአለሁ። ...... በአሁኑ ሰዓት በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ያለውን ሁኔታ በመመልከት፣ የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኛ የሚወስደው እርምጃ፣ በሚከተለው መልክ እንዲሆን እጠይቃለሁ።

1. « ..... ከኤርትራ ግዛት የምዕራባዊው ቆላ ወደ ሱዳን ገብቶ ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል፣ ከዚህ ቀደም የተስማማንበት መፍትሔ፣ የመጀመሪያ ምርጫችን ስለሆነ፣ አሁንም ብርቱ ጥረት እንዲደረግበት ያስፈልጋል።

2. ይህ የማይሳካ ሆኖ ለኤርትራ ነፃነት እንዲሰጥ፣ የጣልያን ወዳጆች እየጠነከሩ ከመጡ፣ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ልኮ የሕዝቡን ፍላጐት ያጣራ የተባለው ሀሳብ እንዲጸድቅ፣ ብርቱ ጥረት ማድረግ ነው::

3. ይህ በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰው ሀሳብ በሚጸድቅ ጊዜ፣ ሌላው ጥንቃቄ የሚጠይቀው፣ ከሚመደቡት የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ቡድኖች መካከል፣ ከመስኮብም ሆነ ከሳቴሊቶቹ አንድም አባል እንዳይመረጥ፣ብርቱ ጥረት እንዲደረግ ያስፈልጋል ...... »

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የቤቨን መምሪያ በግልጽ የሚያስረዳው፣ የአሜሪካኖች የፌዴሬሽን ፕላን፣ እንኳንስ እንዲጸድቅ፣ ንግግርም እንዲደረግበት የማይፈለግ መሆኑን ነው:: የአሜሪካኖቹን መፍትሔ አንቀበልም ያሉት እንግሊዞች ብቻ ሳይሆኑ፣ ኢትዮጵያና ጣልያንም አልፈለጉትም:: ከሁሉ ይበልጥ የዋሽንግተንን መንግሥት ያናደደው፣ የፌዴሬሽኑን ሀሳብ አልቀበልም ለማለት፣ የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ካርሎ ስፎርሳ የሰጠው የዕብሪት መልስ ነው:: « ..... የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ለኤርትራ ጉዳይ መፍትሔ እንዲሆን በማሰብ፣ ያደረገውን ሙከራ እናመሰግናለን:: ..... የጣልያን መንግሥት ለኤርትራ ነፃነት ከመስጠት በስተቀር ሌላ መፍትሔ አይቀበልም:: ..... የኤርትራ ሕዝብ ነፃነቱን ለመቀዳጀት የተዘጋጀ ከመሆኑም በላይ፣ በሥልጣኔ ረገድ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይበልጥ ወደፊት የተራመደ ስለሆነ፣ የውጭው ፖሊሲና የመከላከያው ጉዳይ የንጉሡ ሥልጣን ሆኖ፣ የውስጥ አስተዳደር መንግሥት ይቋቋምለታል የተባለው አይጠቅመውም:: ..... ከዚህ ይልቅ ኤርትራ ነፃነቷን ካገኘች በኋላ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ሰፊ የሆነ የኤኮኖሚ ግንኙነት እንዲኖር ቢታሰብ፣ የጣልያን መንግሥት ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል:: ..... »

ይህን በመሰለ አነጋገር የስባ ሰባቱ ዓመት ሽማግሌ ካርሎ ስፎርሳ፣ የዩናይትድ ስቴትስን መንግሥት እስከዚህ መዳፈሩ፣ ብዙዎቹን የፖለቲካ ታዛቢዎች አስገርሟል:: የአሜሪካኑ የዲን አቸሰን ቁጣ እና የእንግሊዙ የኤርነስት ቤቨን ኩርፊያ ቢደመርም፣ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ለጣልያን የተሰለፉላት ደጋፊዎች የሚያስተማምኑ ስለሆኑ፣ ካርሎ ስፎርሳ አልተበገረም:: የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የአሜሪካኖችን ሀሳብ ወርውሮ መጣሉ ኒውዮርክ እንደተሰማ፣ በንዑስ ኮሚቴ 17 ስብሰባ ላይ ዋናዎቹ ጠበቆቹ ፓኪስታንና አርጀንቲና « ..... የኤርትራ ሕዝብ ፈቃደኛነቱ ሳይጠየቅ፣ የፌዴሬሽን አስተዳደር እንዲቀበል ለመወሰን የተባበሩት መንግሥታት ሥልጣን የለውም ..... » የሚል ዲስኩራቸውን መለፈፍ ጀመሩ::

የፌዴሬሽኑ ፕላን ሲቀርብ፣ ከአሜሪካ ጋር ተባባሪ ደራሲዎች በመባል ከተሰለፉት አገሮች መካከል፣ ብራዚል እና ሕንድ፣ ለኤርትራ ጉዳይ ከዚህ የተሻለ መፍትሔ አይገኝም እያሉ ወገኖቻቸውን ለማሳመን ቢሞክሩም፣ የሚደግፉቸው አላገኙም:: የአሜሪካኖች ፕላን ባልተጠበቀ ሰዓት በድንገት የቀረበ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ጉዳዩን በኮድ ለጃንሆይ አስረድተው መልስ ለማግኘት ጊዜው ስለአጠረ፣ በራሳቸው ኃላፊነት አንድ አቋም መውሰድ ግዴታቸው ነበር::




የታላቋ ብሪታንያ እና የአሜሪካ መልዕክተኞች እርነስት ቤቨንና ፎስተር ደለስ፣ በኤርትራ ጉዳይ ስለሚወስዱት እርምጃ ሲወያዩ፤

(ኅዳር 1949)
(ፎቶU.N)

መጀመሪያ፤ ፌዴሬሽን የተባለው አሠራር፣ ለኢትዮጵያ በጣም እንግዳ ነገር ስለሆነ፣ በአገራችን ካለው የአስተዳደር ሥርዓት ጋር ለማጣጣምና በተግባር ላይ እንዲውል ለማድረግ፣ ሰፊ ጥናትና ዝግጅት ይጠይቃል:: ሁለተኛ፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን የምትቀላቀለው፣ ለአስተዳደሯ የራሷ የሆነ መንግሥት አቋቁማ ስለሆነ፤ የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን በውጭ ጉዳይና በመከላከያ ብቻ መወሰኑን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አይቀበሉትም:: ሶስተኛ፤ የፌዴሬሽኑ ሕገ መንግሥት የሚዘጋጀው፣ በአሥመራ ያሉት ጣልያኖች እንደ አገሩ ሕዝብ እኩል ተቆጥረው በሚካፈሉበት ኮሚሲዮን እንዲሆን መታሰቡን፤ የኤርትራ ሕዝብ አይቀበለውም:: ስለዚህ፤ ኢትዮጵያ ምንም እንኳን እንደ ጫልያን የዕብሪት መንፈስ በተዋህደው አነጋገር፣ አሜሪካንን ማስቀየም ጥቅሟ ባይሆንም፤ የቀረበውን ሀሳብ ለማጥናት ረዘም ያለ ጊዜ ስለሚጠይቅ፣ ለመቀበል አልተዘጋጀንም የሚል መልስ ብትሰጥ ይሻላል ተብሎ፣ በዚሁ ተፈጸመ::

አሜሪካኖች በታሪካቸው ብዙ ጊዜ እንደታየው፣ የረቀቀ ዲፕሎማሲ ኖርዋቸው አያውቅም:: እንደተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በመሳሰሉት የኢንተርናሽናል ጉባኤዎች ላይ፣ ለሚደቀኑት ችግሮች መፍትሔ ለማቅረብ የፈለጉ እንደሆነ፤ ከታላቁ ከዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ የሚሰጠው አስተያየት በታላቅ ክብር መደመጥ አለበት የሚል ስሜት ይሰማል:: ብዙ ተቃዋሚዎች የሚያጋጥማቸው፣ ሀሳባቸው ሁልጊዜ የሚነቀፍ ነው ተብሎ ሳይሆን፣ አብዛኛው በአቀራረባቸው የሚያሳዩት የበላይነት መንፈስ ነው:: ከዚህ በቀር ደግሞ በዓለም ጉዳይ ላይ የሚያቀርቡት ሀሳብ እንዲሰምር፤ የየአገሮቹን መንግሥታት የማስተባበርና የማግባባት፣ ቀደም አድርገው ጊዜውን የማዘጋጀት ጥበብ ይጐድላቸዋል:: በተለይም ወደ ኋላ የቀረውን ሕዝብ ለመርዳት በጐ ፈቃድ የላቸውም ማለት ቢያስቸግርም፣ ችግሩ የት ላይ እንደሆነ፣ የጠለቀ ጥናት በማድረግ ተረድተውለት አያውቁም:: ስለ ችግረኛው ዓለም ሕዝብ ጉዳይ መፍትሔ ፍለጋ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ፣ ከአገሩ የተፈጥሮ ሀብት አቅምና፣ ከሕዝቡ የሕይወት ልማድ ጋር የሚጣጣም ሀሳብ ሲሰነዝሩ፣ ታይተው አያውቁም:: በተመቻቸና ድሎት ባጠቃው ዓለም ላይ የሚኖሩ ስለሆኑ፤ ዳቦ ብርቁ ለሆነው ሕዝብ፣ እንደ ማሪ አንቱዋኔት (MARIE - ANTOINETTE) ኬክ ለምን አይቀርብለትም ? ለማለት ምንም ያህል አይቀራቸውም::

የድሀው አገር መንግሥት የነፃነት ባንዲራውን እያውለበለበ፣ ለተራበው ሕዝቡ እርዳታ ለማግኘት ከአሜሪካኖች ጋር ከሚያደርገው ውይይት ይልቅ፤ ከቀድሞ ገዥዎቹ ከኮሎኒያሊስቶቹ ጋር ሲከራከር፣ የበለጠ ግልጽ ይሆንለታል:: የቋንቋና የአስተሳሰብ መቀራረብ ስለአለ፣ የኮሎኒያሊስቶቹን ተንኮላቸውንም ሆነ በጐ ፈቃዳቸውን ለመገንዘብ ጊዜ አይወስድበትም:: የቀድሞ ገዥዎቹም፣ ከባለቤቱ ያላነሰ አንዳንድ ጊዜም በበለጠ፣ የአገሩ ችግር አምን ላይ እንደሚገኝና መድኃኒቱም ምን እንደሆነ፣ በትክክል ያውቁታል:: በተጨማሪም ቅን ሲሆኑ ለመርዳት፣ ሲጣመሙ ለማጥቃት፣ የተንኮላቸው ጥበብ የረቀቀ ስለሆነ፣ የቀድሞ ተገዥዎች ከቀድሞ ገዥዎቻቸው፣ ለአገራቸው ልማት ለማስገኘት ልበ ሰፊና እርቆ ተመልካች መሆን ይገደዳሉ:: አለበለዚያ እንደ ጊኔው ሴኩ ቱሬ (SEKOU TOURE) በር ዘግቶ፣ ነፃነት በድህነት በሚል ጩኸት ለሀያ አምስት ዓመታት፣ አገሩም ሳይለማ ሕዝቡም ሳያልፍለት ባዶ ቤት ይቀራሉ:: አሜሪካኖች ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ የችግረኛው ዓለም ሕዝብ ፕሮብሌም በአጭርና በረዥም ጊዜ ውስጥ እንዴት እንደሚፈታ፣ በትክክል አይታያቸውም:: ለልማት ፕሮጀክት በማዘጋጀት እንርዳ ብለው የተነሱም እንደሆነ፣ እነሱ ከደረሱበት ደረጃ የሚጀምር፣

ወይም እነሱ የተጠቀሙበትን ዘዴ እየነደፉ ወጭውን ከመጠን በላይ ከማሳበጥ በስተቀር፣ በአገሩና በድሀው ሕዝብ አቅም ሊሠራ የሚችል ፕላን መወጠን አይሆንላቸውም::

ለምሣሌ፤ ለኤርትራ የወደፊት ዕድል የሚሻለው፣ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ማቀላቀል ነው ብለው ሲነሱ፤ ስለ ሕገ መንግሥቱ አዘገጃጀትና፣ ስለ አቶኖሚው አስተዳደር ሥልጣን ያቀረቡት ፕላን፤ ቀጥሎም በድምፅ ብልጫ እንዲጸድቅላቸው፣ እንግሊዞችን ችላ ብለው ብቻቸውን የወሰዱት እርምጃ፤ የአሜሪካኖችን የአሠራር ጠባይ የሚያሳይ ነው:: የኤርትራ ሕዝብ በቅኝ ገዥዎች በሚሰቃይበት ዘመን፣ በገዛ አገሩ የዘር ልዩነት እየተደረገበት ከአራተኛ ክፍል በላይ እንዳይማር ክፉ ግፍ የተፈጸመበት ስለሆነ፣ በ1949 ዓ.ም የአቶኖሚውን መንግሥት ለመምራት የሚችል የሰው ኃይል የሌለው መሆኑን አሜሪካኖች አላስታወሱም:: በኤርትራ ያሉት የኮሎኒያሊስት ጣልያን ርዝራዦች፣ ለሃምሣ ዓመታት በሕዝቡ ላይ የፈጸሙት በደል አንሶ፣ የአገሪቱ የወደፊት ዕድል ሲመሠረት፣ የሕገ መንግሥት አዘጋጆች እንዲሆኑ ሲያሳስቡ፤ የአቶኖሚውንም መንግሥት የምትመሩት እናንተ ናችሁ እንደ ማለት የሚቆጠር መሆኑን አሜሪካኖች አልተረዱትም:: እንግሊዞችን በምክሩ ውስጥ ሳያስገቡ፣ ኢትዮጵያና ጣልያን መስማማታቸው ሳይታወቅ፣ ብን ሕንድና በነ ብራዚል ታጅበው፣ ጥቅምት 19 ቀን 1949 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ በአሥር ሰዓት፣ በንዑስ ኮሚቴ 17 ገበታ ላይ የዘረጉት የፌዴሬሽን ፕላን፣ የሚቀበለው አጥቶ እዚያው ጠረጴዛ ላይ እንደተበተነ ወድቆ ቀረ::

የሙሶሊኒ ወራሾች እነ ኮንት ስፎርሳ አርቀው የሚያዩ ቢሆን ኖሮ፣ በኤርትራ ለሚኖሩት ዜጎቻቸው ለፈ ዕድል ለማስገኘት፣ ከዚህ አሜሪካኖች ከለፉበት የፌዴሬሽን ፕላን የተሻለ መፍትሔ አልነበረም:: ጣልያኖች፤ ድፎ ዳቦ ካልቀረበልን እንቀምስም ብለው ሲንቀባረሩ ሙልሙሉ አመለጣቸው:: የአሜሪካኖች ፕላን ሰፋ ያለ ሙግት እንኳን ሳይደረግበት፣ ተድበስብሶ መና የቀረበት ዋናው ምክንያት፤ እንግሊዞች ስለተቀየሙ፤ ኢትዮጵያ ስለአዘነች፤ መስኮቦች ከነ ወገኖቻቸው ስለተቃወሙ አይደለም:: <u>የጣልያን መንግሥት አሜሪካኖች የነደፉለትን ጥቅም ባለመገንዘብ፤ አልፈልግም ብሎ ስለጣለው ብቻ ነው::</u>

የአሜሪካ የፌዴሬሽን ፕላን፣ ብዙም ሳያጣጥር በቶሎ ከሞተ በኋላ፤ በንዑስ ኮሚቴ 17 ውስጥ የጣልያን ወዳጆች፣ ለኤርትራ ነፃነት ለማስወሰን ጊዜው አሁን ነው ብለው መሯሯጥ ሲጀምሩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሎንዶንና በዋሽንግተን መካከል የተፈጠረው ቅሬታ በፍጥነት ተወግዶ፣ የዩናይትድ ስቴትስና የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች ሕብረት እቀድሞ ቦታው ተመልሶ ብቅ አለ:: የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲን አቸሰን፣ በዋሽንግተን የእንግሊዝን አምባሳደር ባነጋገሩበት ጊዜ፣ ለኤርትራ የፌዴሬሽን መፍትሔ ሲዘጋጅ፣ ከታላቋ ብሪታንያ ጋር ምክክር ሳይደረግ መቅረቱ ስህተት መሆኑን ስለአመኑበት፤ ከይቅርታ ጋር የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ወደነበረው የወንድማማችነት መንፈስ በፍጥነት እንዲመለስ አደረጉ::

አርጀንቲና እና ፓኪስታን ከአሜሪካ ቀርቦ የነበረውን መፍትሔ በተቃወሙ ጊዜ፤ « .... <u>የኤርትራ ሕዝብ ፈቃዱ ሳይጠየቅ የፌዴሬሽን ቀንበር ሊጫንበት አይገባም</u> .... » የሚል መግለጫ መስጠታቸው ይታወሳል:: ይህንን የተቃውሞ ዘዴ በመጠቀም፣ እንግሊዞችና አሜሪካኖች ከአንዳንድ እስያውያኖችና ከኮመንዌልዝ

አገሮች ጋር ሆነው፣ ለኤርትራ ነፃነት እንዲሰጥ በዓቲናቹ ስም፣ አርጀንቲና ያቀረበው መፍትሔ « ሕዝቡ ነፃነት መፈለግ አለመፈለጉ ሳይጠየቅ ሊወሰን አይቻልም » አሉ::

የኤርትራ ግዛት ለኢትዮጵያና ለሱዳን እንዲከፈል ተደጋግሞ የቀረበው ሀሳብ፣ በአሁኑ ሰዓት ለመጽደቅ ምንም ዓይነት ዕድል እንደሌለው አሜሪካና እንግሊዝ ተስፋ ሲቆርጡ፤ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ልኮ የሕዝቡን ፍላጐት እንዲያጣራ፣ ከዚህ ቀደም በአውስትራሊያ ቀርቦ የነበረውን ሀሳብ እንደገና ለመቀስቀስና ደጋፊዎች ለመሰብሰብ እርምጃ ወሰዱ:: እነዚህ ለጣልያን ያደሩ የላቲን አሜሪካ በጥባጮች በአሁኑ ሰዓት የሚያደርጉትን ተንኮል ለማገድና የአንድ ዓመት ጊዜ ለማግኘት፤ ከዚህ የተሻለ ዘዴ ሊኖር እንደማይችል አርግጠኞች ሆኑ:: በመሠረቱ የጣልያንም መንግሥት ቢሆን ቀደም ሲል ለደጋፊዎቹ የሰጠው መምሪያ፣ ለኤርትራ የነፃነቱ ጉዳይ የማይሳካ ከሆነ፣ የሕዝቡ ፍላጐት ይታወቅ ተብሎ መርማሪ ኮሚሽን እንዲላክ ማስደረግ መሆኑ ይታወሳል:: ስለዚህ ነፃነት ይሰጥ ከሚለው ግሩፕ፣ የሕዝቡ ፍላጐት ይጠየቅ የሚለው ወገን እንዲያሸንፍ፤ እንግሊ አሜሪካኖች በሕብረት የሚያደርጉት ጥረት፣ ዞሮ ዞሮ የጣልያንን ሁለተኛ ምርጫ ለማስወሰን ስለሆነ፤ እነ ኮምት ስፎርሳ እያሾፉ ከመተረክ በስተቀር ተጐዳን ብለው አልጮሁም::

ለኤርትራ ነፃነት ይሰጥ የሚባለውንና በሌላ በኩል ደግሞ መርማሪ ኮሚሽን እንዲላክ የሚታሰበውን በብርቱ የተቃወመች ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች:: አራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ልከው አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀልን መፈለጉ ስለተረጋገጠ፣ በድጋሚ ሌላ መርማሪ ያስፈለገበት እውነተኛው ምክንያት ምንድን ነው ? በማለት የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ደጋግመው ቢጠይቁም መልስ አላገኙም:: የንዑስ ኮሚቴ 17 ዲክታተሮች የውስጥ ደንብ እንደሚያስረዳው፤ የተፈረደበት ጥያቄ ማቅረብ የለበትም:: ዳኛውም መልስ እንዲሰጥ አይገደድም::

ከጥቅምት 11 ቀን እስከ ኅዳር 1 ቀን 1949 ዓ.ም ድረስ « ንዑስ ኮሚቴ 17 » ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ለሊቢያ፣ ለሱማሌና ለኤርትራ መፍትሔ ለማቀናበር ሲያማታ እና ሲያምታታ ከሰነበተ በኋላ፣ በመጨረሻ አዘጋጅቶ ያወጣው ረቂቅ ውሳኔ፣ ኢትዮጵያ እንደጠበቀችው ጣልያንን የሚያረካና የቀ.ኃ.ሥን መንግሥት የሚያሳዝን ሆነ::

1. ሊቢያ፣ የትሪፖሊታንያ፣ የሲረናይካና የፈዛን አውራጃዎቿ በአንድነት ተዋህደው ከጥር 1 ቀን 1952 ዓ.ም በፊት ነፃነቷ እንዲሰጣት፣

2. ሱማሌ፣ ለሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ጣልያን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድራት፣

3. ኤርትራ፣ አምስት የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች የሚሰየሙበት ኮሚሲዮን ወደ ኤርትራ ተልኮ፣ የሕዝቡ ፍላጐት ምን እንደሆነ መርምሮ የሚያቀርበው ራፖር ከታየ በኋላ፣ በመጭው ዓመት በሚደረገው ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ውሳኔ እንዲሰጠው፤ በንዑስ ኮሚቴ 17 ገበታ ላይ ወንበር ከያዙት ሀያ አንድ አገሮች፣ አሥራ ስባቱ ተስማምተው፣ ለዋናው ኮሚሲዮን አስተላለፉ:: ይህ « ንዑስ ኮሚቴ 17 » ሥራውን

ከመጀመሩ በፊት ጥቅምት 10 ቀን 1949 ዓ.ም አባሎቹ ሲመረጡ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ « የጣልያን ኮሚቴ » ብለው እንደሰየሙት ሁሉ፣ በእውነትም የጣልያን ኮሚቴ መሆኑን በአሠራሩ ደህና አድርጉ አረጋገጠ።

የንዑስ ኮሚቴው ረቂቅ ውሳኔ መጀመሪያ በዋናው ኮሚሲዮን ቀጥሎ በጠቅላላው ጉባኤ መታየት ስለአለበት፤ እስከ መጨረሻው ተሟግቶ ለማስለወጥ ተስፋ አንቆርጥም ብለው የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ትግላቸውን ቀጠሉ።

# የዋናው ኮሚሲዮን ችሎት

መላው የተባበሩት መንግሥታት አባሎች የሚካፈሉበት የዋናው ኮሚሲዮን ጉባኤ፣ በንዑስ ኮሚቴ «17» ተዘጋጅቶ የቀረበለትን ረቂቅ ውሳኔ በሚመረምርበት ጊዜ፣ ለትክክለኛ ፍርድ የቆሙ አንዳንድ አገሮች በሚሰጡት አስተያየት፤ የጣልያንና የግሩፖቹ ሤራ ሊፈርስ ይችላል በማለት የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ተስፋ አድርገው ነበር።

ጉባኤው ሥራውን ሲጀምር፣ የዩጐዝላቪያና የኒውዚላንድ፣ የላይቤሪያና የፊሊፒን መልዕክተኞች በንዑስ ኮሚቴ 17 የተዘጋጀው መፍትሔ ኢትዮጵያን ለማሳዘን የተሰነዘረ በመሆኑ፣ ዋናው ኮሚሲዮን ለውሳኔ እንዳይቸኩል አስጠነቀቁ። እንደዚሁም የታላቋ ብሪታንያ እና የአሜሪካ እንደራሴዎች በሰጡት መግለጫ፣ ንዑስ ኮሚቴ 17 እንደጠየቀው ለሁለተኛ ጊዜ መርማሪ ኮሚሲዮን ወደ ኤርትራ መላክ፣ ጊዜ ለመፍጀት ካልሆነ በስተቀር፣ ከዚህ ቀደም በአራቱ ኃያላን መንግሥታት ቡድኖች የተደረገውን ጥናት ሊለውጠው አይችልም በማለት ጉባኤውን ለማሳመን ሞከሩ። በተለይም የኒውዚላንድ መልዕክተኞች መሪ፣ ሰር ካርል በሬንድሰን (SIR CARL BERENDSEN) በገለጸው አስተያየት፣ « .... በዘር፣ በባሕልና በታሪኩ ያለውን አንድነት አምኖበት፤ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር እንቀላቀል ብሎ ሲጠይቅ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንቅፋት መሆን አይገባውም ... » የሚል አስተያየት ሰጥቶ ነበር። ነገር ግን በብዛትም ሆነ በአፈኝነት የኮሚሲዮኑን ገበታ አንቀው የያዙት የጣልያን ወገኖች፣ መድረኩን እየተቀባበሉ የንዑስ ኮሚቴ 17 የሥራ ውጤት እጅግ የሚደነቅና የሚመሰገን ከመሆኑም በላይ፣ ከዚህ ከቀረበው ሌላ የተሻለ መፍትሔ አይገኝም እያሉ፣ በጩኸት አዳራሹን ስለአፈኑት፣ በጣም ጥቂቶቹ የኢትዮጵያ ደጋፊዎች አስተያየት አልተደመጠም።

የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ባደረጉት ንግግር፣ « የንዑስ ኮሚቴ 17 » አባሎች ሆነው የተመረጡት የጣልያን ወገኖች፤ የሮማ መንግሥት የሰጣቸውን መምሪያ ነጥብ በነጥብ ተከትለው ያዘጋጁትን ሕገ ወጥ የሆነ ረቂቅ ውሳኔ፣ እነሱ ራሳቸው አድናቂዎች፤ እነሱ ራሳቸው አመስጋኞች ሆነው፣ የሚያደርጓቸውን የማወናበጃ ዲስኩሮች፣ ኮሚሲዮኑ እንዲገነዘበው በሰፊው ጥረው ነበር። እንደተባለውም የጣልያን አፈ ጉባኤዎች በአርጀንቲናና በፓኪስታን ተቀዳሚነት « ...... ለኤርትራ ጉዳይ ተገቢው መፍትሔ ነፃነትን መስጠት ነበር። ነገር ግን አንዳንድ አገሮች የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ልኮ፣ የሕዝቡን ትክክለኛ ፍላጐት አጣርቶ ያቅርብልን ብለው ስለአመለከቱ፤ ሁላችንም በዚህ ሀሳብ